# ታሪካዊ ሥነ-መለኮት

# አመጣጡና ትንተናው

በዶክተር ፓውል እንዝ
Dr. Paul Enns

ተርጓሚ
ምኒልክ አስፋው እና ሰሎሞን ጥላሁን

ልዩ ረዳት
ሰብለወርቅ ጳውሎስ

ኤዲተር
ገበየሁ አየለ

Published by
የላፕስሊ/ብሩክስ ፋውንዴሽን
LAPSLEY/BROOKS FOUNDATION
Dallas, Texas --- Addis Ababa
U.S.A. Ethiopia

1999 - 1991

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved
1991 ዓ.ም. (1999)

ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው
“Historical Theology”
Written and copyrighted
by Dr. Paul P. Enns
1989
being a portion of the
“Moody Handbook of Theology”
Moody Press
Chicago, Ill. U.S.A.
ከሚለው መጽሐፍ ሲሆን
የታተመውም በደራሲው ፈቃድ ነው።

አሳታሚ
የላፕስሊ/ብሩክስ ፋውንዴሽን
ስልክ 201464   ፖስታ 41221
አዲስ አበባ   ኢትዮጵያ

Publisher
Lapsley/Brooks Foundation
Dallas, Texas, U.S.A.

# ምስጋና

ይህ የትርጉም ሥራ ዳር እንዲደርስ ሞያዊ እርዳታ በመስጠት ረገድ የተሳተፉትን ኢትዮጵያውያን በሙሉ፥ በተለይም እንግዳሽ ማርቆስ፥ ትፍስህት ለማና ሚሚ ይልማ ላደረጉት አስተዋጽዎ ከልብ እናመሰግናለን።

# የመጽሐፍ ማውጫ

ምዕራፍ 1 -- የታሪካዊ ሥነ-መለኮት መግቢያ ............... 11
- የታሪካዊ ሥነ-መለኮት ፍቺ ............... 11
- የታሪካዊ ሥነ-መለኮት ዓላማ ............... 11
- የታሪካዊ ሥነ-መለኮት ክፍሎች ............... 12
- የታሪካዊ ሥነ-መለኮት እድገት ............... 12
  - ሥነ-መለኮት በጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ............... 12
  - ሥነ-መለኮት በመካከለኛው ዘመን ............... 14
  - ሥነ-መለኮት በዘመነ-ተሐድሶ (Reformation) ............... 15
  - ዘመናዊው ሥነ-መለኮት ............... 17

ምዕራፍ 2 -- ጥንታዊ ሥነ-መለኮት ............... 18
- ሐዋርያት አባቶች ............... 18
  - የሐዋርያት አባቶች ትምህርተ ቅዱሳት መጻሕፍት ............... 19
  - የሐዋርያት አባቶች ትምህርተ እግዚአብሔር ............... 19
  - የሐዋርያት አባቶች ትምህርተ ክርስቶስ ............... 19
  - የሐዋርያት አባቶች ትምህርተ ደኅንነት ............... 20
  - የሐዋርያት አባቶች ትምህርተ ቤተ ክርስቲያን ............... 20
  - የሐዋርያት አባቶች ትምህርተ ፍጻሜ-ዘመን ............... 21
- የጥንት አቃቢያነ-እምነት ............... 22
  - የአቃቤ እምነታውያን ትምህርተ ቅዱሳት መጻሕፍት ............... 23
  - የአቃቤ እምነታውያን ትምህርተ እግዚአብሔር ............... 24
  - የአቃቤ እምነታውያን ትምህርተ ክርስቶስ ............... 25
  - የአቃቤ እምነታውያን ትምህርተ ቤተ ክርስቲያን ............... 25
- ጥንታዊ ኑፋቄዎች ............... 26
  - ከሙሴ ሕግ ጋር የተያያዙት ............... 26
  - ከኖስቲካዊ (Gnostic) ፍልስፍና ጋር የተያያዙ ............... 26
  - ማርሲዮን ከተባለው ሰው ካኖን ጋር በተያያዘ መልኩ ............... 27
- የካኖን ድንጋጌና የእምነት መግለጫዎች ............... 29

- የእምነት መመሪያ ........ 29
- የአዲስ ኪዳን ካኖን ........ 29
- የሐዋርያት የእምነት መግለጫ ........ 30
- ♦ ጥንታዊ አስተምህሮ ሥላሴ ........ 31
  - ሞናርኪያኒዝም [Monarchianism] ........ 31
  - አርዮሳዊነት ........ 33
  - የኒቅያው ጉባኤ ........ 33
  - የቁስጥንጥንያው ጉባኤ ........ 34
- ♦ ጥንታዊ አስተምህሮ ክርስቶስ ........ 35
  - መነሻ ........ 35
  - አቡሊናርዮሳዊነት ........ 35
  - ንስጥሮሳዊነት ........ 36
  - አውጣኪነት ........ 36
- ♦ ጥንታዊው ሥነ-ሰብእነት ........ 38
  - ኃጢአትና ጸጋ ........ 38
- ♦ ጥንታዊው አስተምህሮ ደኅንነት ........ 41
  - ሥርየትና ደኅንነት ........ 41
  - የደኅንነት አፈጻጸም ........ 41
- ♦ ጥንታዊው አስተምህሮ ቤተ ክርስቲያን ........ 42
  - ጥምቀት ........ 42
  - የጌታ እራት ........ 43
- ♦ ጥንታዊው የሥነ-ፍጻሜ አመለካከት ........ 44

ምዕራፍ 3 -- የመካከለኛው ዘመን ሥነ-መለኮት ........ 46

- ♦ በመካከለኛው ዘመን የነበሩ ክርክሮች ........ 47
  - የኢኮኖላትሪያ (Iconoclastic) ክርክር ........ 47
  - የ'ፊሎክዌ' (Filioque) ክርክር ........ 48
  - የአስቀድሞ መወሰን አስተምህሮ (Predestination) ክርክር 48
  - የጌታ እራትን አስመልክቶ የነበረ ክርክር ........ 49
- ♦ የመካከለኛው ዘመን ሊቃዊነት ........ 50
- ♦ የመካከለኛው ዘመን ሥነ-ሰብእነት (Anthropology) ........ 51

አንሰለም ............................................................ 51
ቶማስ አኩናስ ............................................................ 51
የማርያም ኃጢአት የለሽነት (ቅድስና) ............................ 52
መደምደሚያ ............................................................ 52
♦ የመካከለኛው ዘመን አስተምህሮ ደኅንነት ......................... 53
ሥርየት ............................................................ 53
የእግዚአብሔር ጸጋ ............................................................ 54
እምነትና ሥራዎች ............................................................ 55
ጽድቅ ............................................................ 55
♦ የመካከለኛው ዘመን አስተምህሮ ቤተ ክርስቲያን ............... 55
የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች ............................................ 55
ቅጽስና ............................................................ 57
የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ............................................ 58


## ምዕራፍ 4 -- የዘመነ ተሐድሶ (የሪፎርሜሽን) ሥነ-መለኮት


............................................................ 59
♦ የተሐድሶ መሠረቶች ............................................ 59
♦ የዘመነ ተሐድሶ መሪዎች ............................................ 61
ማርቲን ሉተር (1483-1546) ............................................ 61
ጆን ካልቪን (1509-1564) ............................................ 62
ኧልሪክ ዝዊንግሊ (1484-1531) ............................................ 63
♦ የዘመነ ተሐድሶ ትምሕርተ ቅዱሳት መጻሕፍት ........................ 64
የሉተር አስተምህሮ ............................................ 64
የዝዊንግሊ አስተምህሮ ............................................ 65
የካልቪን አስተምህሮ ............................................ 66
♦ የዘመነ ተሐድሶ ትምህርተ ክርስቶስ ............................ 67
♦ የዘመነ ተሐድሶ ሥነ-ሰብአዊነት ............................ 67
የተሐድሷውያን አመለካከት ............................................ 67
ሱስንዮሳዊው አመለካከት ............................................ 68
አርሚኒዮሳዊ አመለካከት ............................................ 68
♦ የዘመነ ተሐድሶ ትምሕርተ ደኅንነት ............................ 69

አስቀድሞ መወሰን (Predestination) ................................. 69

ሥርየት ................................................................. 69

እምነትና ሥራ ......................................................... 71

♦ የዘመነ ተሐድሶ ትምሕርተ ቤተ ክርስቲያን ........................ 74

ሉተራዊ አመለካከት ................................................... 74

ካልቪናዊ አመለካከት ................................................ 75

የአናባፕቲስቶች (Anabaptists) ወይም የጸግማዊ መጥምቃውያን አመለካከት ....................................... 77

## ምዕራፍ 5 -- ዘመናዊ ሥነ-መለኮት ................................ 80

♦ ኪዳናዊ ሥነ-መለኮት ................................................ 80

♦ ሉተራዊ ሥነ-መለኮት ................................................ 81

♦ ካልቪናዊ ሥነ-መለኮት ............................................... 82

♦ ለዘብተኛ ሥነ-መለኮት ............................................... 83

♦ የአዲሱ ቀጥተኛ ሃይማኖት ሥነ-መለኮት ............................ 85

♦ መደምደሚያ ........................................................... 87

## አባሪዎች

♦ የተለያዩ የሥነ-መለኮት ትምህርቶች መግለጫ .................. 89

♦ በዚህ መጽሐፍ የተጠቀሱ የእንግሊዝኛ ቃላት ..................... 95


........................................................

## ሠንጠረዦች


♦ የአስተምህሮ ክርስቶስ ኑፋቄዎች ...................................... 37

♦ ፔላጊዩስ እና አውግስጢኖስ ስለ ኃጢአት ያላቸው አመለካከት ............................................................................ 40

♦ የመካከለኛው ዘመን ቅዱሳት ምስጢራትና መንፈሳዊ ጥቅማቸው ......................................................... 56

♦ ተሐድሷውያን (ሪፎርመርስ) በኃጢአት ሥርየት ላይ ያላቸው አመለካከት ............................................................ 70

♦ ተሐድሷውያን ስለ ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ሕጎች ያላቸው አመለካከት ............................................................ 74

♦ የተሐድሷውያን ሥነ-መለኮት ........................................ 78

♦ ሥነ-መለኮታዊ አመለካከት፥ በዘመናዊ ቤተ ክርስቲያን .... 87

# ታሪካዊ ሥነ-መለኮት
# አመጣጡና ትንተናው

# ማሳሰቢያ

- የመጽሐፉ ተርጓሚ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ አንዳንድ ክፍሎችን ግልጥ ለማድረግ ሲል በደራሲው ፍቃድ አንዳንድ ማብራሪያዎችን ጨምሯል።
- የተጠቀሱት ጊዜያት የተመለከቱት በአውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ነው።
- በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን ማዕረጎች፥ የሥራ ተግባሮች እና ቢሮዎችን ከምዕራብ ሀገር ቤተ ክርስቲያኖች ጋር ማመሳሰል አስቸጋሪ ነው። የኢትዮጵያው ቤተ ክርስቲያን ድርጅታዊ መዋቅር በብዛት የሚመሳሰለው ፕሪስት/ Priest፥ ቢሾፕ/Bishop፥ አርችቢሾፕ/Archbishop፥ ካርዲናል/ Cardinal፥ ፖፕ/Pope ከሚገኙባት ከሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ጋር ነው። "ፕሪስት" (ቄስ) በአንድ ቀበሌ የሚገኝ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊ ነው። "ቢሾፕ" (ጳጳስ) በአንድ አውራጃ ውስጥ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያን ቄሶች የበላይ ኃላፊ ነው። "አርችቢሾፕ" (ሊቀ ጳጳስ) በአውራጃዎች ውስጥ ለሚገኙ ጳጳሳት ኃላፊነት አለበት። "ፖፕ" (የሮም ጳጳስ) ወደ 100 የሚጠጉ ጳጳሳትን ("ካርዲናሎች") አማካሪዎቹና በከፍተኛ በታ ላይ አስተዳዳሪ እንዲሆኑ ይመርጣቸዋል። የሮም ጳጳስ በዓለም ዙሪያ በሚገኙ የሮም ካቶሊክ አብያተ ክርስቲያን ላይ ራስ ለመሆን በካርዲናሎች ይመረጣል።
- ተጨማሪ ጥናት ለማድረግ የሚፈልጉ ሰዎችን ለመርዳት ሲባል አንዳንድ ስሞችና አገላለጦች በጽሑፉ ለመጀመሪያ ጊዜ በተከሰቱ ወቅት በእንግሊዝኛ በቅንፍ ተመልክተዋል። አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜም የቃላቱ የአማርኛ አነባበብ በቅንፉ ውስጥ ታክሏል። የሁሉም ቃላት ዝርዝር በፊደል ቅደም ተከተል በመጽሐፉ መጨረሻ ይገኛል።
- የሥነ-መለኮት ትምህርቶችን የሚያመለክቱ ቃላትና ስሞች አጭር ማብራሪያ በጽሑፉ መጨረሻ ቀርቧል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች እነዚህ ማውጫዎች ለጥናታቸው ጠቃሚ ሆነው ያገኟቸዋል ብለን እናምናለን።

# - 1 -

# የታሪካዊ ሥነ-መለኮት መግቢያ

## የታሪካዊ ሥነ-መለኮት ፍቺ

ታሪካዊ ሥነ-መለኮት በዘመናት መካከል ያለው ክርስቲያናዊ ነገረ መለኮት የተገለጠበት ነው። ይህ የክርስትና ሥነ-መለኮት የዳበረበት፥ ያደገበት፥ በውስጡም የተከሰቱ ለውጦች የሚታወቁበት መንገድ ነው። ታሪካዊ ሥነ-መለኮት እንደ አስተምህሮ እግዚአብሔር፥ አስተምህሮ መንፈስ ቅዱስ፥ አስተምህሮ ክርስቶስ፥ አስተምህሮ ደኅንነትና አስተምህሮ ቤተ ክርስቲያን የመሳሰሉትን አበይት አስተምህሮዎች አመሠራረት፥ አዘገጃጀትና አስተዳደጋቸውን ይመረምራል።

## የታሪካዊ ሥነ-መለኮት ዓላማ

የታሪካዊ ሥነ-መለኮት ዓላማ፥ የቤተ ክርስቲያንን ቀኖናዎች ታሪካዊ ጅማሬ መግለጥ፥ እንዲሁም ቀኖናዎቹ ያስከተሉትን ለውጦችና እድገቶች መፈተሽ ነው። ታሪካዊ ሥነ-መለኮት በአስተምህሮዎች ምሥረታ ውስጥ ያለውን የእድገትና የለውጥ ክፉና ደግ ጎን ለማየት ጥረት ያደርጋል። የቤተ ክርስቲያን አቅጣጫ በሥነ-መለኮት አቅጣጫ ላይ ተጽእኖ ማድረጉ እውነት ነው። "ዘመነ-ሊቃዊነት" [Scholasticism] (11-14ኛ ምዕተ ዓመት)* ለአመንክዮ በሰጠው ትኩረት ሳቢያ፥ ሥነ-መለኮት ከእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እንዲያፈነግጥ ተጽእኖ ሆኖበታል። በአንጻሩ ደግሞ ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት ሉዓላዊነት ያደላው "ዘመነ-ተሐድሶ" ["Reformation"] (16ኛ ምዕተ ዓመት)፥ ሥነ-መለኮትን በጸጋ ላይ አጽንኦት ወደ መስጠቱ አቅጣጫ መልሶታል። የ"ዘመነ-አብርሆት" ["Enlightenment"]** ፍልስፍና ግን ሥነ-መለኮት ወደ ፀረ-ሉዓላዊነት (ማለት ከተፈጥሮ የሚልቅ ነገር የለም) ወደሚለው አመለካከት እንዲያደላ አድርጎታል።

ታሪካዊ ሥነ-መለኮት በዘመናት መካከል የሆነውን የሥነ-መለኮት እንቅስቃሴ ያስረዳል፥ ይገልጣል። ከዚህ በመነሣት አስተምህሮዎች እንዴት እንደበቀሉና እንዳቆጠቆጡ፥ እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ ከቅዱሳት መጻሕፍት እንዴት እንዳፈነገጡ ማወቁ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው።

---

* በዚህ ርእስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት አባሪ አንድን ይመልከቱ።

---

** በአውሮፓ ታሪክ ውስጥ 18ኛ ምዕተ ዓመት "ዘመነ-አብርሆት" [Age of Enlightenment] በመባል ይታወቃል።

# የታሪካዊ ሥነ-መለኮት ክፍሎች

በታሪካዊ ሥነ መለኮት እድገት ውስጥ አራት አበይት ክፍሎች ይታወቃሉ፦ (1) ጥንታዊ ሥነ-መለኮት (ከመጀመሪያው ክፍለ ዘመን-590 ዓ.ም. የነበረው)፤ (2) የመካከለኛው ዘመን ሥነ-መለኮት (590-1517 ዓ.ም.)፤ (3) የዘመነ-ተሐድሶ ሥነ-መለኮት (1517-1750 ዓ.ም.)፤ (4) ዘመናዊ ሥነ-መለኮት (ከ1750 ዓ.ም. እስከ አሁን ያለው)።

# የታሪካዊ ሥነ-መለኮት እድገት

## *ሥነ-መለኮት በጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን*

በክርስቶስ ምድራዊ ሕይወት የተፈጸሙ ሁኔታዎችን ያወቁና ለሐዋርያት ዘመን ቅርብ የነበሩ ሐዋርያት አባቶች የተዉልን ጽሑፎች ታላቅ ቁምነገርን የያዙ ናቸው። እንደ ትምህርተ ሥላሴ፥ የክርስቶስ መለኮትነትና ዘላለማዊነት፥ እንዲሁም ደኅንነት ባሉ ጠቃሚ ጉዳዮች ላይ ያተኩራሉ። ዐቃቤ እምነታውያን [Apologists] ደግሞ በሁለተኛው ምዕተ ዓመት የተነሡ ሌሎች ቡድኖች ሲሆኑ፥ ተቺዎችን በመቃወምና ለክርስትና በመቆም ስለ ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች ፈላስፎችንና ነገሥታትን ሞግተዋል። ከክርስትና እምነት ማፈንገጥ የተጀመረውም በዚህ ዘመን ነበር። የአይሁድ ሃይማኖት ተከታዮች ከሙሴ ሕግ ጋር ጥብቅ አሉ። ኖስቲካውያን [Gnostics]* የተባሉት ቡድኖች ደግሞ ክርስትናን "ቁስ አካል እርኩስ ሲሆን መንፈስ ጥሩ ነው" ከሚለው ፍልስፍና ጋር ሊያዛምዱት ከጀሉ። ማርቅያን [Marcion]* የተባለ ሰውና ተከታዮቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መካተት ስላለባቸው መጻሕፍት ብዛት የተለያዩ አሳቦችን በማምጣት ጥርጣሬና ውዝግብ አስነሡ። ሞንታኑስ [Montanus]* የተባለ ሰው ተከታዮች ደግሞ አስተምህሮ መንፈስ ቅዱስንና ሥነ-ፍጻሜን በተዛባ ትምህርታቸው በከሉት። በዚህም ሳቢያ ክርስትና ገና ከጅማሬው በመከላከልና በማጥቃት ተግባር ውስጥ ለመግባት ተገዶ ነበር። የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን በማርቅያን ክፉ ትምህርት ሳቢያ ሃያ ሰባቱን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የጸና ካኖን ** ለማዘጋጀት ተገደደች።

---

* በዚህ ርእስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት አባሪ አንድን ይመልከቱ።

---

** "ካኖን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የጥንት አብያተ ክርስቲያን የእምነታቸው መመሪያና መተዳደሪያ እንዲሆኗቸው የተቀበሏቸውን የመጻሕፍት ስብስብ ነው። ቃሉ ተመሳሳይ ከሆነ የግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን፥ ትርጉሙም "የሚለካ" ወይም "መለኪያ" ማለት ሊሆን ይችላል። (ማብራሪያው በሚቀጥለው ገጽ ይቀጥላል።)

አስተምህሮ-ሥላሴም አርዮስ [Arius]* ከተባለ ሰው ተግዳሮት ገጠመው። ይህ ሰው አትናቴዎስ [Athanasius] ከተባለ ሰው ጋር ያደረገው ያላቋረጠ ሙግት የክርስቲያኑን ጎራ አጥለቅልቆት ነበር። የኒቅያው [Nicea] ጉባኤ በ325 ዓ.ም. ታሪካዊውን አስተምህሮ-ሥላሴ አጸደቀ። በዚህም መሠረት ክርስቶስ ከአብ ጋር የባሕርይ እኩልነት ያለው መሆኑ ግንዛቤ አገኘ።

ቤተ ክርስቲያን በአራተኛውና በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በክርስቶስ ጣምራ ባሕርያት መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ ብዙ ስትታገል ቆይታለች። በዚሁ ትግል መሠረት ትክክለኛ የሆነውና ስሕተተኛ የሆነው አመለካከት መጀመሪያ በ325 ዓ.ም. በኒቅያ፥ በኋላም በ451 ዓ.ም. በኬልቄዶን [Chalcedon] ተገልጧል።

ሰው ከውርስ ኃጢአት ነፃ ስለሆነ መልካም የሆነውን የመምረጥ ችሎታ አለው፥ በሚለውና ፔላጊዩስ [Pelagius]* የተባለ ሰው ከሚያቀነቅነው ትምህርት የተነሣ ከአውግስጢኖስ [Augustine] ጋር የተፈጠረው ግጭት ተባባሰ። አውግስጢኖስ፥ ሰው በኃጢአቱ ሳቢያ ሙሉ በሙሉ ከወደቀበት ሁኔታ ለመነሣት፥ የእግዚአብሔር ፀጋ ያስፈልገዋል የሚልና የጸጋ ትምህርት ደጋፊ የሆነ ታላቅ ሰው ነበር። ይሁን እንጂ መለስ አድርጎ ደግሞ ከደኅንነት በፊት ለተፈፀሙ ኃጢአቶች ማስወገጃ ጥምቀት አስፈላጊ ነው በማለት አስተማረ። በዚሁ መሠረት በጥምቀት የሚገኝ ደኅንነትና የሕጻናት ጥምቀት የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ሆኑ።

---

* በዚህ ርእስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት አባሪ አንድን ይመልከቱ።

---

በሃይማኖት አካባቢዎች "ካኖን" በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ተጽፈዋል የሚባሉትንና በዚህም ምክንያት በመንፈሳዊነት ረገድ በጣም ዋጋ ያላቸውን መጻሕፍት ያመለክታል። ስለዚህም ነው ከሌሎች በርካታ የክርስቲያናዊ ጽሑፎች የተለዩት። የካኖን ሂደት የተጀመረው በ95 ዓ.ም. ገደማ ከመጨረሻው ደቀ መዝሙር (ከዮሐንስ) ሞት በኋላ ሲሆን፥ ለብዙ ዓመታትም ቀጥሏል።

የአዲስ ኪዳን ካኖን ውሳኔ በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ የተደረገ ሳይሆን፥ የክርስቲያኖች የጋራ ስምምነት ውጤት ነው። በጣም የቆየው የካኖን ዝርዝር የእስክንድርያው ጳጳስ የሆነው አትናቴዎስ በ387 ዓ.ም. በጻፈው ደብዳቤ ላይ ይገኛል። በደብዳቤው፥ በአሁኑ አዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙትን 27 መጻሕፍት ዘርዝሯል። የካርታጎው ጉባኤ በ397 ዓ.ም. በጉዳዩ ላይ ሳይነጋገር የአትናቴዎስን ዝርዝር አጽድቋል።

በአሁኑ ጊዜ "ቅዱሳት መጻሕፍት" ብለን የምንጠራው ካኖን የተጀመረው በአይሁዳውያን ሲሆን አሁን "ብሉይ ኪዳን" ብለን የምንጠራውን 39 መጻሕፍት ያቀፈ ነው። ዛሬ የካቶሊክ ካኖን 80 መጻሕፍትን (በ1545 በትሬንት ጉባኤ የታከሉትን 14 መጻሕፍት ጨምሮ)፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካኖን 81 መጻሕፍትን፥ የፕሮቴስታንትና የግሪክ ኦርቶዶክስ ካኖን 66 መጻሕፍትን ያጠቃልላል።

## ሥነ-መለኮት በመካከለኛው ዘመን

መካከለኛው ዘመን የሚባለው የተሐድሶ እንቅስቃሴ የጀመረበትና ከ590-1517 ዓ.ም. የነበረው ጊዜ ነው። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከነበረው ብልሹ መንፈሳዊ ሕይወት የተነሣ ከ500-1500 ዓ.ም. የነበረው ጊዜ በአውሮፓ ታሪክ "የጨለማው ዘመን" በመባል ይታወቃል። በማርቲን ሉተር የተመራውን የተሐድሶ እንቅስቃሴ ያቀጣጠለውም ይኸው ችግር ነበር።

የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ በአያሌው እያደገ የመጣው በዚሁ በመካከለኛው ዘመን ነው። ትምህርቶቹም እንደሚከተለው በተከታታይ ተነደፉ። በ593 ዓ.ም. የፐርግቶሪ* ትምህርት፥ በ600 ዓ.ም. በቅዱሳን፥ በማርያምና በመላእክት ስም ጸሎት ማድረግ፥ በ709 ዓ.ም. የሮም ጳጳሱን** እግር መሳም፥ በ995 ዓ.ም. የሙታን ቅዱሳንን ታሪክ በቀኖናት ውስጥ መጨመር፥ በ1079 ዓ.ም. የቀሳውስት ምንኩስና (ድንግልና)፥ በ1090 ዓ.ም. በጸሎት ጊዜ በመቁጠሪያ መድገም፥ በ1215 ዓ.ም. ቅዱስ ቁርባን (የጌታ እራት) በሚወሰድበት ጊዜ ኅብስቱና ወይኑ በቀጥታ ወደ ጌታ ሥጋና ደም ይቀየራል [Transubstantiation/ ትራንሰብስታንሺዬሽን]*** የሚለው እና ለቄስ ንስሐ የመግባት ትምህርት፥ እንዲሁም በ1439 ዓ.ም. የተነደፉት ሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሥርዓቶች ናቸው።

የመካከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያን ብዙ አከራካሪ ጉዳዮች ገጥመዋታል። የምዕራባዊቱ ቤተ ክርስቲያን አንድ ክንዋኔ የሆነውና በአምልኮ ላይ ሥዕላ ሥዕሎችን የመጠቀሙ ልማድ አወዛጋቢ ሆነ። መንፈስ ቅዱስን የሚልክ አብ ነው? ወይስ አብና ወልድ ሁለቱም? የሚለው ጥያቄም የምሥራቁንና የምዕራቡን አብያተ ክርስቲያን ሁለት ላይ ከፈላቸው። የጌታ እራትንም አስመልክቶ የተነሣው ንትርክ ወይንና ኅብስቱ ወደ ጌታ ሥጋና ደምነት ይቀየራል ወደሚለው ትምህርት አመራ። የሥርየት አስተምህሮን በሚመለከትም አወዛጋቢ አመለካከቶች ብቅ ብለው ነበር።

---

* "ፐርግቶሪ" [Purgatory] በሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት መሠረት፥ አማኞች ከሞቱ በኋላ ሙሉ ይቅርታ ስላልተደረገለት ኃጢአታቸው የሚሠቃዩበትና መንግሥተ ሰማይ ለመግባት የሚጠብቁበት ቦታ ነው።

** በዚህ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ የሚገኘውን የማሳሰቢያ ገጽ ይመልከቱ።

*** በዚህ ጉዳይ ላይ በገጽ 43ና 49 ላይ የሚገኘውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

ይህ ዘመን ሃይማኖትን በአመክንዮታዊ መንገድ ለመከላከል የሚያስችል ሊቃዊ አስተሳሰብ እያደገ የመጣበት ነው። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ካቋቋሙት መሪዎች አንዱና ዋናው ቶማስ አኩዊነስ [Thomas Aquinas] በዚህ እንቅስቃሴ የታወቀ ምሁር ሆነ።

የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ከአውግስጢኖሳዊው አስተምህሮ እያፈነገጠች በሄደች መጠን፥ ሌሎች አስተምህሯዊ አመለካከቶች ማቆጥቆጥ ጀመሩ። በዚህም መሠረት ሰው ለደኅንነቱም ሆነ ለቅድስናው በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ተሳትፎ ሊያደርግ ሲጥር ይታይ ጀመር። በመሆኑም በሥራ መጽደቅና መቀደስ የሚለው አመለካከት በተለይ ሰባቱን የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች ከመፈጸም ጋር በመቆራኘት ከፍተኛ ሥፍራ ያዘ። የሮማው ጳጳስ "የክርስቶስ ወኪል" የተባለበትም ይኸው ዘመን ነው። በመሆኑም በሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ለጳጳሱ መገዛት መሠረታዊ ጉዳይ ሆነ።

## ሥነ-መለኮት በዘመነ-ተሐድሶ [Reformation]

በተሐድሶ ዘመን እንቅስቃሴ በዋነኛነት የሚታዩ ብዙ ሰዎች አሉ። ጥቅምት 31 ቀን 1517 ዓ.ም. (እ.አ.አ) ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን በመቃወም በጀርመን አገር ዊተንበርግ በተባለ ሥፍራ ባለች ቤተ ክርስቲያን በራፍ ላይ ማርቲን ሉተር [Martin Luther] የተባለ የቤተ ክርስቲያኒቱ ካህን ዘጠና አምስቱን አንብሮ [theses] በምስማር በመቸንከር የተሐድሶን እንቅስቃሴ ጫረ። ዳግም ልደት በጸጋና በእምነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ነበር ሉተር የተረዳው። ይህ ግንዛቤው ነው በሕይወቱ ሁሉ ያበረታታው። በአማኝ ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን ሊኖረው የሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም የእግዚአብሔር ቃል መሆን እንዳለበት አበክሮ ገልጧል። ይህ ወቅት በተለይ ኤራስመስ የተባለ ሰው ባሳተመው ግሪክኛ አዲስ ኪዳን ሳቢያ ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት መለስ የተባለበት ነበር።

እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስን በሳይንሳዊ መንገድ በመተርጎም ረገድ የታወቀው፥ ፖለቲከኛ፥ ጸሐፊና የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ስዊዘርላንዳዊ የተሐድሶ ሰው ጆን ካልቪን [John Calvin] ብቅ አለ። "የክርስትና ሃይማኖት ድንጋጌዎች" [Institutes of the Christian Religion] የተሰኘውና እጅግ የዳጎሰው መጽሐፉ በፕሮቴስታንት ሥነ-መለኮት ውስጥ ለዓመታት አሻራውን የጣለ ነው። ካልቪን ለእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ከፍተኛ አጽንኦት ይሰጣል። በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ድንጋጌ ወይም ውሳኔ መሠረት እያንዳንዱ ሁኔታ አስቀድሞ ተመድቧል የሚል እምነትም አለው።

የካልቪንን ሥነ-መለኮታዊ አመለካከት በጠቅላላ ይከተል የነበረና ኡልሪክ ዝዊንግሊ [Ulrich Zwingli] የተባለ ሰው፥ አናባፕቲስት [Anabaptist]* የተሰኘ እንቅስቃሴ አቀንቃኝ ሆኖ በመነሣት የጌታ እራት (ቅዱስ ቁርባን)፥ አገልግሎቱ በተለይ ለመታሰቢያነት ብቻ ነው ለሚለው የተከታዮቹ አመለካከት አስተዋጽኦ አድርጓል። ዝዊንግሊ ቅዱሳት መጻሕፍት ያሉትን ብቻ ከመቀበል አኳያ ከሉተርና ከካልቪን በበለጠ ሁኔታ ተሐድሶን አራምዷል።

በዚህ ጊዜ የሥርየት አስተምህሮ ዋና አወዛጋቢ ጉዳይ ይሆን ጀመር። ሉተርና ካልቪን ሥርየትን አስመልክቶ የክርስቶስን የምትክነት ሞት በአፅንኦት ሲያምኑ፥ የዩኒተሪያኒዝም** መንገድ ጠራጊ የሆነው የፋውስተስ ሱስንዮስ [Faustus Socinus]** ግን ተቃወመ። እንደ ሁጎ ግሮቲየስ [Hugo Grotius] እምነት፥ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቃይቶ የሞተው ስለ እኛ ኃጢአት አይደለም። ነገር ግን ሞቱ በግልጥ የሚያመለክተው የኃጢአትን አስከፊ ውጤት፥ እንዲሁም ሰው በኃጢአቱ ሳቢያ ሊደርስበት ይገባው የነበረውን ሥቃይና ቅጣት ነው። የጀኮበስ አርሚኒየስ [Jacobus Arminius] ሥነ-መለኮትም በክርስቶስ ስለ እኛ በምትክ መሞት የሚገኘውን ሥርየት ተቃወመ።

በተሐድሶ ዘመን የጌታ እራት ጉዳይ የመለያያ ነጥብ ሆነ። ሉተራዊው ሥነ-መለኮት በጌታ እራት ሥርዓት ጊዜ በሚወሰደው ኅብስትና ወይን ዙሪያ የጌታ ህልውና ይኖራል የሚል አመለካከት [Consubstantiation/ካንሰብስታንሺዬሽን]*** ነበረው። ካልቪን፥ አማኙ የጌታ እራትን ሲወስድ በኅብስቱና በወይኑ አማካይነት ጸጋ ይተላለፍለታል፥ ለሚለው ትምህርት አጽንኦት ሰጥቶታል። ዝዊንግሊ የተባለው ሰው ግን፥ የጌታ እራት መታሰቢያ ብቻ መሆኑን አስተማረ። እንደ እርሱ እምነት፥ ወይኑና ኅብስቱ ሲወሰድ መታሰቢያ እንጂ የጸጋ መተላለፊያ አይደለም።

አናባፕቲስት የተሰኙት ወገኖች በአማኞች ጥምቀት ላይ የነበራቸውን ከፍተኛ እምነትና፥ ይህንንም ተከትሎ የሕጻናትን ጥምቀት በተመለከተ የነበራቸውን ተቃውሞ በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ላይ በማስረጽ ከፍተኛ ተጽዕኖ አድርገዋል።

---

* በምዕራፍ 5 የቀረበውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

---

** በዚህ ርእስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት አባሪ አንድን ይመልከቱ።

---

***በዚህ ጉዳይ ላይ በገጽ 75 ላይ የሚገኘውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

## ዘመናዊው ሥነ-መለኮት

ዘመናዊው ሥነ-መለኮት በአብርሆት [Enlightment] እና እሱ ባስከተላቸው ውጤቶች ክፉኛ ተጎድቷል። ይህን ያደረገውም ሰውንና አመክንዮን [reason] ማዕከላዊ በማድረግ ነው። የአሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ፈላስፎችና ሥነ-መለኮታውያን ደግሞ ይህንኑ አስተሳሰብ ይበልጥ ገፉበት። አማኑኤል ካንት [Immanuel Kant] የተባለው ፈላስፋ የአመክንዮን አስፈላጊነት ተቀብሎ፥ ከዚያ ውጭ ያለውን ነገር ሁሉ ተቃወመ። ፍሪድሪክ ሽለይርማከር [Friedrich Schleiermacher] የቤተ ክርስቲያንን ድንጋጌዎችና አስተምህሮዎች በመቃወም በሃይማኖት ውስጥ የስሜት ግንዛቤን አስፈላጊነት አጠበቀ። ጆርጅ ሄግል [George Hegel] የተባለ ሌላ ሰው ደግሞ፥ ሃይማኖት የሁለት ተቃራኒ አመለካከቶች አዝጋሚና የማያቋርጥ ሂደት ውጤት እንደሆነ አድርጎ ተመለከተው። በተለይ እነዚህ ስማቸው ከላይ የተጠቀሰ ሦስት ሰዎች የአመለካከት አሻራቸውን በዘመናዊው ሥነ-መለኮት ላይ ጥለው አልፈዋል። በዘመናዊው ሥነ-መለኮት ጉያ የሰው አመክንዮ፥ ልዕለ-ተፈጥሮን [supernatural] የመቃወምና መጽሐፍ ቅዱስን ስሕተት እንዳለው የመቁጠር አስተሳሰብ ይገኛል።

በለዘብተኛ ሥነ-መለኮታዊ አስተሳሰብ የሰለጠነው ካርል ባርት [Karl Barth]፥ ምንም እንኳ ወደ ወግ አጥባቂነት ሥነ-መለኮታዊ አስተሳሰብ ባይመለስ፥ በ1919 ዓ.ም. ባስነሣው ተቃውሞ ሳቢያ ዘመናዊው ሥነ-መለኮት አዲስ አቅጣጫ ያዘ። በዚህ ላይ በመመሥረትም "አዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት ትምህርት" [Neo-Orthodoxy/ኒዮ-ኦርቶዶክሲ]* የተሰኘው የአመለካከት ዘርፍ ተፈጠረ። ይህ ትምህርት በሰው ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔርን መለኮታዊነት በቅርብ ማየትንና ከእርሱ ጋር መገናኘትን መለማመድ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አጉልቶ አሳይቷል። "አዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት" ሥነ-መለኮታውያን፥ በአብዛኛው በአመለካከት ቢለያዩም፥ ሁሉም መጽሐፍ ቅዱስ እስትንፋሰ-መለኮት እንደሆነ አያምኑም። ብዙዎች የክርስቶስን የሥጋ ትንሣኤ ታሪካዊ እውነትነት ይክዳሉ። መጽሐፍ ቅዱስንም እንደ ተረት እንጂ እንደ ታሪካዊነቱ አይቀበሉትም። የዘመናዊው ሥነ-መለኮት ብዙ አስተሳሰቦች ከለዘብተኛነትና ከአዲሱ ቀጥተኛ ሃይማኖት ሥነ-መለኮት የመነጩ ናቸው።

* በዚህ ርእስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ምዕራፍ 5ና አባሪ አንድን ይመልከቱ።

# - 2 -

# ጥንታዊ ሥነ-መለኮት

የአስተምህሮ ክርስትና ታሪክ ጥናት ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጥናት ጋር ተመሳሳይ ነው። ይሁን እንጂ፥ የሥነ-መለኮት ታሪክ አስተምህሮዎች በዘመናት ላሳዩት እድገት አጽንኦት ሲሰጡ፥ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ደግሞ በአብዛኛው ከአስተምህሮ ክርስትና ጉዳዮች ውጪ ከቤተ ክርስቲያን እድገት ጋር በተያያዘ መልኩ ባሉ ጉዳዮች ላይ ያተኩራል።

## ሐዋርያት አባቶች

ከሐዋርያት አባቶች የሚተላለፉ ጽሑፎች አስፈላጊና ጠቃሚ ናቸው። ይህ የሆነበት ምክንያት፥ እነዚያ ሰዎች የአዲስ ኪዳን ሐዋርያት በኖሩበት ዘመን የኖሩ በመሆናቸው ነው። የሐዋርያት አባቶች ጽሑፎች የሚከተሉት ናቸው:- በ97 ዓ.ም. "የመጀመሪያው የሮማው ቀሌምንጦስ [Clement] መልእክት ለቆሮንቶስ ሰዎች"፤ በ150 ዓ.ም. ገደማ በማን እንደተጻፈ ያልታወቀው ስብከት መሰሉ "የቀሌምንጦስ ሁለተኛ መልእክት"፤ በ110 ዓ.ም. ለኤፌሶናውያን፥ ለማግኔዝያን፥ ለትራሊያን፥ ለሮማውያን፥ ለፊላደልፊያውያን፥ ለስምረኔውያውያን፥ ለፖሊካርፕ [Polycarp] እና ለስምረኔው ፓትሪያርክ የተጻፉት "የኢግናትየስ [Ignatius] (የአንጾኪያው ጳጳስ) መልእክቶች"፤ በ100 ዓ.ም. የተጻፈው "የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ትምህርት" ['Didache'/'ዲዳኬ']* የተሰኘው፤ ከ70-132 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ የተጻፈው "የባርናባስ መልእክት"፤ "የሄርሚሱ እረኛ" የተሰኘውና ከ140-145 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ የተጻፈው፤ በ125 ዓ.ም. ገደማ የተጻፉት "የፓፒየስ [Papias] (የሂሪያፖሊስ [Hieropolis] ጳጳስ) ቁርጥራጭ ጽሑፎች"።

የሐዋርያትን ጽሑፎች በምናጠናበት ጊዜ፥ ከአዲስ ኪዳን ጽሑፎች ጋር አያሌ የዓይነት ልዩነቶች እናይባቸዋለን። በውስጣቸውም ጥቂት አዲስ ነገሮች አሉ። ከሁሉም ይልቅ ጽሑፎቹ ውስጥ ሆን ተብሎ ከአስተምህሮ ጉዳዮች ይልቅ ሥነ-ምግባራዊ ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩሩ ተደርገዋል። ሆኖም እነዚህ ጽሑፎች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን አሰባሰብ

---

* 'ዲዳኬ' በግሪክኛ "ትምህርት" ማለት ሲሆን፥ በ1ኛው ወይም በ2ኛው ክፍለ ዘመን ለተጻፈ አንድ ጽሑፍ መጠሪያም ያገለግላል። ይህ ጽሑፍ በ1873 ዓ.ም. በቁስጥንጥንያ ከሚገኝ አንድ የቤተ ክርስቲያን ቤተ መጻሕፍት የተገኘ ነው። ጽሑፉ "የአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ትምህርቶች" በመባል የሚታወቅም ሲሆን፥ የቀድሞ ቤተ ክርስቲያንን ልምድና ትምህርት ያብራራል።

ትክክለኛነትና ተአማኒነት እንዲሁም አንድነት ለማረጋገጥ ጠቅመዋል። ከዚህም ሌላ በሁለተኛው ምዕተ ዓመት ብቅ ባሉት የእምነት ዐቃቢያን፥ የይሁንታ ጽሑፎችና የአዲስ ኪዳን ጽሑፎች መካከል አስተምህሯዊ ግንኙነቶች ይፈጥራሉ።

## የሐዋርያት አባቶች ትምህርተ ቅዱሳት መጻሕፍት

ጽሑፎቻቸውን ከቅዱሳት መጻሕፍት ጽሑፎች ጋር ማዋሀድና ማዛመድ የሐዋርያት አባቶች የጋራ ባሕርይ ነበር። ከብሉይ ኪዳንና ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ረጃጅም ክፍሎች እንኳን ሳይቀሩ እንደ ሰምና ወርቅ እያዛመዱ በጽሑፎቻቸው ይጠቅሳሉ።

የቅዱሳት መጻሕፍትን ሥልጣንም ከግምት ያስገባሉ። ቀሌምንጦስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቶቹ "መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል" እያለ ከኃጢአት ስለመጠበቅ ያስጠነቅቃል። የቅዱሳት መጻሕፍትን እውነተኛነትና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የተሰጡ መሆናቸውንም በዚሁ መልእክቱ ሲያረጋግጥ፥ በዚሁ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ "አንድም ከጽድቅ የራቀና ሐሰት ነገር የለም" በማለት ጽፏል። ስለ ብሉይ ኪዳንም "ቅዱሳት ጽሑፎች"፥ "የእግዚአብሔር ንግግሮች" በማለት ጠቅሷል።

የሐዋርያት አባቶች የቅዱሳት መጻሕፍት አተረጓጎም፥ በአብዛኛው በቀጥታ ሳይሆን በምሳሌያዊ ገለጣ ወይም በተለዋጭ ዘይቤ ነው። የብሉይ ኪዳንንም ክፍል ሲያጣቅሱ "አንቺ ያልወለድሽ መካን ሆይ ዘምሪ" (ኢሳይያስ 54፡1) የሚለውን "ቤተ ክርስቲያን ልጆችን ከማግኘቷ በፊት መካን ነበረች" በማለት ይተረጉሙታል። ሌላው ምሳሌ "የሄርሚሱ እረኛ"፤ የተሰኘው መልእክት ነው። አግናጢዮስ ትራሊያናውያንን በጽሑፉ ሲያበረታታቸውና ሲያነቃቃቸው ደግሞ፥ "የጌታ ሥጋ በሆነው እምነትና የክርስቶስ ኢየሱስ ደም በሆነው ፍቅር እራሳችሁን አድሱ" ብሏል።

## የሐዋርያት አባቶች ትምህርተ እግዚአብሔር

በሥላሴዎች የማመኑ ጉዳይ የጸና ነው፤ ቀሌምንጦስ የሥላሴን እኩልነት ሲገልጥ፦ "እግዚአብሔር አብ ሕያው እንደሆነ፥ ጌታ ኢየሱስም ሕያው ነው፥ መንፈስ ቅዱስም እንዲሁ፤ እነርሱም የምርጦቹ እምነትና ተስፋ ናቸው፤ የአጥናፈ ዓለሙ ፈጣሪና ጌታ፥ እግዚአብሔር ነው" ብሏል።

## የሐዋርያት አባቶች ትምህርተ ክርስቶስ

ስለ ክርስቶስ ያሉ እውነቶች የሚደነቁና የጸኑ ናቸው። አግናጢዮስ የክርስቶስን መለኮትነት አስመልክቶ ታላቅ ቁም ነገሮችን ተናግሯል። ወደ

ሮምና ወደ ኤፌሶን በጻፋቸው ደብዳቤዎቹ፥ "ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛ አምላክ" ብሏል። በአማኞች ስለማደሩ ደግሞ "እርሱ ራሱ እንደ አምላካችን በእኛ ውስጥ ይኖር ዘንድ" ካለ በኋላ፥ ክርስቶስ "የአብ አሳብ"፥ "የእግዚአብሔር ጥበብ" እንደሆነ፥ "ዓለም ሳይፈጠር በፊት ከአብ ጋር እንደነበር" እንዲሁም "ወልድነቱን" ገልጧል። ፓሊካርፕ የተባለው ሌላ ጸሐፊ ደግሞ፥ "ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛ አምላክና ጌታ" ብሏል። ቀሌምንጦስም እንዲሁ "ኢየሱስ ከአብ የተላከ" መሆኑን ገልጧል። የኢየሱስ ሰብእና በሐዋርያው ዮሐንስ ጽሑፍ ተረጋግጧል። ትንሣኤውም እንደዚሁ በቀሌምንጦስና በአግናጢዮስ ተደጋግሞ ተጠቅሷል። ቀሌምንጦስና ፓሊካርፕ የክርስቶስን ሊቀ ክህነትና ከመላእክት መላቅ ጠቅሰዋል።

## *የሐዋርያት አባቶች ትምህርተ ድኅነት*

ሐዋርያት አባቶች፥ የደኅንነት መገኛ የክርስቶስ ደም መሆኑን በመደጋገም ገልጠዋል። ቀሌምንጦስ እንዲህ ብሏል፡- "ዓይኖቻችንን በክርስቶስ ደም ላይ እናድርግ። ለእኛ ደኅንነት በመፍሰሱና ለዓለም ሁሉ የንስሐን ጸጋ በማስገኘቱ ይህ ደም ለአብ ምን ያህል ውድ እንደሆነም እንገንዘብ።" የቀሌምንጦስ መግለጫ የክርስቶስ መሥዋዕትነት ለተወሰኑት ሰዎች ብቻ እንዳልሆነ ይጠቁማል። ንሰሐ መግባትንም አፅንኦት አድርጎበታል። አግናጢዎስም እንዲሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ማመን ደኅንነት እንደሚያስገኝ ገልጧል።

ያም ቢሆን ለደኅንነት፥ ሥራም እንደሚያስፈልግ ተተኩሮበታል። ቀሌምንጦስ በዚህ ጉዳይ ላይ ባለው አቋሙ፥ የሎጥንና የረዓብን መዳን እንግዳ ከመቀበል ተግባራቸው ጋር አያይዞታል። በትምህርቱ መሠረት ደኅንነት የጌታን ትእዛዝ በጥንቃቄ ከመጠበቅ፥ ሥጋንም ከማጥራት እና የአብን ፈቃድ ከማድረግ ጋር የተቆራኘ ነው። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት፤ ፍቅር፥ ዓለማዊ ደስታን መሰናበትና ክፉ ምኞትንም መቃወም ያስፈልጋል፤ ጽድቅንም መለማመድ ዓቢይ ጉዳይ ነው።

እነዚህ መግለጫዎች እጅግ የሚበረታቱና ፈሪሀ እግዚአብሔርን የሚያስተምሩ ናቸው። ቢሆንም ከደኅንነት መልእክት ጋር ያለውን ነፃ የእግዚአብሔር ጸጋ የመቀነስና በወጉ ያለመግለጥ ሁኔታ ይታይባቸዋል። በክርስቲያናዊው አስተሳሰብ የመጀመሪያ አካባቢ ብቅ ካሉ አስተምህሯዊ ግድፈቶች አንዱ ነገር ይህ ነው።

---

* በዚህ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ የሚገኘውን የማሳሰቢያ ገጽ ይመልከቱ።

## የሐዋርያት አባቶች ትምህርተ ቤተ ክርስቲያን

የሐዋርያት አባቶች ዘመን የዲያቆናት፥ የሽማግሌዎች እንዲሁም የጳጳሳት* የሥራ ድርሻና ሥልጣን በግልጥ የዳበሩበት ነበር። የአማኞችን ለሽማግሌዎችና ለጳጳሶች ሥልጣን የመገዛት ጉዳይ ሐዋርያት አባቶች በጥብቅ አተኩረውበታል። ቀሌምንጦስ፥ አማኞች ከሽማግሌዎች ጋር በሰላም እንዲሆኑ፥ ለሥልጣናቸውም እንዲገዙ፥ ቅጣትንም እንዲቀበሉ በጥብቅ አሳስቧል። አግናጢዎስ፥ አንድ አማኝ ለጳጳሳት የሚያደርገውን መታዘዝ፥ ክርስቶስ ለአብ፥ ሐዋርያትም ለክርስቶስ ካሳዩት መታዘዝ ጋር ያመሳስለዋል። እነዚህ ጸሐፊዎች፥ መሪዎች ትልቅ ክብር ይገባቸዋል ይላሉ። አግናጢዎስ፥ "ያለ ጳጳስ አንዳች ነገር አታድርጉ፥ ሐዋርያት ለክርስቶስ እንደታዘዙ ለሽማግሌዎች ታዘዙ... ሰዎች ሁሉ ዲያቆናትን እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ ያክብሯቸው፥ ጳጳሱ የአብ ምሳሌ ሆኖ እንደሚከበር፥ ሽማግሌዎችም የእግዚአብሔር ጉባኤ ናቸው። ከእግዚአብሔር አብና ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያሉ ሁሉ ከጳጳሱ ጋር አሉ" ብሏል። በመቀጠልም "ኢየሱስ ክርስቶስ አብን እንደተከተለ ሁሉ፥ ጳጳሳችሁን ለመከተል ሁሉን ነገር አድርጉ። ሽማግሌዎችንም ልክ እንደ ሐዋርያት ተከተሏቸው፤ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነውና ዲያቆናትንም አክብሩ... ክርስቶስ በሚገኝበት ሁሉ ዓለም አቀፉ ቤተ ክርስቲያን እንደምትገኝ፥ ጳጳሱ በሚገኝበት ሕዝቡ ሁሉ ይገኝ" ብሏል።

እያደገ የመጣው የጳጳሱ ሥልጣን በአግናጢዎስ መግለጫ ላይ ቁልጭ ብሎ ይታያል።

> "ማንም ቢሆን፥ ቤተ ክርስቲያንን አስመልክቶ በምንም ዓይነት መልኩ ያለ ጳጳስ አንዳች ነገር እንዳያደርግ። ሥጋወደሙ መቀበልና መስጠትም ተገቢ የሚሆነው፥ በጳጳሱና ጳጳሱ በወከለው በኩል ሲሆን ብቻ ነው። ጳጳሱ በሌለበት የፍቅር ማዕድ ማዘጋጀትም ሆነ የጥምቀት ሥርዓት መፈጸም ሕገ ወጥነት ነው። ጳጳሱ ያጸደቀው ሁሉ ግን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ይሆናል። እርግጠኛነትና ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ የምታደርጉትን ነገር ሁሉ ጳጳሱ ይወቀው። እግዚአብሔርንና ጳጳሱን ማክበር መልካም ነው። ጳጳሱን የሚያከብር በእግዚአብሔር የተከበረ ነው።"

የጌታ እራትም (ቅዱስ ቁርባን) "የሞት ማርከሻና ከክርስቶስ ጋር ለዘላለም እንድንኖር የሚያደርገን ነው" ተብሎ ይጠቀስም ነበር። 'ዲዳኬ' ['Didache'] የተሰኘው ትምህርትም፥ ከጌታ እራት በፊትም ሆነ በኋላ ስለሚደረገው ጸሎት፥ እንዲሁም ጥምቀትንና ጾምን አስመልክቶ መመሪያ ይሰጣል።

### የሐዋርያት አባቶች ትምህርተ ፍጻሜ-ዘመን

የፍጻሜ ዘመንን በተመለከተ ብዙ መረጃዎች የሉም። ሁለተኛው መልእክተ ቀሌምንጦስ የእግዚአብሔር መንግሥት ከእግዚአብሔር መገለጥ ጋር እንደሚመጣና፤ የዚህ ዓለም መንግሥት በክርስቶስ ሲተካ፥ ሕዝቦች ሁሉ እንደሚደነቁ ይጠቅሳል። በእግዚአብሔር መንግሥትና በዘላለም ሕይወት መካከል ልዩነት እንዳለም ተጠቅሷል፥ አማኞች ለተጋድሎና ለጽናታቸው አክሊልን የሚቀዳጁት በዚሁ መንግሥት ጊዜ መሆኑን ጠቅሶ፥ ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌለው ኑሮ የኖሩ ሁሉ በክርስቶስ መገለጥ ጊዜ ይፈረድባቸውና በማይጠፋ እሳት የሚቃጠሉ መሆናቸውን ገልጧል።

ባርናባስም [Barnabas] የኢየሱስ ክርስቶስን ምጽአት እይቀሬነት መሠረት በማድረግ አማኞችን አበረታቷቸዋል። ፓፒየስ የተባለው ጸሐፊም የሺህ ዓመቱን መንግሥት ትምህርት የሚቀበል መሆኑን ቀጥሎ ባለው መግለጫው አረጋግጧል፡-

> "በትንቢት የተነገረው በረከት የሚከናወነው ያለጥርጥር በዚሁ መንግሥት ዘመን ነው። ጻድቅ ከመቃብር ተነሥቶ ሲነግሥ፥ ተፈጥሮ ከእሥራት ሲፈታና ነፃ ሲሆን፥ ምድር ከሰማይ ጠልና ከሰባው አፈር ብዙ የምግብ በረከት ታፈራለች። ጌታ ይህን ዘመን አስመልክቶ ያስተምር የነበረው "ወይን የሚያፈራበት፥ አንዱ እግር አሥር ሺህ ግንድ፥ አንዱ ግንድ ከአሥር ሺህ ቅርንጫፍ፥ በእያንዳንዱ ቅርንጫፍ ላይ አሥር ሺህ ቀንበጥ፥ በእያንዳንዱም ቀንበጥ ላይ አሥር ሺህ ተቀጥላ፥ በእያንዳንዱም ተቀጥላ ላይ አሥር ሺህ የወይን ፍሬ፥ አንዱ ፍሬ ሲጨመቅ ብዙ የወይን ጠጅ ይወጣዋል። ይህን የምድር ፍሬ ውጤት የሚመገቡ እንስሳት በሰላምና በአንድ ላይ ከመኖራቸውም በላይ፥ ሙሉ በሙሉ ለሰው ልጅ የሚገዙ ይሆናሉ።"

## የጥንት አቃቢያነ-እምነት

ክርስትናን ባለመገንዘብ ከተፈጠረው ማጥላላትና ስም ማጥፋት የተነሣ፥ ከአሕዛብ ወገን የሆኑ ታዋቂ ክርስቲያኖች ለክርስትና ጥብቅና በመቆም አቃቤ እምነታዊ ጽሑፎችን ጽፈዋል። እነዚህ ቀደምት ክርስቲያን ጸሐፊዎች "የእምነት አቃቤያን" (የእምነት ጠባቂዎች) [Apologists] በመባል ይታወቃሉ። ሥራቸውም በሦስት ነገር ላይ ያተኮረ ነበር። (1) የክርስትና እምነትን ከኢ-አማኒያን ሐሰተኛ ሙግት፥ በላኤሰብነትን [cannibalism]፥ በሥጋ ዘመዳሞች መካከል የሚደረግን የግብረ ሥጋ ግንኙነትን፥

ስንፍናን እና ፀረ-ማሕበረሰባዊነት ከመሳሰሉ ክሶች ተከላክለዋል። (2) አይሁዳውያን ብሉይ ኪዳን፥ በአምሳያና ሊመጣ ባለ ነገር መልክ እያደረገ ስለ ክርስቶስ የሚናገረውን የተረዱት በስሕተት እንደሆነ በማስገንዘብ፥ ጣኦት አምልኮን፥ የአምልኮውን ድርጊትና የጣኦታቱን ምግባረ ብልሹነት እግዚአብሔር ራሱን ከገለጠበት አዲስ ኪዳን ጋር እያነጻጸሩ ይቃወሙ ነበር። (3) የትንቢቶችን ፍጻሜና፥ እውነትነቱ በተአምራት የተረጋገጠውን የአዲስ ኪዳን መገለጥ ደግፈው በመከራከር ተገቢ ድርሻቸውን ተወጥተዋል።

ዋና ዋናዎቹ የእምነት አቃቢያንና ጽሑፎቻቸው የሚከተሉት ናቸው፦ በ150 ዓ.ም. ባልታወቀ ሰው ለዲዮጊተስ [Diognetus] የተጻፈው መልእክት፥ በ125 ዓ.ም. ለንጉሥ ሐድሪያን [Hadrian] የተጻፈውና፥ አሁን የጠፋው የአቴንሱ ጳጳስ የቆድራቶስ [Quadratus] አቃቤ እምነታዊ ጽሑፍ፥ ወይ ለሐድሪያን ወይ ለአንጦኒዮስ ፒዮስ [Antonius Pius] በአቴናዊው ፈላስፋ በአርስታይድስ [Aristides] የተጻፈው፥ ሜሊቶ [Melito] የተባለው የሰርዴስ ጳጳስ ለማርቆስ አውሬሊዮስ [Marcus Aurelius] የጻፈው አቃቤ እምነታዊ መልእክት፥ ለዚሁ ሰው በሂሪያፖሊሱ ጳጳስ ቀላውዴዎስ አቡሊናርዮስ [Claudius Apollinarius] የተጻፈው መልእክት፥ ሚልቲያደስ [Miltiades] የተባለ አቴናዊ ፈላስፋ አይሁዶችንም አሕዛብንም በመቃወም የጻፈው፥ በ177 ዓ.ም. ገደማ አቴናጎራስ [Athenagoras] የተባለው ሰው ማርቆስ አውሬሊዮስን ተቃውሞ፥ ኢ-አማኒነት፥ በላኤሰብነትና ምግባረ ብልሹነት በክርስትና ላይ የሚያነሡትን ተቃውሞ በማውገዝ የጻፈው አቃቤ እምነታዊ ጽሑፍ። የአንጾኪያው ቴዎፍሎስም [Theophilus] በእግዚአብሔር ስለማመንና ስለትንሣኤው ተስፋ፥ እንዲሁም አረመኔያዊነትን በማውገዝ ጽሑፎቻቸውም ከብሉይ ኪዳን ጋር ሲነጻጸሩ መናኛ እንደሆኑ በመግለጥ ሦስት ጽሑፎችን አዘጋጅቷል። አሶራዊው ታቲያንም [Tatian] የክርስትናን ተገቢነት [reasonableness] "ከባዕድ አምልኮ ከንቱነት" ጋር በማነጻጸር ተከላከሏል። ከእምነት አቃቢያን እጅግ ታላቅ እንደሆነ የሚገመተው ጁስቲን ማርቲር [Justin Martyr] ፥ ሁለት አቃቤ እምነታዊ ጽሑፎችን ከማዘጋጀቱም በላይ ከአይሁዳዊው ትራይፎ [Trypho] ጋርም ተወዛግቧል። ይህ ሰው ቀደም ሲል ፈላስፋ ስለነበር አማኝ ከሆነ በኋላ የፍልስፍና እውቀቱን ለክርስትና መከላከያነት ተጠቅሞበታል።

## የአቃቤ እምነታዊያን ትምህርተ ቅዱሳት መጻሕፍት

ዲዮጊተስ ለተባለው ሰው የተጻፈ አንድ መልእክት ከእግዚአብሔር ስለሚመጣ መገለጥ አበክሮ ገልጧል። የአጥናፈ ዓለሙ ጌታ ራሱን ለሰው የገለጠበት ሁኔታም እንዲህ ተብራርቷል፦ "የማይታየው አምላክ ራሱ

ከሰው ልጅ አስተሳሰብ በላይ የሆነው እውነቱንና ቅዱስ ትምህርቱን ከሰማያት በሰው ልጆች ልብ ተክሎታል።” ይህ አባባል እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጠውን መገለጥ ከፈላስፎች መላምታዊ ግምት ጋር ያነጻጽራል። መልእክቱ የሚያስረዳው፥ እግዚአብሔር ራሱን በቃሉ (በክርስቶስ ማለት ነው)፥ የገለጠ መሆኑን ነው። ፍልስፍናዊ ስያሜው በግሪክኛ ‘ሎጎስ’ ማለት ሲሆን፥ ትርጉሙም ቃል ወይም ንግግር ማለት ነው። ስለሆነም ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ለሰው ልጅ የተላከ ቃል ነው። በዚህ መልኩ በተለይ የእምነት አቃቢያኑ፥ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን መገለጥ ለሰው ልጆች ያስተላለፈ መምህር ነው በማለት አበክረው አስገንዝበዋል። በመሆኑም አንባቢያን፥ በደብዳቤው ላይ የተጠቀሰውን መልእክት ክርስቶስ ከአንደበቱ ያወጣው እንደሆነ አድርገው እንዲገነዘቡት አጥብቆ ያሳስባል።

## *የእቃቤ እምነታውያን ትምህርተ እግዚአብሔር*

ወደ ዲዮጊነስ የተላከውን መልእክት የጻፈው ሰው፥ የእንጨትና የድንጋይ አማልክትን ከንቱነት በሰፊው ገልጧል። ይህ ጸሐፊ እነዚህ የድንጋይ አማልክት፥ ሰዎች በኀዳና የሚራመዱባቸው ከመሰሉ ድንጋዮች የተሠሩ፥ በሰባሽና ፈራሽ መሆናቸውንም ለአንባቢዎቹ አስገንዝቧል። እንዲያውም ከወርቅና ከብር የሚሠሩ አማልክት በጨለማ እንዳይሰረቁ ይቆለፍባቸዋል ይላል። እግዚአብሔርን ግን፥ “የማይታይ፥ ኃያልና የዓለማት፥ የአጥናፈ ዓለሙ ፈጣሪና ጌታ፥ ሁሉን የሠራ፥ በሥርዓትም ያቀናበረ ነው” ብሏል። ጁስቲን ማርቲር የተባለው የሥነ-መለኮት ሰውም ይህን አምላክ፥ “ከሁሉ የላቀ እውነተኛ አምላክ፥ የጽድቅ፥ የይቅርታና የበጎ ነገሮች ሁሉ አባት፥ ኃጢአትም ያልነካው ነው” ብሎታል።

እግዚአብሔር እራሱን ከመግለጡ በፊት አምላክ ምን እንደሚመስል ሰዎች አያውቁም ነበር። አሁን ግን “ደግ፥ መልካም፥ ሩህሩህ፥ እውነተኛና እርሱ ብቻ መልካም እንደሆነ” ያውቃሉ። የሰው ልጅ ሞትና ፍርድ የተገባው ሆኖ ሳለ፥ እግዚአብሔር ምሕረቱ የበዛ በመሆኑ የሰዎችን የኃጢአት ዋጋ ይከፍል ዘንድ ልጁን ላከ። በዚህም እግዚአብሔር የፍቅር አምላክነቱን ገልጧል። ዮሐንስ 3፡16 ውስጥ የተጠቀሱት ቃላት ይህንኑ ያስገነዝባሉ።

አቴናጎራስ የተባለው የሃይማኖት አባት፥ ስለ እግዚአብሔር አንድነትና ስለ ሥላሴ ግልጥ አሳብ በማቅረብ ሲያስገነዝብ፡- “እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው፥ አልተፈጠረም፥ ዘላለማዊ ነው፥ የማይታይ፥ የማይወሰን እና ከሰዎች እውቀት በላይ ነው። እርሱን መረዳት

የሚቻለው በአእምሮና ከእርሱ በሚሰጥ ጥበብ ብቻ ሲሆን፥ በውበት፥ በመንፈስና አንደበት ሊገልጥ በማይቻል ኃይል ተከቧል። አጥናፈ ዓለሙ በእርሱ ቃል ተፈጥሯል፤ በአንድነትና በሥርዓትም ሆኗል።" ስለ መንፈስ ቅዱስም እንዲህ በማለት ይጠቅሳል፦ "ከአምላክ የሚመነጭና እንደ ፀሐይ ጨረር ተመልሶ ወደ እርሱ የሚሄድ ነው።" ጄስቲን ማርቲር፥ ስለ ሥላሴ ሲናገር ወልድ ሁለተኛውን ደረጃ ሲይዝ፥ የትንቢት መንፈስ ደግሞ ሦስተኛውን ሥፍራ ይይዛል በማለት ለየት ያለ መግለጫ ሰጥቷል።

## የአቃቤ እምነታውያን ትምህርተ ክርስቶስ

ቃል የሆነው ክርስቶስ በራሱ ሕዝብ ተቀባይነት እንዲያጣና በአሕዛብ ይታመንበት ዘንድ ከእግዚአብሔር ተላከ። ዘላለማዊነቱም በዚህ ጽሑፍ ውስጥ፥ "ከመጀመሪያው የነበረ ቃል. . .ዘላለማዊው" ተብሎ ተጠቅሷል። አቴናጎራስም ክርስቶስን "የአብ የመጀመሪያ ፍሬ" ቢለውም ወልድ የተፈጠረ ነው የሚለውን አይቀበልም። እንዲህም ይላል፦ "እግዚአብሔር ዘላለማዊ አሳብ እንደመሆኑ መጠን፥ ቃሉም ቢሆን ከመጀመሪያው በእርሱ ውስጥ በዘላለማዊ ጥበብ የነበረ ነው።" ከዚህ ሌላ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ፥ ደግሞም፥ "በአሳብና በግብር ቃል የሆነ. . . የእግዚአብሔር ልጅ የአብ ልብና ቃል ነው" ብሏል።

ክርስቶስም በሥራው፥ "ለእኛ የተከፈለ ዋጋ፥ ለሕገ ወጦቹ ቅድስና፥ ለክፉ አድራጊዎች ንጽሕና፥ ለጽድቅ የለሾቹ ጽድቅ፥ ለምግባረ ብልሹዎች መልካም ምግባር፥ ለሟቾች ሕይወት ሰጪ" ሆኖ ቀርቧል። ዳዮግኒተስ የተባለው ጸሐፊም፥ "በአንድ ጻድቅ በኩል ሕዝቦች ይጸድቃሉ" ብሏል። እዚህ ላይ የሮሜ 5 እና የ1ኛ ጴጥሮስ 3፡18 ቋንቋ በግልጥ ይታወሳሉ።

## የአቃቤ እምነታውያን ትምህርተ ቤተ ክርስቲያን

ጄስቲን ማርቲር፥ ኢሳይያስ 1፡16-20 ላይ ያለው ጥቅስ ስለ ክርስቲያን ጥምቀት ይናገራል ከማለቱም ሌላ፥ ይህ ሥርዓት አዲስ ልደትን ያስከትላል ይላል። የጌታ እራትን መውሰድ ያለባቸው አማኞች ብቻ መሆናቸውን ሲገልጥም፥ "በጸሎት የተቀደሰው ምግብ (ማለትም ኅብስቱና ወይኑ)፥ የሥጋ ለባሹ የኢየሱስ ሥጋና ደም ነው፤ በኅብስቱና በወይኑ መለወጥ ምክንያት፥ ሰውነታችን ሳያቋርጥ መንፈሳዊ ምግብን ይመገባል ብሏል።" የጌታ እራት በሚወሰድበት ጊዜ አማኙ የሚቀበለው በቀጥታ

የክርስቶስን ሥጋና ደም ነው፥ የሚለው የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ እዚህ ላይ ይታያል።

# ጥንታዊ ኑፋቄዎች

## ከሙሴ ሕግ ጋር የተያያዙት

ክርስትናን የተቀበሉ አይሁዳውያን ከሙሴ ሕግ ጋር ሙጥኝ ማለታቸው የማይቀር መሆኑ ግልጥ ነው። ይህ ችግር በአዲስ ኪዳኑ ጴጥሮስ ጠባይ ላይ እንኳ የታየ ሲሆን፥ ቤተ ክርስቲያንን የገጠማት መሆኑም በሐዋርያት ሥራ 15 ላይ ተገልጧል። በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥ ለደኅንነት የሙሴ ሕግጋትን መከተል አስፈላጊ ነው የሚሉ የአይሁድ-ክርስቲያን ሀራጥቃዎች ነበሩ። ናዝራዊ [Nazarenes] የሚባሉት አይሁድ ክርስቲያኖች የሙሴን ሕግ በጥብቅ ይፈጽሙ፥ ሰንበትን ያከብሩ፥ ግርዛትንና የምግብ ሕግጋትን ይከተሉ ነበር። ይሁን እንጂ ሕግጋታቸውን በአሕዛብ ላይ አልጫኑም። የክርስቶስን መለኮትነትና ከድንግል መወለድ ተቀብለዋል። ትምህርቱም ከሙሴና ከነቢያት የበለጠ እንደሆነ ያምናሉ። ናዝራዊ ክርስቲያኖች በዕብራይስጥ በተጻፈው የማቴዎስ ወንጌል ብቻ ይጠቀሙ የነበረ ቢሆንም፥ የጳውሎስን ሐዋርያነትም ተቀብለዋል። ኢቢዮናውያን [Ebionites]* ደግሞ፥ የክርስቶስን ከድንግል መወለድም ሆነ መለኮትነት ይክዱና ሰው የሆነ የማርያምና የዮሴፍ የሥጋ ልጅ ነው ይሉት ነበር። ከነቢይነት ያለፈ እንዳልሆነ ቆጠሩት። የጳውሎስን ሐዋርያነትም አልተቀበሉም፤ ከሕግ ያፈነገጠ ከሀዲ ነው አሉት። ኤልቄሳውያን [Elkesaites] የሚባሉት ክፍሎች ደግሞ፥ ኤልቄሳኢ ለተባለ ሰው መልአክ ተገልጦ በሰጠው መጽሐፍ፥ ኢየሱስ ሰብአዊ ከሆኑ ወላጆች የተወለደ መልአክ ነው ብሎ ነግሮታል ብለው አስተማሩ። ከድንግል ማርያም መወለዱን በመካድም የመላእክት አለቃ ነው ብለው አመኑ። ሕግ መፈጸም ያለበት መሆኑን በማመን፥ ሰንበት መከበር ያለበት መሆኑንና የግርዘትን አስፈላጊነት አስተምረዋል። የቈላስይስ መልእክትና አንደኛ ጢሞቴዎስ የሚጠቅሱት ምናልባት ይህን ኑፋቄ ይሆናል።

## ከኖስቲክ [Gnostic] ፍልስፍና ጋር የተያያዙ

“ኖስቲካዊነት” የሚለው ስያሜ የተገኘው፥ ‘ግኖሲስ’ ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን፥ ትርጉሙም “እውቀት” ማለት ነው። የሚያመለክተውም የኑፋቄውን ባሕርይ ነው። ኖስቲካዊነት በግሪኮች

---

* በዚህ ርእስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት አባሪ አንድን ይመልከቱ።

አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ የፍልስፍና ሥርዓት ሲሆን፥ በዚህ ፍልስፍና መሠረት፥ ቁስ አካል እርኩስ (ክፉ) ሲሆን፥ መንፈስ ደግሞ መልካም (ጥሩ) ነው። እንዲህ ከሆነ፥ ይህን ክፉ ቁስአካላዊ ዓለም እግዚአብሔር ሊፈጥረው አይችልም። በዚህ የፍልስፍና ሥርዓት መሠረት፥ ኖስቲካውያን፥ አማልክት እንደ ሰንሰለት የተያያዙና ተከታታይ የሆኑ እንዲሁም በመካከላቸው የሥልጣን ተዋረድ ያላቸው ናቸው ብለው ያምናሉ። ከአማልክት ሁሉ የሚበልጠው ደግሞ ፍፁም መንፈስ ነበር። እንዲሁም እርሱ "ብርሃን"፥ "ከሁሉ በላይ" እና "የሁሉ አባት" ተብሎ ይጠራ ነበር። ከእርሱ በታችና በዙሪያውም 'ኤየንስ' ['Aeons'] የተባሉ ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸው አማልእክት ነበሩ። ከነዚህ አማልክት አንዱ የሆነውና 'ዴሚኧርጅ' ['Demiurge'] የተባለው ወደ ታች ወረደና ምድርን ፈጠረ። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተጽፎ የምናገኘው ያህዌ እርሱ ነው። ይህ ዴሚኧርጅ "ፈጣሪ ለመሆን የሚያስችል በቂ መንፈስና ዓለምን ለመፍጠር የሚያስችልም በቂ ቁስ አካል በውስጡ ያለው ነው።" ከአማልክቱ መካከልም "ከሁሉ በላይ" ለሆነው እጅግ ቅርብ የሆኑት ወደ ፍፁም መንፈስነት የተጠጉ ሲሆኑ፥ ከእነርሱ ራቅ ያሉት ደግሞ የመንፈስና የቁስ አካል ቅይጦች ነበሩ።

ይህ ዓይነቱ ፍልስፍና፥ የፍልስፍናው ተከታዮች ኢየሱስን አስመልክቶ ያላቸውን እውቀት የተዛባ አድርጎታል። ሁለት የተለያዩ አመለካከቶች ነበሩ:- አንደኛው፥ ቁስ አካል እርኩሰት (ክፉ) በመሆኑ ክርስቶስ በሥጋ ማለት በቁስ አካልነት ለመገለጥ አይችልም፤ እንዲያው መከራን ለመቀበል ሰብአዊ በሆነ ቅርጽ ተገለጠ እንጂ፥ ሥጋ አልሆነም ይላል። ሌላው አመለካከት ደግሞ፥ መለኮታዊ የሆነው 'ሎጎስ' ("ቃል") ሰብአዊ በሆነው ኢየሱስ ላይ አረፈና ከስቅለቱ በፊት ተለየው በማለት ያመለክታል። በዚህ አስተሳሰብ መሠረት፥ ደኅንነት ፍልስፍናዊነትም አለበት። ለተመረጡት የተገለጠን እውቀት ከመረዳት ጋር ያያይዛል። ኃጢአትና ክፋት የሚያያዙት ካለማወቅ ጋር ነው። የኖስቲካዊነትም ዘመናዊ ገጽታ "ክርስቲያን ሳይንስ" [Christian Science] በሚል ስያሜ የሚታወቀው ኑፋቄ ነው።

## ማርቅያን ከተባለው ሰው ካኖን ጋር በተያያዘ መልኩ

እጅግ ባለጠጋ የነበረው ማርቅያን፥ በ139 ዓ.ም. ወደ ሮም በመምጣት በቤተ ክርስቲያን ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር የሞከረ ሰው ነበር። እቅዱ ባልተሳካለት ጊዜ፥ እንግዳ አስተምህሮዎች ያሉባትና የራሱ የሆነች ቤተ ክርስቲያን መሠረተ። ፍልስፍናዊ ጎናቸውን ብቻ በመቃወም፥ አንዳንድ የኖስቲካዊ አስተሳሰቦችን ይከተል ጀመር። ከሕግ ጋር በመቀየጥ ከተበከለው ወንጌል ውስጥ የወንጌል መሠረታዊ እውነት የገላቲያ መልእክት

ነው ብሎም አመነ። ከጳውሎስ አሥር መልእክቶችና በታረመ መልኩ ከተዘጋጀው የሉቃስ ወንጌል በስተቀር፥ ሌሎቹን ቅዱሳት መጻሕፍት በሙሉ አልተቀበለም። ፈጣሪ በሆነው፥ እንዲሁም የብሉይ ኪዳንን ሕግ በሰጠው ክፉ አምላክና፥ ራሱን በክርስቶስ በኩል በገለጠው የአዲስ ኪዳን አምላክ መካከል ልዩነት አለ በማለት ገለጠ። ክርስቶስ የብሉይ ኪዳን መሢሕ አይደለም በአካላዊ ሥጋም አልተገለጠም፥ የአዲስ ኪዳኑን መሀሪ አምላክ ግን ገልጧል ካለ በኋላ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕግን ባለመቀበል የብሉይ ኪዳኑን አምላክ ለመጻረር ተገለጠ፥ በዚህም ምክንያት አይሁዳውያን ሰቀሉት። ቢሆንም ክርስቶስ እውነተኛ የሥጋ አካል ስላልነበረው ጉዳት አላደረሱበትም ብሏል። ኖስቲካዊ ደኅንነት የሚገኘው በእውቀት ነው የሚሉትን በመቃወምም፥ ደኅንነት በእምነት ነው በማለት አስተማረ።

ማርቅያን ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እየቀነሰ በማውጣት፥ የራሱን ካኖን በማዘጋጀቱ ሳቢያ፥ ቤተ ክርስቲያን ትክክለኛውን ካኖን እንድትመሠርት በመገፋፋት ረድቷታል ለማለት ይቻላል።

ሞንታኑስ ከተባለ ሰው አስተምህሮ ጋር በተያያዘ መልኩ ትንሹ እስያ ውስጥ በምትገኘውና ፍርግያ በመባል በምትታወቅ ስፍራ፥ ከኖስቲካዊነት በተቃረነ መልኩ የከረረ የብሕትውና ትምህርት ያስተማረው ሞንታኑስ ብቅ አለ። ይህ ሰው በጥምቀቱ ጊዜ በልሳን በመናገር የመንፈስ ቅዱስ ዘመን እንደመጣና የዓለምም መጨረሻ እንደተቃረበ ተናግሮ ነበር። አዲሲቱ ኢየሩሳሌምም በቅርቡ የሺሁን ዓመት መንግሥት ለማብሰር ከሰማይ ብቅ እንደምትል ገለጠ። የአምላክን መገለጥ ለዓለም በማብሰር ረገድ እርሱና ደቀ መዛሙርቱ የመጨረሻዎቹ ነቢያት መሆናቸውንም አስታወቀ። ከደቀ መዛሙርቱ መካከል አዳዲስ መገለጦችን በመስጠት በነቢይነት የሚታወቁ ሁለት ሴቶች ነበሩ። ሞንታኑስ የወንጌላዊው ዮሐንስን ጽሑፍ ተገን በማድረግ፥ መንፈስ ቅዱስ የሆነው ጰራቅሊጦስ ለዓለም ለመናገር የሚጠቀምበት አፈ መለኮት የሆነ ያህል ይሰማው ጀመር። የዘመን ፍጻሜ በመሆኑ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በመገለጥ ላይ መሆናቸውንም ተናግሯል። በአጠቃላይ ሲታይ የአስተምህሮው ሁኔታ ትክክል ቢሆንም፥ "መንፈስ ቅዱስ በነቢያት መናገሩን ቀጥሏል። ይህ ሴቶችንም ያጠቃልላል" ብሏል።

ሞንታኑስ ተከታዮቹ ጥብቅ ሥነ ምግባር እንዲኖራቸው ይፈልግ ስለነበር፥ ትንሹ እስያ ውስጥ ከፍ ያለ ተቀባይነትን አግኝቷል። በጾምና ከቅንጦት ምግብ በመቆጠብ ላይ ከማተኮሩም በላይ ከትዳር ጓደኛ ሞት በኋላ ጋብቻን ይከለክልና ብህትውናን፥ እንዲሁም ሰማዕትነትን ያበረታታ ነበር።

ትምህርቱ በ381 ዓ.ም. በቁስጥንጥንያው ጉባኤ ቢወገዝም፥ ታዋቂውን ተርቱሊያንን እንኳ እስኪማርክ ድረስ ከፍተኛ ተቀባይነትን አግኝቶ ነበር።

# የካኖን ድንጋጌና የእምነት መግለጫዎች

## የእምነት መመሪያ

ከመናፍቃን ቡድኖችና አስተማሪዎች መከሰት የተነሣ፥ በተለይም በማርቅያን ሳቢያ፥ እውነተኛዎቹን አስተምህሮዎችና ትክክለኛዎቹን የእስትንፋሰ-መለኮት መጻሕፍት መወሰኑ አስፈላጊ ሆነ። የአዲስ ኪዳን ካኖን እውቅናን ከማግኘቱ በፊት፥ የቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች እውነተኛውን አስተምህሮ ለመቀበልም ሆነ የተሳሳተውን ለመቃወም "የእምነት መመሪያ" ለማውጣት ተገደው ነበር።

የቀድሞው የሐዋርያት የእምነት መግለጫም ይኸው ነው። የቀድሞው የእምነት መመሪያ በማቴዎስ 28፡19 የተጠቀሰውና ስለ ሥላሴ የሚመሰክረው የጥምቀት መመሪያ ነበር።

"ጥንታዊ የሮማውያን የእምነት መግለጫ" የሚባለው ይህ መመሪያ፥ በሐዋርያት የተጀመረና በጴጥሮስ አማካይነት ወደ ሮም ተወስዶ እስከ ሁለተኛው መቶ ዓመት አጋማሽ ድረስ ጥቅም ላይ እንደዋለ ይታመናል። ይህ አጭር የሮማውያን የእምነት መግለጫ እንዲህ ይነበባል፦ "በልዑል እግዚአብሔር አብ አምናለሁ፥ ብቻውንም ልጁ በሆነ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ፥ በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማርያም በተወለደ፥ በጴንጤናዊው ጲላጦስ በተሰቀለው፥ በተቀበረው፥ በሦስተኛውም ቀን ከሞት በተነሣው፥ ወደ ሰማይ ባረገና በአብ ቀኝ በተቀመጠ፥ በሙታንና በሕያዋን ላይ ሊፈርድ በሚመጣ፥ በመንፈስ ቅዱስም፥ በቅድስት ቤተ ክርስቲያንም፥ በኃጢአት ስርየትም፥ በሥጋ ትንሣኤም፥ በዘላለም ሕይወትም እናምናለን።"

## የአዲስ ኪዳን ካኖን

ለአዲስ ኪዳን ካኖን መጀመሪያ እውቅና በተሰጠበት ወቅት፥ የጳውሎስ መልእክቶች በየአብያተ ክርስቲያኑ የመነበብ ሥልጣን አግኝተው ነበር። ኤሬኔዎስ ማርቅያንንና ኖስቲካውያንን በመቃወም አራቱን ወንጌላት ተቀበለ። በ175 ዓ.ም. አካባቢ ሙራቶሪያን ካኖን ውስጥ ዕብራውያን፥ 1ኛ እና 2ኛ ጴጥሮስ፥ 1ኛ ዮሐንስ እና የያዕቆብ መልእክት ሲቀሩ፥ ሌሎቹ

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተመዘገቡ። አትናቴዎስ የተባለው ሰው ደግሞ በ367 ዓ.ም. ሁሉንም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት አስመዘገበ። ከዚያም ሃያ ሰባቱ መጻሕፍት በስፋት ተቀባይነት አገኙ።

## የሐዋርያት የእምነት መግለጫ

ቀዳሚው የሐዋርያት የእምነት መግለጫ የወጣው፥ በግምት በ340 ዓ.ም. ሲሆን፥ የማርቅያንንና የሌሎችን የስሕተት ትምህርት ለመከላከልና ትክክለኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ለማጽናት የተደረገ ተጨማሪ ጥረት ነበር። እያንዳንዱ ሐዋርያ ለዚህ መግለጫ የጽሑፍ አስተዋጽኦ አድርጓል የሚል አፋዊ ታሪክም አለ። ጅማሬው በእርግጥ እጥር ምጥን ባለ መልኩ ከማቴዎስ 28፡19 ሊሆን ይችላል። ሌሎች መሠረታዊ የቅዱሳት መጻሕፍት መሠረቶች ደግሞ ሮሜ 10፡9-10፥ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡3፥ 15፡4፥ እና 1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16 ሊሆኑ ይችላሉ።

የሐዋርያት የእምነት መግለጫ የወጣው፥ ሐዋርያት ባስተማሩበትና በሰበኩበት ዘመን ነው። "የእምነት መመሪያ" የሚለው ስያሜ በቀደመ መልኩ የሐዋርያትን የእምነት መግለጫ ይመለከታል። መግለጫው በሁለት መልኩ የዳበረ ነበር፤ አንደኛው "ጥንታዊ የሮማውያን የእምነት መግለጫ" ተብሎ የሚታወቀው፥ አጠር ያለውና የቀደመው ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ ረዘም ያለና "የተቀበልነው" በመባል የሚታወቀው ነበር። ይህ "የተቀበልነው" የተሰኘ አቀራረብ እንዲህ ይነበባል፡- "ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በልዑል እግዚአብሔር አብ አምናለሁ፥ አንድያ ልጁ በሆነ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ፥ በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ፥ ከድንግል ማርያም በተወለደ፥ በጴንጤናዊው ጲላጦስ በተሠቃየ፥ በተሰቀለ፥ በሞተ፥ በተቀበረ፥ ወደ ሲኦል በወረደ፥ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን በተነሣ፥ ወደ ሰማይ ባረገ፥ በልዑል እግዚአብሔር ቀኝ በተቀመጠ፥ ከዚያም በሙታንና በሕያዋን ላይ ሊፈርድ በሚመጣ፥ በመንፈስ ቅዱስ፥ በአንዲት ቅድስት ሁሉ-አቀፋዊት ቤተ ክርስቲያን፥ በቅዱሳን ሕብረት፥ በኃጢአት ይቅርታ፥ በሥጋ ትንሣኤ፥ በዘላለም ሕይወት አምናለሁ። አሜን።" ይህ ረጅምና ቀዳሚ የእምነት መግለጫ የታየው በ650 ዓ.ም. ቢሆንም ከ460 ዓ.ም. ጀምሮ እንደነበረም ይታወቃል።

የሐዋርያት የእምነት መግለጫ ዓላማ፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመተካት ሳይሆን፥ ይልቁንም ለማጽናት፥ እውነትነታቸውን ለማረጋገጥና ቤተ ክርስቲያንንም ከሰርጎ ገብ መናፍቃን ለመጠበቅ ነው። ለምሳሌ

በመግለጫው ላይ "ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በልዑል እግዚአብሔር እናምናለን. . ." የሚለው አሳብ "ክፉ የሆነ ፈጣሪ አምላክ" የሚለውን የማርቅያንን አሳብ የሚሽር ነው። "ከድንግል በተወለደ፥ በሞተ. . ." በማለት ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ የሚገልጠው ደግሞ፥ የኖስቲካውያንንና ዶሴቲሲያውያንን፥* [Docetists] "ኢየሱስ መንፈስ ብቻ ነው" የሚለውን ትምህርት ይሽራል።

# ጥንታዊ አስተምህሮ ሥላሴ

አስተምህሮ ሥላሴን አስመልክቶ የነበረው ዋነኛ ችግር፥ ብሉይ ኪዳናዊው የአሀዳዊነት እምነት ነበር። ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር አንድ ነው ከሚለው ትምህርቷ ጋር የክርስቶስን መለኮትነት እንዴት ነው የምትቀበለው? የሚለው ጥያቄ ዋነኛው ነበር። ቤተ ክርስቲያን ገና ከጅማሬዋ የሥላሴን አስተምህሮ በሚመለከት ግልጥ የሆነ ግንዛቤ አልነበራትም። ክርስቶስ በተለያየ መንገድ ነበር ይገለጥ የነበረው። አንዳንዶቹ የእግዚአብሔር አሳብ፥ ማለት አካላዊነት ያልነበረውና ሥጋ በለበሰ ጊዜ አካላዊ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ('ሎጎስ') ነው ሲሉት፥ ሌሎች ደግሞ የለም ከአብ ጋር አይስተካከል እንጂ፥ ዘላለማዊነት ያለው ነው ይሉ ነበር። በመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ዘመን፥ አስተምህሮ መንፈስ ቅዱስን አስመልክቶ ያለውም ግንዛቤ በጣም አነስተኛ ነበር። አንዳንዶች መንፈስ ቅዱስ ከአብም ሆነ ከወልድ ያነሰ አድርገው ነበር የተገነዘቡት።

## *ሞናርኪያኒዝም [Monarchianism]*

አስተምህሮ ሥላሴን በሚመለከት ቤተ ክርስቲያንን የገጠሟት ሁለት ጉዳዮች፥ በአንድ በኩል የእግዚአብሔርን አንድነት (አሀዳዊነት) ጠብቆ፥ በሌላ በኩል ደግሞ የክርስቶስን መለኮትነት መቀበሉ ነበር። አስተምህሮ ሥላሴን አስመልክቶ በመጀመሪያ የተከሰተው ኑፋቄ፥ በሁለት የሚከፈለው "ሞናርኪያኒዝም" ነው። የዚህ ኑፋቄ አንደኛው ክፍል፥ ብዙ ተቀባይነት ያላገኘው "ኃያል ሞናርኪያኒዝም" ["Dynamic Monarchianism"] የተሰኘው ሲሆን፥ የክርስቶስን አካላዊነት በመሻር የእግዚአብሔርን አሀድነት ለማጽናት ሞክሯል። ቀደም ሲል በ190 ዓ.ም. ይህን ዓይነቱን አስተምህሮ ያራመደው፥ የቢዛንቲኑ [Byzantium] ቴዎዶተስ [Theodotus]፥ ከዚያ በኋላ ደግሞ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ የሆነው የሳምሳጢው [Samosota] ጳውሎስ ነበር። ስለ 'ሎጎስ' (ቃል) ሲያስተምርም እንዲህ ብሏል፦

---

* በዚህ ርእስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት አባሪ አንድን ይመልከቱ።

"ከአብ ጋር ልዩነት የለውም፥ ይሁን እንጂ በግጻዌ መለኮት ["Godhead"] ውስጥ አንድ ጉልህ አካል አይደለም። የሰው አመክንዮ [reason]፥ በሰው ውስጥ እንዳለ ሁሉ፥ ሎጎስም በእግዚአብሔር ውስጥ ስለሚኖር በእግዚአብሔርነት ሊቆጠር ይችላል። ይሁን እንጂ እርሱ አካላዊነት የሌለው ኃይል ነው። ይህ ኃይል በሰዎች ሁሉ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፥ በኢየሱስ ሰብአዊነት ውስጥ ግን ይበልጥ ይሠራል። በሌላ በማንም ላይ ባልተደረገ ሁኔታ በኢየሱስ ሰብእና ጠልቆ በመግባት የርሱን ሰብእና አምላክ አደረገው። ስለዚህ ምንም እንኳ እንደ እግዚአብሔር ባይቆጠርም፥ የመለኮት ክብር የተገባው ነው።"

ይህ አስተምህሮ የእግዚአብሔርን አሃዳዊነት ቢጠብቅም፥ በሥላሴ መካከል ያለውን የአካላት ልዩነት ግን የጠበቀ አይደለም።

የሞናርኪያኒዝም ሁለተኛ ጉዳይ፥ ቅርጻዊ ሞናርኪያኒዝም [Modalistic Monarchianism] የሚባለው ሲሆን፥ ይህም ኃያል ሞናርኪያኒዝም [Dynamic Monarchianism] ከሚለው ይልቅ ተቀባይነት አግኝቷል። ይህ አቀራረብ የእግዚአብሔርን አንድ ብቻ መሆን ቢጠብቅም፥ ለክርስቶስ መለኮትነትም ከፍተኛ አጽንኦት ይሰጣል። በተሠገዎ (ሥጋን በመልበስ) መከራን የተቀበለውና የሞተውም አብ ነው የሚል እምነትም ነበረው። ይህ አስተምህሮ የትምህርቱ አቀንቃኝ በነበረውና ሰባልዩስ [Sabelius] በተባለ የምሥራቅ አገር ሰው መጠሪያነት የሰባልዮስ ትምህርት የሚል ስያሜ አግኝቷል።

ስያሜያዊ "ቅርጻዊነት" ሞዳላዊነት ["Modalistic"]** የሚለው ስያሜ፥ እግዚአብሔር አንድ አምላክ ሆኖ በተለያየ ቅርጽ ማለትም፥ አንዳንዴ አብ፥ ሌላ ጊዜ ወልድ፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ በመሆን ራሱን የገለጠ መሆኑን ያመለክታል። ምንም እንኳን ስያሜያዊ ሞናርኪያዊያን ስለሦስት አካላት ቢናገሩ፥ አንድ አምላክ መኖሩንና ይህ አምላክ ራሱን በሦስት ስያሜ ወይም ቅርጽ መግለጡን ያምናሉ። በዚህ አመለካከት መሠረት አብ እንደ ወልድ ተወለደ፥ አብ በመስቀል ላይ ሞተ፥ አብ ራሱን በራሱ ከሞት አስነሣ ማለት ነው። እንዲያውም የዚህ ትምህርት ጀማሪ ነው ተብሎ የሚገመተውና ፕራክሲየስ [Praxeus] የተባለው ሰው አብ የራሱ ልጅ ሆነ ብሏል።

---

** በዚህ ርእስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት አባሪ አንድን ይመልከቱ።

## አርዮሳዊነት

ሥላሴን አስመልክቶ በተነሣው ውዝግብ ውስጥ እጅግ ታዋቂው የአሌክሳንድሪያው ቤተ ክርስቲያን መሪ የነበረው፥ አርዮስ ነው። አርዮስ ቅርጻዊ ሞናርኪያኒዝምን በመቃወም ሲያስተምር፥ ዘላለማዊ ተብሎ የሚጠራ አንድ አምላክ ብቻ ሲሆን፥ እርሱም ከሰው አእምሮ በላይ ነው ብሏል። ክርስቶስ ዘላለማዊ ነው ማለት፥ ሁለት አማልክት አሉ እንደማለት ነው ብሎም አስተማረ። በትምህርቱ፥ ወልድ ጅማሬ አለው፥ እርሱ ህልውና ያልነበረበት ጊዜ ነበር ካለ በኋላ፥ ወልድ ከአብ እኩል ባሕርይ የለውም፥ በአብ የተፈጠረ ነው ብሏል። ከዚህም ሌላ ክርስቶስ ከሌሎች ፍጥረታት በፊት የተፈጠረና በእርሱም በኩል እግዚአብሔር ሌሎችን ፍጥረታት የፈጠረበት ነው። ስለዚህ ክርስቶስ ከፍጥረታት ሁሉ ከፍተኛውን ሥፍራ የያዘ ነው፤ ቢሆንም እግዚአብሔር ስላልሆነ የመለወጥ ባሕርይ አለው አለ።

አርዮስ ርቱዕ አንደበት በነበረው የአሌክሳንድሪያው አትናቴዎስ ተቃውሞ ገጥሞታል። አትናቴዎስ በመለኮት ውስጥ ያሉትን ሦስት አካላት ሳይጥል፥ የእግዚአብሔርን አንድነት በጽኑ ያስተማረ ሰው ነው። የወልድን ዘላለማዊ ህላዌም አስገንዝቧል። በመሆኑም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ለትክክለኛው ሃይማኖት ቋሚና ተሟጋች በመሆን ጎልቶ ይታያል።

## የኒቅያው ጉባኤ

በአርዮስ ትምህርት የተነሣ የተፈጠረውን ውዝግብ ለመፍታት በ325 ዓ.ም. ኒቅያ በተባለው ሥፍራ አንድ ጉባኤ ተካሄደ። በጉባኤው ላይ 300 ጳጳሳት ተገኝተው ነበር። ጉባኤው አርዮስንም ሆነ፥ አርዮሳዊነትን የሚቀበሉትን ሁሉ አውግዟል። በንጉሡ ካስጸደቀ በኋላም የሚከተለውን የሃይማኖት መግለጫ አወጣ፡-

> “ሁሉን በሚችል፥ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ፥ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን። የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው፥ በአንዱ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ፥ ከአብ ብቻውን በተገኘው፥ ከአብ ጋር መገኛው [‘ኡሲያስ’/‘ousias’] አንድ በሆነው፥ ከአምላክ በተገኘ አምላክ፥ ከብርሃን በተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ በተገኘ እውነተኛ አምላክ፥ በተፈጠረ ሳይሆን በተወለደ፥ ከአብ ጋር በማንነት [‘homoousion’] አንድ በሆነ፥ ሁሉ በእርሱ በሆነ፥ በሰማይም ይሁን በምድር ባለው፥ ለእኛ ለሰው ልጆች ደኅንነት ወርዶ ሥጋ በሆነ፥ ሰውም በሆነ፥ መከራን በተቀበለ፥ በሦስተኛው

ቀን በተነሣ፥ ወደ ሰማይ ባረገ፥ በሙታንና በሕያዋን ላይ ሊፈርድ በሚመጣው እናምናለን።"

በሃይማኖት መግለጫው ውስጥ የተጠቀሰው "ማንነት" የተሰኘው ቃል አመጣጡ 'ሆሞሲዮን' ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን፥ ፍቺውም ክርስቶስ የአብ አምሳያ ነው ማለት ሳይሆን፥ ከአብ ጋር ፍፁም የሆነ የህልውና አንድነት አለው ማለት ነው። "ከአምላክ በተገኘ አምላክ" እና "ከእውነተኛ አምላክ በተገኘ እውነተኛ አምላክ" የሚለው አገላለጥ፥ የክርስቶስን መለኮትነት ይበልጥ የሚያጸና ነው። "የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ" የሚለውና "ወደ ምድር የመጣ" የሚለው ደግሞ የሰው ልጅነቱን አበክሮ ይገልጣል።

ከኒቅያው ጉባኤ በኋላ 'ሆሞሲዮን' በሚለው ቃል ዙሪያ የሚሽከረከር ውዝግብ ተፈጠረ። ይህ ቃል ብዙዎች ተቃውመውት ነበር። ቃሉ ለረዥም ግዜ የውዝግብ አርዕስት ሆኖ ቆይቷል። በዚህ መካከል አርዮስና አትናቴዎስ በተደጋጋሚ ከቤተ ክርስቲያን ተወግደዋል። በአንድ ወቅት ደግሞ ምዕራባውያን የአትናቴዎስን አመለካከት ሲደግፉ፥ ምሥራቃውያን ደግሞ ሌላ የተሻሻለ መግለጫ ፈለጉ። በመጨረሻ ግን በ381 ዓ.ም. ንጉሥ ቴዎዶሲዮስ [Theodosius] የኒቅያውን የሃይማኖት መግለጫ የተቀበለውን የቁስጥንጥንያ ጉባኤ ሰበሰበ። ጉባኤውም 'ሆ ሞሲያን' የሚለውን ቃል በሃይማኖት መግለጫው ውስጥ መቀበሉን አረጋግጧል።

## የቁስጥንጥንያው ጉባኤ

በኒቅያው ጉባኤ የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ ከሥላሴ አካላት አንዱ የሆነው የመንፈስ ቅዱስ አስተምህሮ በግልጥ አልተቀመጠም። መግለጫው ያረጋገጠው "በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን" የሚለውን ብቻ ነበር። በዚህ ጊዜ አርዮስ የወልድ የመጀመሪያ ፍጡር መንፈስ ቅዱስ ነው ብሎ አስተማረ። የቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ መቅዶንዮስ [Macedonius] ደግሞ፥ መንፈስ ቅዱስ ልክ እንደ መላእክት ፍጡር የሆነና የወልድ ተገዢ ነው አለ። አትናቴዎስ ግን መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር የህልውና አንድነት ['homoousian'/'ሆሞኡሲያን'] አለው በማለት አጸና። ይሁን እንጂ፥ የቁስጥንጥንያው ጉባኤው በ381 ዓ.ም.፥ "ጌታ በሆነና ሕይወት በሚሰጥ፥ ከአብ በሚወጣና ከአብና ከወልድ እኩል አምልኮን በሚቀበል፥ በነቢያትም በተናገረ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን" የሚለውን መግለጫ አውጥቷል። መግለጫው መንፈስ ቅዱስ በህልውና ከውልድና ከአብ ያነሰ ሳይሆን፥ እኩል መሆኑን በጽኑ አረጋግጧል።

# ጥንታዊ አስተምህሮ ክርስቶስ

*መነሻ*

ሥላሴን አስመልክቶ የሚነሣ ውዝግብ የሥነ-ክርስቶስም ውዝግብ ነው። ክርክሩ የሚያካትተው የክርስቶስን እውነተኛ መለኮትነትና እውነተኛ ሰብእና ብቻ ሳይሆን፥ በሰብእናውና በመለኮትነቱ መካከል ያለውን የባሕርይ ግንኙነትም ነው። ጉዳዩ በውዝግብ ሂደ፥ መጣ እያለ ቀጠለና ዶሴቲሲያውያን የተሰኙ ወገኖች የኢየሱስን ሰብእና፥ ኢቢዮናውያን* የተባሉት ደግሞ መለኮትነቱን ካዱ። አርዮሳውያን መለኮትነቱን ዝቅ አደረጉ፥ አቡሊናርዮሳውያን የተባሉት ክፍሎች ሰብእናውን አሳነሱ፥ ንስጥሮሳውያን የሁለቱን ባሕርያት ውህደት ካዱ፥ አውጣኪዎች** ደግሞ የክርስቶስን አንድ ባሕርይ ብቻ አጸኑ።

# አቡሊናርዮሳዊነት

ወጣቱ አቡሊናርዮስ [Apollinarius] በመባል የታወቀው ሰው፥ አርዮሳዊነትን በመቃወም ወደ ተቃራኒው አቅጣጫ እጅግ የራቀ ትምህርት አስተማረ። በዚህ አክራሪነቱም ኑፋቄ ሆኗል። አቡሊናርዮስ "መለኮት የሆነው ቅድመ ህላዌ ቃል ('ሎጎስ')፥ ሰው በሆነው ኢየሱስ ውስጥ በመንፈስ አደረ። ስለዚህ ኢየሱስ ሰብአዊ አካልና ሰብአዊ ነፍስ ቢኖረውም፥ የሰው መንፈስ አልነበረውም" በማለት አስተማረ። የሰው መንፈስ ስለሌለው ደግሞ የኢየሱስ አካል እንደ ሰው አካል ሊቆጠር አይችልም. . . በማለትም የክርስቶስን የሰውነት ባሕርይ ከሰብእና በታች አድርጎታል። በርሱ አመለካከት የሰው መንፈስ የኃጢአት ማደሪያ ነው፤ ስለዚህ ክርስቶስ ኃጢአት የለሽ የሚሆነው ሰብአዊ ያልሆነ መንፈስ ሲኖረው ብቻ ነው።

የአቡሊናርዮስ አመለካከት ትልቁ ችግር፥ የክርስቶስን መለኮትነት ተቀብሎ ትክክለኛ ሰብእናውን መካዱ ነው። በዚህ ትምህርት መሠረት ክርስቶስ ከሰብእና በታች ነው። አቡሊናርዮስ በክርስቶስ ሰብእናና

---

* ኢቢዮናውያን በጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ከድንግል መወለድና አምላክነቱን ከደው፥ ኢየሱስ ሰብአዊ የሆነ ነቢይ ብቻ ነው በማለት የሚያስተምሩ የሃይማኖት ክፍል ናቸው።

---

** በዚህ ርእስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት አባሪ አንድን ይመልከቱ።

በመለኮትነቱ መካከል ያለውን አንድነት ሲፈልግ፥ የክርስቶስን ሰብእና ክዷል። በዚህም ሳቢያ በ381 ዓ.ም. በተካሄደው የቁስጥንጥንያ ጉባኤ ተወገዘ።

## ንስጥሮሳዊነት

ንስጥሮስ [Nestorius] የኬልቄዶን ጉባኤ ማርያምን "የአምላክ እናት" በማለት የጠቀሰውን መግለጫ አልወደደውም። ምንም እንኳ መግለጫው ስለ ክርስቶስ ሰብእና ቢገልጥም፥ ንስጥሮስ ይህን የማርያምን አምልኮ ያስከተለ መግለጫ ተቃውሟል። ክርስቶስን አስመልክቶ በአንድ አካል ሁለት ባሕርይ መኖሩን ከመቀበል ይልቅ፥ "በክርስቶስ መለኮትነትና ሰብእና መካከል ውህደት መኖሩን በመካድ ሁለት ባሕርይ፥ በሁለት አካላት" የሚል አቋም ያዘ። ክርስቶስ በሰብእናው መከራን ሲቀበል፥ መለኮትነቱ ጣልቃ አልገባም በማለትም አስተማረ። (ጆን የተባለው የደማስቆ መምህርም ይህን የመሰለ አመለካከት ነበረው።) ይህ ትምህርት፥ የክርስቶስን ሥጋ መልበስ ትክክለኛ ትምህርት የሚቃወምና፥ መለኮትነቱንና ሰውነቱን ከመቀበል ይልቅ፥ በክርስቶስ ያሉ ሁለት አካላት ሳይዋሃዱ አምላክም ሰውም ሆነው ለየብቻ ይኖራሉ የሚል ነው። ንስጥሮስ ማርያም የኢየሱስ ሰብእና ብቻ መገኛ ስለሆነች፥ ክርስቶስ ሁለት የተለያዩ አካላት አሉት ብሎም አምኗል። ይህ ሰው የክርስቶስን መለኮትነት የካደውን አርዮስንና፥ የማርያምን አምልኮ ለመቃወም ቢነሣም፥ የክርስቶስን ሰብእናና መለኮትነት መዋሃድ ክዶ በ431 ዓ.ም. በኤፌሶኑ ጉባኤ ተወግዟል።

## አውጣኪነት

ከ380-456 ዓ.ም. የኖረው አውጣኪ [Eutyches]፥ ንስጥሮስን በመቃወም "ሞኖፊሳይት" [Monophysite] የተሰኘውንና ክርስቶስ አንድ ባሕርይ ብቻ እንዳለው የሚገልጠውን የኑፋቄ ክፍል መሠረተ። በዚህም መሠረት "ክርስቶስ መለኮታዊ ባሕርዩ ለሰብእና ባሕርዩ እንደሚመች ሆኖ ሰብእናውን ያዘ እንጂ በእርግጥ መለኮት አልነበረም። . . . እንዲሁም ሰብአዊ ባሕርዩ ለመለኮታዊ ባሕርዩ የሚመች ሆኖ መለኮታዊ ባሕርዩን ያዘ እንጂ በእርግጥ ሰብአዊ አልነበረም" አለ።

በአውጣኪ ትምህርት መሠረት እንግዲህ፥ ክርስቶስ ሰብአዊም መለኮታዊም አይደለም። ይህ ሰው በትምህርቱ አዲስ ሦስተኛ ባሕርይ ፈጠረ። በዚህ ትምህርት መሠረት ክርስቶስ ሰብአዊም መለኮታዊም ያልሆነ አንድ ባሕርይ ብቻ ነው ያለው።

ይህ አመለካከት በ451 ዓ.ም. በኬልቄዶን ጉባኤ ቢወገዝም፥ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተቀብላዋለች።

በኋላም የዚህ አመለካከት ልዩ ልዩ ገጽታ "ሞኖቴላይት" [Monothelite] በሚባለው አዲስ ስያሜ ተራባ። ይህ አመለካከት ክርስቶስ ያለው አንድ ፍቃድ ብቻ ነው የሚል ትምህርት ሲያቀርብ ቆይቶ፥ በ680 ዓ.ም. በተካሄደው የቁስጥንጥንያ ጉባኤ ተወግዟል።

## የአስተምህሮ ክርስቶስ ኑፋቄዎች

| መናፍቃን | ወቅት | ማጣቀሻ | መለኮታዊውን ባሕርይ | ሰብአዊውን ባሕርይ |
|---|---|---|---|---|
| ዶሴቲሲያውያን | የ1ኛው ምዕተ ዓመት መገባደጃ | 1ኛ ዮሐንስ 4፡1-3 | ተቀበሉ | ካዱ |
| ኢቢዮናውያን | 2ኛው ምዕተ ዓመት | ኤሬኔዎስ | ካዱ | ተቀበሉ |
| አርዮሳውያን | 4ኛው ምዕተ ዓመት | በ325 ዓ.ም. በኒቅያ ጉባኤ የተወገዘ | ዝቅ አደረጉ | ተቀበሉ |
| አቡሊናርዮሳውያን | 4ኛው ምዕተ ዓመት | በ381 ዓ.ም. በቁስጥንጥንያ ጉባኤ የተወገዘ | ተቀበሉ | ዝቅ አደረጉ |
| ንስጥሮሳውያን | 5ኛው ምዕተ ዓመት | በ431 ዓ.ም. በኤፌሶን ጉባኤ የተወገዘ | ተቀበሉ* | ተቀበሉ |
| አውጣኪዎች | 5ኛው ምዕተ ዓመት | በ451 ዓ.ም. በኬልቄዶን ጉባኤ የተወገዘ | ዝቅ አደረጉ** | ዝቅ አደረጉ |

* ንስጥሮሳውያን ክርስቶስ ሁለት አካል ነበረው ብለው ያምኑ ነበር።

** አውጣኪዎች ክርስቶስ ሙሉ ሰውም ሆነ ሙሉ መለኮታዊ ያልሆነ፥ አንድ የተዋሃደ ባሕርይ ነበረው በማለት ያስተምሩ ነበር።

# ጥንታዊው ሥነ-መለኮት

## *ኃጢአትና ጸጋ*

ፔላጊዩስ። ይህ ሰው የተገለለና አስቸጋሪ ኑሮ የኖረ እንግሊዛዊ መነኩሴ ሲሆን፥ አውግስጢኖስ ካለፈባቸው መንፈሳዊ ውዝግቦች አንዱንም የሚያውቅ አልነበረም።

ፔላጊዩስ ስለ ሰው እና ስለ ደኅንነት ያለውን አስተምህሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ያቀረበው ወደ 400 ዓ.ም. ገደማ ሮም ውስጥ ነው። በ410 ዓ.ም. ወደ አፍሪካ መጥቶ አውግስጢኖስ ከተባለው ሰው ጋር ቢገናኝም፥ በሁለቱ መካከል የከረረ አለመግባባት ተፈጥሮ ነበር። የግጭታቸው መሠረታዊ ጉዳይ፥ የሰውን ነጻ ፈቃድና የውርስ ኃጢአት [original sin] የሚመለከት ነበር። ፔላጊዩስ፥ ሰው መልካምም ሆነ ክፉ ማድረግ ከሚችል ነፃ ፈቃድ ጋር እንጂ፥ ከአዳም ከሚወረስ ኃጢአት ጋር አይወለድም ብሎ አመነ። ይህም የሚሆነው ሰው ሲወለድ እግዚአብሔር እያንዳንዷን ነፍስ ልክ እንደ አዳም ጊዜ ነጻ አድርጎ ስለሚፈጥራት ነው። እያንዳንዷም ነፍስ መልካም ወይም ክፉ የማድረግ ችሎታ አላት። እንደ እውነቱ ከሆነ ኃጢአት የለሽ ኑሮ ለመኖር ይቻላል። ምክንያቱም የአዳም ኃጢአት የሰውን ልጅ ዘር በሙሉ ሳይሆን፥ እርሱን ብቻ ነው የሚመለከተው። ስለሆነም ማንኛውም ሰው በማንኛውም አጋጣሚ ከሚቀርቡለት ክፉና ደግ ሁኔታዎች መካከል መርጦ መልካሙን ወይም ክፉውን ለማድረግ ይችላል። ፔላጊዩስ በዓለማችን ያለው የኃጢአት ችግር ምክንያቱ ሰዎች "መጥፎ ምሳሌ ስለሚያዩ"፥ ወይም "የተሳሳተ ትምህርት ስለሚሰጣቸው" ነው ይላል። ምንም እንኳ የእግዚአብሔር ጸጋ በሕይወት ለሚገጥም ክፉ ነገር ማሸነፊያ የሚጠቅም ቢሆን፥ ለደኅንነት ግን አስፈላጊ አይደለም። ምክንያቱም ሰው ደኅንነትን የመምረጥ ችሎታ አለው። ሰው በውርስ ያገኘው ክፉ ነገር ስለሌለ፥ የሕጻናት ጥምቀት ለደኅንነት አስፈላጊ አይደለም። የሕጻናት ጥምቀት ልጆችን የማስመረቅ ሥርዓት ብቻ ነው ይላል።

አውግስጢኖስ። ይህ ሰው የተወለደው በ354 ዓ.ም. ሰሜን አፍሪካ ውስጥ ነው። ምንም እንኳ እናቱ ክርስቲያን ብትሆን፥ እርሱ ግን ከመልካም ሥነ ምግባር የወጣ፥ የተቅበዘበዘ፥ ሰላምና ዕረፍት የለሽ ሕይወት ያለው ነበር። ለሕይወቱ ሰላም በመሻትም የማኒኪያውያን* ደቀ

---

* ማኒኪያውያን በ3ኛው መቶ ዓመት ፋርስ በተባለው አገር የተነሣው ማኒ የተባለ ኑፋቄ ተከታዮች ነበሩ። ማኒ የፋርሳውያንን፥ የክርስቲያንና የቡዲህስትን ትምህርቶች በማጣመር አዲስና የተለየ ሃይማኖት አስነሣ። ራሱንም 'ጰራቅሊጦስ' ['parakletos'] ('አፅናኝ' የዮሐንስ ወንጌል 14፡ 16) ብሎ በመጥራት፥ እየሰበከና እያስተማረ በፋርስ፥ በሕንድና በባቢሎን ተጓዘ። ትምህርቱም ወደ ምዕራብ በመስፋፋት እስከ መካከለኛው ዘመን ድረስ ቆየቷል።

መዝሙር ሆነ። ቀጥሎም አዲሱን የፕሌቶ [Plato] ፍልስፍና አጠና። አምብሮዝ [Ambrose] በተባለው የሚላን [Milan] ጳጳስ አማካይነትም ስለ ክርስትና አወቀ። ይሁን እንጂ፥ የኃጢአትን አስከፊ ኃይል ለማሸነፍ አለመቻሉ ያሠቃየው ነበር። ሮሜ 13፡14 ላይ ያለውን ቃል ካነበበ በኋላ ግን፥ ከዚህ የኃጢአት ሸክም በመላቀቅ ክርስቲያን ሆነና ሕይወቱ ተለወጠ። ወዲያውኑ የጳውሎስን መልእክቶች በጥንቃቄ ማጥናቱን ቀጠለ፤ የእግዚአብሔርን ጸጋም ተለማመደ።

ያለምንም ጥርጥር ሥፍራው በጳውሎስና በሉተር መካከል ነው የሚባልለት የሥነ-መለኮት ሰው አውግስጢኖስ፥ የሚከተሉትን አስተምህሮዎች መሥርቷል፦ ሰው ከውድቀት በፊት በእግዚአብሔር አምሳል በጥበብ፥ በፍጹምነት፥ በቅድስናና ኢ-መዋቲ በሆነ ሕይወት ውስጥ ነበር። በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረውን ክብር ያጣው ከአዳም ኃጢአት የተነሣ ነው። ለእግዚአብሔር ሊኖረው የሚገባን ፍቅር በራስ ፍቅር ተካው። ኃጢአትን ለመከላከል ወደማይችልበት ሁኔታ ተለወጠ። የሰው ፈቃድ ተበከለ፥ ወደ ክፋም አዘነበለ፥ ነጻ መሆኑም ቀረ።

በዚህም ምክንያት በኃጢአት የወደቀው ሰብአዊ ተፈጥሮውና ውጤቱ፥ ለመላው የሰው ልጅ ተላለፈ። በአውግስጢኖሳዊው የኃጢአት መተላለፍ አስተምህሮ መሠረት፥ የሰው ልጅ በሙሉ "በአዳም ዘር ውስጥ" ነበር። በመሆኑም አዳም ኃጢአት በሠራ ጊዜ፥ መላው የሰው ዘር፥ እስከ ዘመን ፍጻሜ የሚኖረው ሁሉ፥ በአዳም ኃጢአት እንደተሳተፈ ተቆጥሮ በበደለኛነት ይፈረድበታል። እንደዚህ ነው አውግስጢኖስ ሮሜ 5፡12 ላይ ያለውን ቃል የተገነዘበው። ይህ የጸጋ መገፈፍና ፍርድ ሕፃናትን ሳይቀር በክሏቸዋል።

ሰው ከፍጹም የኃጢአት ብክለት እንዲድንና የተገፈፈ ጸጋው ይመለስለት ዘንድ፥ የእግዚአብሔር ጸጋ ያስፈልገዋል። በውድቀት ሳቢያ የሰው ብቸኛ ፈቃድ ኃጢአት ማድረግ ሆነ። መልካም ነገር ማድረግ ተሳነው። በዚህ ምክንያት፥ ደኅንነትን ለማረጋገጥ እግዚአብሔር ጸጋውን ላከ። ይህንንም አውግስጢኖስ "የማይገታ ጸጋ" ብሎ ሰይሞታል። የእግዚአብሔር ጸጋ የሰውን ተፈጥሮ በመቃወምና በመቃረን አይሠራም። ይልቁንም ሰው መልካሙን ይመርጥ ዘንድ ፈቃዱን ይለውጠዋል። የሰው ፈቃድ እየታደሰ ወደ እውነተኛው ነጻነት ይመለሳል። እግዚአብሔር ሰው በነጻ ምርጫው ወደ መልካም ምግባርና ቅድስና እንዲያዘነብል ያደርገዋል። በዚህ ሁኔታ በሰው ለሚገኘው መልካም ነገር ሁሉ ምንጩ የእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ይሆናል። ወንጌልን ለማመን እንኳ የሚያስችለው ይኸው ጸጋ

ነው። ለኃጢአተኛ ጸጋ የተሰጠው ስላመነ ሳይሆን፥ ያምን ዘንድ ነው። ምክንያቱም እምነት ራሱ የእግዚአብሔር ስጦታ ነውና።

*መደምደሚያ።* በፔላጊዩስና በአውግስጢኖስ መካከል ያለው ልዩነት በጣም የሰላ ነበር። ፔላጊዩስ ሰው ነጻ ሆኖ እንደተወለደ፥ የፈቃድንም ጸጋ እንዳልተገፈፈና ወደ ክፉ የሚያዘነብል የውርስ ኃጢአት እንደሌለበት ያምናል። እንደእርሱ እምነት ሰው የእግዚአብሔር ፀጋ ሳያስፈልገው፥ እግዚአብሔርን ለማገልገል የመምረጥ ችሎታ አለው። አውግስጢኖስ እንደሚያምነው ግን፥ የአዳም ኃጢአት ወደ መላው የሰው ዘር ተላልፏል። ሰው ሁሉ በኃጢአት ተበክሏል። ፈቃዱም ወደ ክፉ ያዘነብላል። ሰውን የሚያድነው የእግዚአብሔር ጸጋ ጣልቃ ገብነት ብቻ ነው። ሰው መልካሙን የማድረግ ነፃ ምርጫ አልነበረውም። ደኅንነት ማለት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚያደርገው መተባበር ሳይሆን፥ ለደኅንነቱ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ መደገፉ ነው።

| ፔላጊዩስ እና አውግስጢኖስ ስለ ኃጢአት ያላቸው አመለካከት | | |
|---|---|---|
| *የማነጻጸሪያ ነጥቦች* | *ፔላጊዩስ* | *አውግስጢኖስ* |
| የውድቀት ውጤት | አዳምን ብቻ በክሏል | መላውን የሰው ዘር በክሏል |
| የውርስ ኃጢአት | የለም | አለ |
| ሰው በልደቱ ግዜ | ነፃ ሆኖ ይወለዳል | ከኃጢአት ዝንባሌ ጋር ይወለዳል |
| የሰው ፈቃድ | ነፃ ነው | ለኃጢአት ተገዢ ነው |
| የሁለንተናዊ ኃጢአት መነሻ | በመጥፎ ምሳሌዎች ሳቢያ የሚመጣ ነው | ከሰው የኃጢአተኝነት ተፈጥሮ የሚመነጭ፤ ሰው "ኃጢአትን አለማድረግ አይቻለውም" |
| በደኅንነት ወደ እግዚአብሔር መመለስ | ያለ እግዚአብሔር ጸጋ የሚቻል ነው | በእግዚአብሔር ጸጋ አማካይነት ብቻ የሚቻል ነው |

ፔላጊዩስ በመጨረሻ በ415 ዓ.ም. በኢየሩሳሌሙ ጉባኤ በኑፋቄነት ተወነጀለ። በ416 ዓ.ም. ደግሞ በርሱ የተሰየመው ፔላጊዩሳዊነት በካርታጎና በሚሌቭ [Mileve] ጉባኤዎች፥ እንዲሁም በ431 ዓ.ም. በኤፌሶኑ ጉባኤ በኑፋቄነት ተወገዘ።

ከዚህ በኋላ የተፈጠረው መጥፎ አጋጣሚ፥ አስታራቂ መሰል አቋም ያለው ከፊል ፔላጊዩሳዊነት መመሥረቱ ነው። የዚህ አቋም

ተከታዮች፥ የእግዚአብሔር ጸጋም ሆነ የሰው ነጻ ፈቃድ፥ በደኅንነት ውስጥ አስፈላጊ ናቸው ይላሉ። ሰው ለደኅንነቱ ከእግዚአብሔር ጋር ሊተባበር ይችላል፥ ምክንያቱም የሰው ፈቃድ በውድቀት ጊዜ ተዳከመ እንጂ ከፋኛ አልተጎዳም ይላሉ። ይህ ከፊል ፔላጊዩሳዊነት በመጨረሻ በሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ተንሰራፋ።

# ጥንታዊው አስተምህሮ ደኅንነት

## *ሥርየትና ደኅንነት*

ሐዋርያት አባቶች የክርስቶስን የምትክ መሥዋዕትነት ያስተማሩ ሲሆን፥ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃልንም አጠንክረው ይዘዋል። ነገር ግን ስለ ክርስቶስ መሥዋዕትነት ጉዳይ በዝርዝር በመግለጥ በጥልቀት አላብራሩም። በመሆኑም ስለ ሥርየት የሰጡትን መግለጫ ልብ ማለቱ ተገቢ ነው። ቀሌምንጦስ የተባለው መንፈሳዊ መምህር የኢየሱስ ክርስቶስ ደም በአብ ዘንድ ክቡር እንደሆነ ሲጠቅስ፥ "ለደኅንነታችን የፈሰሰ ስለሆነ ለዓለም ሁሉ የንስሐን ጸጋ አስገኝቷል" ብሏል። ይህ አገላለጥ ሰው ለራሱ ደኅንነት አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚል ይመስላል። ("የንስሐ ጸጋ" የሚለውና የፈሰሰው ደም ውጤት ለየብቻ እንደሆኑ ያሳያል።) ከዚያም ሌላ፥ ወሰን የሌለውን ሥርየት ("ለዓለም ሁሉ") በማለት ያመለክታል። ቀሌምንጦስ በተጨማሪ፥ የክርስቶስ ደም ላመኑ ሁሉ ሥርየትን እንደሚሰጥ ጠቅሷል። አግናጢዮስ የተባለው ሰውም ተመሳሳይ መግለጫ ሰጥቷል። ሌሎች ተመሳሳይ መግለጫዎችም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ለደኅንነት ወሳኝ መሆኑን ያመለክታሉ። ፖሊካርፕ የተባለው ጸሐፊ፥ የክርስቶስን ለሰው ልጆች በምትክነት መሞት ሲገልጥ፥ "ክርስቶስ ኃጢአታችንን በገዛ ሰውነቱ በመስቀል ላይ ተሸከመው" ይላል።

አትናቴዎስ ደግሞ፥ ይህ የክርስቶስ የምትክነት ሞት ያረካው የእግዚአብሔርን ቅድስናና ፍትሕ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን እውነት ነው ብሎ አስተምሯል። አውግስጢኖስ ደግሞ፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት የእግዚአብሔርን ቁጣ ያገደና ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ያስታረቀ መሆኑን ገልጧል። ይሁን እንጂ የዚህ ሰው የሥርየት አስተምህሮ በደንብ የተቀናበረ አልነበረም።

## *የደኅንነት አፈጻጸም*

ሐዋርያት አባቶች ደኅንነትን ለማግኘት የክርስቶስ ሞት አስፈላጊ መሆኑን ቢገልጡም፥ ሥራ የደኅንነት ማግኛ ሌላ ክፍል እንደሆነም

አስተምረዋል። ቀሌምንጦስ መታዘዝ፥ ለደኅንነት አስፈላጊ መሆኑን በአጽንኦት ገልጧል። ምሳሌም ሲሰጥ፥ ሔኖክን፥ ኖህን አብርሃምንና ሎጥን ጠቅሷል። ረአብም "በእምነት በማስተናገዷ" ድናለች ካለ በኋላ፥ ደኅንነት የሚገለጠው "በቅድስናና በጽድቅ ጎዳና በማለፍ እንዲሁም በጥምቀት ነው" ብሏል። የአብን ፈቃድ መፈጸም፥ ሥጋን ማንጻት፥ የጌታን ትእዛዛት መጠበቅ፥ እርስ በእርስ መዋደድ፥ ክፉ ምኞትን መቃወምና ጽድቅን መለማመድ ተገቢ እንደሆኑ አስተምሯል። ሰው ደኅንነትን ለማግኘት በእግዚአብሔር ሥራ መሣተፍ (መተባበር) አለበት፥ የሚለው አመለካከት በቀጣዮቹ ዓመታት ሲሠራበት ቆይቷል። ጥምቀት የኃጢአት ሥርየት ያስገኛል፥ የሚለው አመለካከትና፥ ቀስ በቀስም የአንዳንድ ክርስቲያኖች ሥቃይና ሰማዕትነት ለሌሎች የኃጢአት ሥርየት ይሆናል የሚለው እምነት ቋሚ ሆነ።

እንደ ፔላጊዩስ ያሉ ሰዎች ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት አፈንግጠው ደኅንነት ሕግን በመጠበቅ ይገኛል ይሉ ጀመር። የኖስቲካዊ መምህራንም፥ ራስን ከቁስ አካላዊው ዓለም ብክለት በማራቅ ደኅንነት ሊገኝ ይችላል አሉ። በምሳሌ ፈቺነቱ የሚታወቀው ሰው አርጌንስ [Origen] ደግሞ፥ ሌላው ቀርቶ ቀስ በቀስ ሁሉ፥ አጋንንት እንኳ ሳይቀሩ፥ ለትምህርት የሚሆናቸውን ቅጣት ከተቀበሉ በኋላ ይድናሉ ብሎ አስተማረ።

# ጥንታዊው አስተምህሮ ቤተ ክርስቲያን

## *ጥምቀት*

ዲዳኬ ['Didache'/የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ትምህርት]፥ ሰው በሥላሴ ስም መጠመቅ፥ እንዳለበትና ከጥምቀት በፊት ተጠማቂውም ሆነ አጥማቂው መጾም እንዳለባቸው ያዛል።

በጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን የጥምቀት ሥርዓት ከፍተኛ ሥፍራን የያዘ ስለነበር፥ ከዚህ በመነሣት ብዙዎች በጥምቀት ስለሚገኝ ዳግም ልደት አስተማሩ። ጁስቲን ማርቲር በመባል የሚታወቀው ሰው፥ የኃጢአትን ሥርየት ለማግኘት፥ በጥምቀት ጊዜ ለተጠማቂው በአብ ስም መማጠን ያስፈልጋል፥ በማለት አስተምሯል። ተጠማቂው ከጥምቀት በኋላ ኃጢአትን ሊያደርግ አይገባውም፥ የሚሠራቸው አንዳንድ ኃጢአቶችም ይቅርታ እንደማይደረግላቸው ይቆጠር ነበር። ምንም እንኳ ይህ አሳብ በሐዋርያት አባቶች ዘንድ አጽንኦት ባይሰጠው፥ በኋለኞቹ ዓመታት ግን ተቀባይነቱ ጨምሯል። ለምሳሌ አውግስጢኖስ የውርስ ኃጢአትና

ከጥምቀት በፊት የተፈጸመ ኃጢአት፥ በጥምቀት ይታጠባል በማለት አስተማረ። ለዚህ ነበር የሕጻናትን ጥምቀት የደገፈው። ይሁን እንጂ፥ አዋቂዎች ጥምቀትን ለመቀበል ንስሐና እምነት እንደሚያስፈልጋቸው ገልጧል። ኤሬኔዎስ [Irenaeus] እና አርጌንስ የሕጻናት ጥምቀት የሚጠቅም መሆኑን ሲያረጋግጡ፥ ተርቱሊያን የተባለው ሰው ግን ተቃውሟል።

የጥምቀት አፈጻጸም ሥርዓት በሐዋርያት አባቶች ግልጥ ትምህርት አልተሰጠበትም። በዲዳኬ ውስጥ ግን በጥምቀት ጊዜ የውኃ መርጨትና ከላይ የማፍሰስን ሥርዓት እንደ አማራጭ ይፈቅዳል። በጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን የነበረው ልምድ ግን በማዘፈቅ ማጥመቅ ነበር።

## የጌታ እራት

አግናጢዮስ ወደ ኤፌሶን በጻፈው መልእክት ላይ የጌታን እራት፥ "የሞት ማርከሻ፥ የሕይወት መድኃኒት እና ከክርስቶስ ጋር ለዘላለም እንድንኖር የሚያደርገን ነው" ይላል። በዲዳኬ ላይም ስለ ጌታ እራት አወሳሰድ መመሪያ ተሰጥቷል። የጌታን እራት ከመውሰድ በፊትና ከወሰዱ በኋላም ስለሚኖረው ጸሎት ተገልጧል። የጌታ እራትን ለመካፈል ጥምቀት አንደኛው መለኪያ ሆኗል። ጁስቲን ማርቲር ሲያስተምር "ይህ በጸሎት ቃል የተቀደሰውና ከእርሱ (ከጌታ) የሚመጣው፥ የእኛም ሥጋና ደም ተመግቦት የሚለወጥበት ምግብ በሥጋ የተገለጠው የኢየሱስ ሥጋወደሙ ነው" ብሏል። በጌታ እራት ጊዜ አማኙ የሚወስደው ኅብስትና ወይን በቀጥታ የጌታ ሥጋና ደም ይሆናል፥ የሚለው የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ [Transubstantiation/ትራንሰብስታንሺዬሽን] የተጸነሰበት አሳብም ይኸው ነው።

የቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች ከጌታ እራት በፊት በግሪከኛ 'አጋፔ' የሚባለውን የፍቅር ግብዣ ይለማመዱ ነበር። ይህም ገበታው በጳጳሱ እየተባረከ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የምስጋና ስጦታ እንደሆነ በመቁጠር ይከናወን የነበረ ነው። በመሆኑም ሥርዓቱ የምግብ ምስጋና ወይም መሥዋዕት በመባል ይታወቅ ጀመር። በቅስና አገልግሎት ጊዜ፥ ቄስ የክርስቶስ ምትክ በመሆን የጌታን ሥጋና ደም ለኃጢአት የሚሆን መሥዋዕት አድርጎ ያቀርብ ነበር። የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የቅዳሴ ሥርዓት አጀማመርም በዚህ የጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን የመሥዋዕት አቀራረብ ሥርዓት ላይ የተመረኮዘ እንደሆነ በግልጥ ይታወቃል። አውግስጢኖስ ምንም እንኳ ይህን ሥርዓት እንደ መታሰቢያ አድርጎ ቢቀበለው፥ አማኙ የሚወስደው ኅብስትና የወይን ጠጅ በቀጥታ የክርስቶስ ሥጋና ደም ይሆናል ብሎ አስተምሯል።

# ጥንታዊው የሥነ-ፍጻሜ አመለካከት

ከ130-140 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ፥ ፓፒየስ የተባለው ሰው፥ ስለ ሺህ ዓመቱ የክርስቶስ መንግሥት የዳበረ መግለጫ ሰጥቷል። ኤሬኔዎስ ፓፒየስ፥ "ይህ መንግሥት ጻድቃን ከሞት የሚነሡበትና የሚነግሡበት ሲሆን፥ ተፈጥሮም ታድሶና ከእስራት ነጻ ሆኖ፥ ለምግብ የሚሆነውን ማንኛውንም ፍሬ የሚሰጥበት ወቅት ነው" በማለት የተናገረውን አመልክቷል። ጌታ ስለዚህ መንግሥት ያስተማረውን ፓፒየስ ሲጠቅስ፥ "እያንዳንዱ አሥር ሺህ ቅርንጫፎች ያሉት ወይን ይበቅላል... አንዲት የስንዴ ቅንጣት አሥር ሺህ ዘለላ ታፈራለች... ለምለሙ ሣርና እንስሳቶችም ሁሉ እንዲሁ ከዚህ የምድር ፍሬ በመጠቀም በሰላምና በስምምነት በሁሉም ነገር ለሰው በመገዛት ይኖራሉ" ብሏል። ፎቲየስ [Photius] የተባለው ሌላ የሥነ-መለኮት ሰው ደግሞ፥ ፓፒየስና ኤሬኔዎስ ሁለቱም፥ "የእግዚአብሔር መንግሥት የምግብ ደስታንም የሚያካትት እንደሆነ" ማስተማራቸውን ጠቅሷል። ስለዚህ እነዚህ መግለጫዎች፥ የሺህ ዓመቱ መንግሥት በትክክል እንደሚመጣ የሚያረጋግጡ ናቸው።

ከቀደሙት ጸሐፊዎች፥ ምናልባት ኤሬኔዎስ ስለ ሺህ ዓመቱ መንግሥት ጠለቅ ያለ መግለጫዎችን ሳይሰጥ አልቀረም። በትንቢቶች መካከል ያሉትን ልዩነቶች በማሳየት፥ ጻድቃን አስቀድመው አዲሱን ሰማይና አዲስ ምድር ለመረከብ እንዲሁም ለመንገሥ እንደሚነሡ፥ ከዚህ መንግሥት ቀጥሎም ፍርድ እንደሚሆን አስተምሯል። ኤሬኔዎስ ይህን እምነቱን የመሠረተው ዘፍጥረት 12፡1-3 ውስጥ በተጠቀሰው አብርሃማዊ ኪዳን ላይ ነው። የምድሪቱ ወራሾች አዲሱን የወይን ጠጅ ስለሚጠጡበት "አዲስ ቃል ኪዳንም" ተናግሯል። ጻድቃን በአዲስና ነጻ በሆነ፥ ምግቡም በተትረፈረፈ አዲስ የፍጥረት ሥርዓት ውስጥ ለመንገሥ ከሞት ይነሣሉ ብሏል። ኤሬኔዎስ የሺህ ዓመቱን ዘመን አስመልክቶ ከኢሳይያስ መጽሐፍ ምዕራፍ 11 እና 65ን ጠቅሷል። የኤሬኔዎስ የቅዱሳት መጻሕፍት አጠቃቀም በጊዜው ከነበሩት ሰዎች አጠቃቀም ጠለቅ ያለና የተቀናበረ ነበር።

ጀስቲን ማርቲር፥ ታቲያን [Tatian]፥ ኤሬኔዎስ፥ ተርቱሊያን [Tertullian]፥ ሂፖሊተስ [Hippolytus] እና አቡሊናርዮስ የተባሉትና ሌሎችም የሥነ-መለኮት ሰዎች የሁለተኛው ምዕተ ዓመት ቅድመ-ሺህ ዓመታውያን [Pre-millennialists]* እንደነበሩ ታውቋል። አልቦ-ሺህ ዓመታዊነት [Amillennialism]* ግብፅ እስክንድርያ ውስጥ ከነበረው የቅዱሳት መጻሕፍት ተምሳሌት አፈታት ጥበብ ጋር የሚያያዝ ሲሆን፥

* በዚህ ርእስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት አባሪ አንድን ይመልከቱ።

እንደ ቀሌምንጦስ፥ አርጌንስና ዲዮናስዮስ [Dionysius] ያሉ ሰዎች በዚህ ክፍል ይመደባሉ። አውግስጢኖስ ይህን ዘመን ቤተ ክርስቲያንና ዓለም የሚፋጩበት ነው ብሎ በማስተማሩ፥ ምናልባት እምነቱን በግልጥ ያሰፈረ የመጀመሪያው አልቦ-ሺህ ዓመታዊ ሳይሆን አይቀርም። አውግስጢኖስ አልቦ-ሺህ ዓመታዊነትን አቋም የያዘበት ምክንያት ልብ ሊባል ይገባል። የሺህ ዓመት መንግሥት እምነት ያላቸው ክርስቲያኖች፥ መጪውን መንግሥት በሥጋዊ መልክ እንዳዩት ተገንዝቧል። ከዚህ የተነሣ የሺህ ዓመት መንግሥት አለ የሚለውን አቋም ተወ።

# - 3 -

# የመካከለኛው ዘመን ሥነ-መለኮት

መካከለኛው ዘመን በመባል የሚታወቀው ጊዜ፥ ቀዳማዊ ጎርጎርዮስ የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ሆኖ ከተሰየመበት ከ590 ዓ.ም. ጀምሮ፥ ማርቲን ሉተር ፕሮቴስታንታዊውን ተሐድሶ እስካቀጣጠለበት እስከ 1517 ዓ.ም. ድረስ ያለውን ዘመን ያጠቃልላል። ቀዳማዊ ጎርጎርዮስ [Gregory I] አውግስጢኖስ የተባለው የሥነ-መለኮት ሰው ትጉህ ተማሪ ከመሆኑም በላይ፥ የአውግስጢኖስን አስተምህሮ በሚገባ እየተረጎመ ብዙ ጽፏል።

ከ500-1500 ዓ.ም. ድረስ የነበረው ዘመን ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ አብዛኛውን ጊዜ በአውሮፓ ታሪክ “የጨለማው ዘመን” ተብሎ ይጠራል። የዚህ ምክንያቱ ቤተ ክርስቲያን በልዩ ልዩ የስሕተት አሠራር ውስጥ የገባችው በዚህ ዘመን በመሆኑ ነው። ይህ ሁኔታ ነበር ቤተ ክርስቲያንን በማርቲን ሉተር አማካይነት ወደ ዘመነ-ተሐድሶ እንድታመራ ያስገደዳት። ሉተር ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ሁኔታዋ እንድትጸዳና ወደ ትክክለኛው አስተምህሮ እንድትመለስ ከፍተኛ ተጋድሎ አድርጓል።

የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ የተስፋፋው በመካከለኛው ዘመን ነው። ጠቅለል ባለ አነጋገር ቤተ ክርስቲያኒቱ ከፊል-ፔላጊዩሳዊ አቋም በመያዝ የሰው ልጅ መንፈሳዊ አቅም እንዳጣ እንጂ፥ መንፈሳዊ ሞት እንደሞተ መታሰብ የለበትም ትላለች። ያም ሆነ ይህ አሁንም ቢሆን ሰው ደኅንነትን ለማግኘት ከእግዚአብሔር ጋር መተባበር ይችላል ትላለች። በመካከለኛው ዘመን፥ አያሌ አዳዲስ ትምህርቶች ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ብቅ ብቅ ብለዋል። ከእነዚህም፥ “ፐርጋቶሪ” [Purgatory]፥* ለማርያምና ለቅዱሳን መጸለይ (እንዲያማልዱ)፥ የቅዳሴ ሥነ-ሥርዓት፥ በጌታ እራት ሥርዓት ጊዜ ኅብስቱና ወይኑ ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደምነት ይለወጣሉ፥ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

---

* በሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት መሠረት፥ አማኞች ከሞቱ በኋላ ሙሉ ይቅርታ ስላልተደረገለት ኃጢአታቸው የሚሠቃዩበትና መንግሥተ ሰማይ ለመግባት የሚጠብቁበት ቦታ ነው።

# በመካከለኛው ዘመን የነበሩ ክርክሮች

## *የኢኮኖላትሪያ [Iconoclastic] ክርክር*

"ኢኮኖላትሪያ" የሚለው ስያሜ፥ 'ኢኮን' እና 'ክላን' ከሚሉ ሁለት የግሪክ ቃላት የመጣ ነው። በግሪክኛ 'ኢኮን' ማለት "ምስል" ወይም "ቅርጽ" ማለት ሲሆን፥ 'ክላን' ማለት ደግሞ "መስበር" ማለት ነው። ከመጀመሪያው የግሪክ ቃል የተገኘውና፥ "አይኮን" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል፥ ሃይማኖታዊ ምስልን ወይም ቅርጽን ያመለክታል። እንግዲህ አንድ ሰው "አይኮኖክላስት" ነው ሲባል፥ ምስሎችን የማውደም ንቅናቄ አቀንቃኝ ነው ማለት ነው። ወደ ሦስተኛው ምዕተ ዓመት ማብቂያ ግድም የቤተ ክርስቲያን ሰዎች የምስል አምልኮን መለማመድ ጀመሩ። ይህም ልምምድ በተከታዮቹ ምዕተ ዓመታት ውስጥ ቀስ በቀስ እያደገ ሄደ። በተለይ የምሥራቋ ቤተ ክርስቲያን ከአረማዊ አምልኮ የተነሣ በዚህ ልምምድ ውስጥ ተዘፍቃ ነበር። የምዕራቧ ቤተ ክርስቲያንም ከዚህ አልራቀችም። ማንበብ የማይችሉ ሰዎችን በጸሎታቸው ያግዟቸዋል በማለት የማርያም፥ የክርስቶስ፥ የሐዋርያትና የሌሎችም ቅዱሳን ምስሎች በብዛት በአገልግሎት ላይ ይውሉ ነበር። ምንም እንኳ ቤተ ክርስቲያን፥ ምስሎች መከበር እንጂ መመለክ የለባቸውም ብላ ብታስተምር፥ ያልተማሩ ሰዎች ግን ምስሎችን ያመልኩ እንደነበር ምንም ጥርጥር የለውም።

ታላቁ ባስልዮስ [Basil the Great] እንዳመለከተው፥ "ለተቀረፁ ምስሎች የሚሰጥ ማንኛውም አክብሮት ውሎ ሲያድር ወደ አምላክ ምሳሌነት ሊለወጥ ይችላል" ብሏል። እንዲህ ያለው ልምምድ የምስል አምልኮን ያበረታታል። ለምስሎች የሚሰጠውን አክብሮት የሚደግፉ ሰዎች እንደሚሉት፥ ምስሎች፥ "ቤተ ክርስቲያንን ያስውባሉ፥ የቀድሞ ትውስታን ይቀሰቅሳሉ፥ ላልተማሩ ሰዎችም የቅዱሳት መጻሕፍትን ቦታ ይተካሉ።" ይህ በምስል አምልኮ የመወዛገብ ጉዳይ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰው፥ ሊዮ [Leo] የተባለ ንጉሥ ለምስል የሚደረገውን ማናቸውንም አክብሮት በከለከለበት በ726 ዓ.ም. ነው። ጎርጎርዮስ ሁለተኛና ጎርጎርዮስ ሦስተኛ በመባል የሚታወቁት ሊቃነ ጳጳሳት፥ የደማስቆው ዮሐንስ ከተባለ ሰው ጋር በማበር፥ ለተቀረፀ ምስል የሚሰጥ አክብሮት መቀጠል አለበት በማለት ተከራክረዋል። ዮሐንስ እንዲያውም ምስሎች እንደ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሊታዩ የሚገባቸውና፥ ልዩ ጸጋንም ሊያጎናጽፉ የሚችሉ ናቸው በማለት አስተምሯል። ይህ ሰው እግዚአብሔርን በማምለክና ምስልን በማክበር መካከል ሊኖር የሚገባውን ግልጥ ልዩነትም አመልክቷል። በ787 ዓ.ም. አንድ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ኒቅያ ውስጥ በመገናኘት የምስሎችን

አስፈላጊነት ከደገፈ በኋላ የክርስቶስና የቅዱሳን ምስሎች፥ "ልባዊ ፍቅርና አክብሮት" ሊሰጣቸው ይገባል በማለት አጽድቋል። ከዚያ ወዲህ የምስል አምልኮ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ዓይነተኛ ጉዳይ ሆነ። በ843 ዓ.ም. ግን የምሥራቋ ቤተ ክርስቲያን ቅርፃቅርፆችን ማለት ከደንጊያ፥ ከብረትና ከእንጨት የተቀረፁትን በማስወገድ ሁኔታው በሥዕል ወይም በምስሎች ብቻ እንዲወሰን አደረገች።

## የ'ፊሎክዌ' [Filioque] ክርክር

በግሪክኛ 'ፊሎክዌ' ማለት፥ "እንዲሁም ወልድ" ማለት ሲሆን፥ "መንፈስ ቅዱስን በጰንጠቆስጤ (የሐዋርያት ሥራ ም. 2) የላከው ማን ነው?" ከሚለው ጥያቄ ጋር የተዛመደ ነው። መንፈስ ቅዱስን የላከው አብ ብቻ፥ ወይስ አብም ወልድም ነበር? ከታሪክ እንደምንረዳው፥ ይህ አከራካሪ የማይመስል ጉዳይ ነው በምሥራቅና በምዕራብ አብያተ ክርስቲያን መካከል አቢይ ልዩነትን የፈጠረው። የግሪክ (የምሥራቅ) ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስን "ነጠላ ሥርጸት (ውፅአት)" [single procession] ይህም ማለት መንፈስ ቅዱስን የሚልከው አብ ብቻ ነው በማለት ታስተምራለች። የሮም (የምዕራብ) ቤተ ክርስቲያን ደግሞ፥ በዮሐንስ 15፥26 ወልድ በባሕርይ (ወይም በመለኮት) ከአብ ጋር አንድ ነው የሚለውን መሠረት በማድረግ የመንፈስ ቅዱስን "ድርብ ወይም ጥንድ ውፅአት (ሥርጸት)" [double procession] ታስተምራለች። እንደ ሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን እምነት፥ መንፈስ ቅዱስን የላኩት አብና ወልድ ነበሩ። በ589 ዓ.ም. በቶሌዶ [Toledo] ጉባኤ ላይ "እንዲሁም ልጅ" የተባለው ሐረግ በኒቅያ የሃይማኖት መግለጫ ላይ ተጨመረ። የምሥራቋ ቤተ ክርስቲያን ግን ይህን አስተምህሮ አልቀበልም በማለቷ ሁኔታው እየከረረ ሄደና፥ በ1054 ዓ.ም. በምሥራቅና በምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ቋሚ ልዩነት ተፈጠረ።

## የአስቀድሞ መወሰን አስተምህሮ [Predestination] ክርክር

የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን፥ ከፊል-ፔላጊዩሳዊውን ፈለግ በመከተሉ ጸንታ በመቀጠሏ፥ ጎትሻክ [Gottschalk] የተባለ መነኩሴ በዘጠነኛው ምዕተ ዓመት ላይ ቤተ ክርስቲያኒቱን ወደ አውግስጢኖሳዊ የአስቀድሞ መወሰን አስተምህሮ ለመመለስ ሙከራ እንዲያደርግ አነሣሣው። ጎትሻክ፥ እግዚአብሔር በዘላለማዊ ድንጋጌው መሠረት ሁሉንም ነገር አስቀድሞ ወስኗል፥ በሚለው አስተምህሮ ላይ በመመሥረት፥ አውግስጢኖሳዊውን አስተምህሮ በብርቱ ደገፉል። ጎትሻክ፥ ሰዎች ለእግዚአብሔር ጥሪ የሚሰጡትን መንፈሳዊ መልስ እግዚአብሔር አስቀድሞ ስለሚያውቅ ዕጣቸውን ይወስናል የሚለውን

የአስቀድሞ መወሰን አስተምህሮ ተቃውሟል። ከዚህም በመነሣት ሁለት ዓይነት የአስቀድሞ መወሰን ሁኔታዎች እንዳሉ አስተማረ። በዚህ አባባል መሠረት፥ አንዳንዶች ለደኅንነት፥ ሌሎች ደግሞ ለዘላለም ኩነኔ ተመድበዋል። በተቃራኒው ደግሞ ሌሎች በእግዚአብሔር ቅድመ ውሳኔ ውስጥ ኃጢአት ጨርሶ የለም! እግዚአብሔር አስቀድሞ የወሰነው የኃጢአትን ቅጣት ብቻ ነው ብለዋል። በመሆኑም እግዚአብሔር አንዳንዶችን ለዘላለም ኩነኔ መድቧቸዋል፥ የሚለው አመለካከት እውነት ሊሆን አይችልም። ጎትሻክ፥ ደኅንነት የሚገኘው በጸጋ እንጂ በሥራ አይደለም የሚለውን አሳብ በጽኑ ደግፏል።

ጎትሻክ በዚህ አባባሉ ጽኑ ተቃውሞ ደርሶበታል። ምክንያቱም በትምህርቱ ውስጥ ለደኅንነት ያበቃሉ በሚባሉ ነገሮች ላይ ማለትም ለምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንና ለበጎ ሥራ፥ እንዲሁም ለሌሎችም የመካከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮዎች ጨርሶ ቦታ አልሰጣቸውም። ስለዚህም በ848 ዓ.ም. ማንዝ [Mainz] በተባለው ሥፍራ በተካሄደው ጉባኤ ተወገዘ፥ ተገረፈ፥ ለዕድሜ ልክም ታሰረ። ይህ ሁሉ ሆኖ አሳቡን ሳያጥፍ በ869 ዓ.ም. ሞተ።

## *የጌታ እራትን አስመልክቶ የነበረ ክርክር*

በ831 ዓ.ም. በፈረንሳይ አገር፥ ኮርቢ [Corbie] በተባለ ገዳም ውስጥ ይኖር የነበረ ራድበርተስ [Radbertus] የተባለ መነኩሴ "ስለ ጌታ ሥጋና ደም" በሚል ርእስ አንድ መጣጥፍ አቀረበ። በዚህ ጽሑፉ፥ በጌታ እራት ሥርዓት ጊዜ ኅብስቱና ወይኑ ወደ ጌታ ሥጋና ደምነት ይለወጣል በማለት አስተምሯል። ራድበርተስ እንዳስተማረው አንድ ካህን "ይህ ሥጋዬ ነው... ይህም ደሜ ነው" የሚለውን የክርስቶስ ቃል ሲናገር፥ አንድ ተአምር ይፈጠራል። ይኸውም ኅብስቱና ወይኑ ወዲያውኑ ወደ እውነተኛው የክርስቶስ ሥጋና ደም ይለወጣሉ። (ይህም በእንግሊዝኛ "Transubstantiation"/ ትራንስብስታንሺዬሽን ይባላል።) ምንም እንኳ የኅብስቱና የወይኑ ውጫዊ ገጽታ ማለት ቀለሙ፥ ቅርፁና ጣዕሙ እንዳለ ቢሆን፥ በውስጡ ግን አንድ ተአምር ይፈጠራል። ራድበርተስ ለአስተምህሮው መሠረት ያደረገው፥ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6 ላይ የተጠቀሰውንና "የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ... የሰው ልጅ የሆነውን ሥጋ ካልበላችሁ፥ ደሙንም ካልጠጣችሁ ሕይወት የላችሁም" በማለት ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የመጨረሻውን እራት በበላ ጊዜ የተናገረውን ቃል ሲሆን፥ ቃሉን እንዳለ ወይም በቀጥታ ነው የተረጎመው። ራድበርተስ እንደሚለው፥ ይህ ተአምር ጥቅም የሚኖረው፥ በእምነት ሥርዓቱ ተካፋይ ለሚሆን አማኝ ብቻ ነው። ለማያምን ሰው ግን አንዳች ፋይዳ የለውም።

ይህ አመለካከት ገና ከመነሻው ተቃውሞ ቢገጥመውም፥ በ13ኛው ምዕተ ዓመት ላይ ግን የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በይፋ ተቀብላዋለች።

# የመካከለኛው ዘመን ሊቃዊነት

ሊቃዊነት የሚለው ቃል በአሥራ አንደኛውና በአሥራ ሁለተኛው ምዕተ ዓመት ላይ "እስኮሌ" ተብለው ለሚጠሩ የገዳም ትምህርት ቤቶች የተሰጠ ስያሜ ነው።

ሊቃውንት በአዕምሮ በማመዛዘን የክርስትናን እምነት ለመተንተንና ለመከላከል በከፍተኛ ደረጃ መማር የጀመሩት በእነዚህ ገዳማት ውስጥ ነበር። ሊቃውንቱ አዲስ እውነትን ፈልፍለው ለማውጣት ሳይሆን፥ የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮዎች በአመክንዮአዊ [reason] መንገድ ለመመከት ነው የሞከሩት። "ሥነ-መለኮት መታየት ያለበት ከፍልስፍና አንጻር እንጂ፥ ከቅዱሳት መጻሕፍት አንጻር መሆን የለበትም" የሚል አመለካከት ነበራቸው።

ሊቃዊ አስተሳሰብ በሰፊው መናኘት የጀመረው፥ በአሥራ ሁለተኛው ምዕተ ዓመት የአርስጣጣሊስ [Aristotle] ሥራዎች ከግሪክ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች በመተርጎማቸው ነው። አንዳንድ ሊቃውንት ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመረዳት የአርስጣጣሊስን የአረዳድ ትንታኔ [Deductive Logic] ዘዴ ተከትለዋል። ሦስት ዓይነት የሊቃዊነት ክፍሎች ነበሩ። አንደኛው፥ ፕሌቶ [Plato] የተባለውን ሰው አስተሳሰብ የተከተለው "እውነትነታዊነት" [Realism] እንደሚያስተምረው፥ ሁለንታዊ አሳብ ከተናጠል ነገሮች ተለይቶ ይኖራል። አንሰለም [Anselm] እና በናቬንቱራ [Bonaventura] የተባሉት ምሁራን፥ የእውነታዊነት አሳብ ዋና አቀንቃኞች ነበሩ። ሁለተኛው፥ የአርስጣጣሊስ አስተሳሰብ ተከታዮች የሆኑት "ለዘብተኞች"፥ የእውነታዊነት ሁለንተናዊ አሳብ ለምሳሌ እውነትና መልካምነት ተጨባጭ ህልውና አላቸው፤ ሆኖም በህልውናቸው ከተናጠል ነገሮች የተለዩ አይደሉም የሚሉት ነው። ከአበላርድ [Abelard] እና ከሊቃውያን መካከል ታላቅ ቦታ የሚሰጠው ቶማስ አኩናስ የዚህ አመለካከት ተጠሪዎች ነበሩ። ሦስተኛው፥ የእውነታዊነት ተቃራኒ የሆነውና በስም ብቻ መወከልን (ስማዊነትን) አሳብ የሚያቀነቅኑት [Nominalists]፥ ከአእምሮ ውጭ ህልውና የለም በማለት ያስተማሩት ነው። አከም የተባለው ምሁር ነበር የዚህ አመለካከት ተጠሪ። ስማውያን ከሰብአዊ ልምምድ ውጭ የሆነውን ማንኛውንም ነገር ጨርሶ ስለማይቀበሉ፥ ስለ ሥላሴ የሚሰጠውን አስተምህሮ አያምኑም። የስማዊነት እሳቤ በተከታዮቹ ምዕተ ዓመታት በተግባራዊና ተጨባጭ ግንዛቤ ፍልስፍናዎች ውስጥ ታይቷል።

# የመካከለኛው ዘመን ሥነ-ሰብእነት

[Anthropology]

## አንሰለም

አንሰለም (1033-1109) የተባለው ሰው አስተሳሰብ ስለ ውርስ ወይም መነሻ ኃጢአት ቢያስተምርም፥ "መነሻ" የሚለው ቃል "ተፈጥሮአዊ" ተብሎ ሊጠራ ይችላል፤ ምክንያቱም ቃሉ የሚያመለክተው የሰውን ዘር መጀመሪያ አይደለም የሚለውን አሳብ አትልቶታል። ይህ ቃል የሚያመለክተው፥ በውድቀት ምክንያት በሰዎች ላይ በግል የደረሰውን ሁኔታ ነው። ምክንያቱም የሰዎች ተፈጥሮ ሁሉ በአዳምና በሔዋን ውስጥ ተወክሏል፤ የአዳምና የሔዋንም ኃጢአት ሰዎችን ሁሉ በክሏል። በመሆኑም፥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰው በኃጢአት በተበከለ ተፈጥሮ ዘሩ ሲባዛ ቆይተዋል። ሕፃናትም ቢሆኑ ሰብአዊ ተፈጥሮን ስለሚጋሩ በኃጢአት ተበክለዋል። በአዳም ውስጥ ኃጢአትን ሠርተዋል፤ በመሆኑም በኃጢአት የተበከሉና በደለኞች ናቸው።

አንሰለም እንደሚያስተምረው፥ የሰዎች እውነተኛ ነጻነት በአዳም ኃጢአት ሳቢያ ቢጠፋም፥ "የፍቃደ ሰብእ ባሕርይ" ግን ጨርሶ አልተደመሰሰም። ሰው አሁንም ቢሆን ፍቃድ አለው፤ አንሰለም ሰው ውሳኔን የማድረግ ነጻነት አለው የሚለውን ፅንሰ አሳብ ሲቃወም፥ ሰው ውሳኔን ለማድረግ የውዴታ ችሎታ አለው የሚለውን ግን ተቀብሏል። አንሰለም፥ ሰው ሁለቱንም ማለት በጎም ሆነ ክፉ ነገር ለመምረጥ ነጻነት አለው የሚለውን አሳብ አይቀበልም። በርሱ እምነት የሰው ፍቃድ የተሠራው በጎ የሆነውን ነገር እንዲመርጥ ነው።

## ቶማስ አኩናስ

አኩናስ ኃጢአትን አሉታዊ በሆነ፥ ማለት መሠረታዊ ጽድቅ የታጣበት አድርጎ ብቻ ሳይሆን፥ አዎንታዊ በሆነ መንገድም ተርጉሞታል። አሉታዊ በሆነ መንገድ ሲተረጉመው፥ የጽድቅ መታጣት፤ አዎንታዊ በሆነ መንገድ ሲተረጉመው ደግሞ፥ የሥጋ ፍትወት ብሎታል። ይህ ኃጢአታዊ ተፈጥሮ በወላጆች በኩል ለልጆች ተላልፏል። አኩናስ እንደሚለው፥ በሰው ዘር መካከል አንድነት ስላለ፥ የአዳም ኃጢአት በሁሉ ላይ ተላልፏል። ይህ ሰው በግልጥ እንደተናገረው፥ "ከአዳም የተወለዱ እንደ አንድ ሰው ሊቆጠሩ ይችላሉ፤ በመሆኑም ከአዳም የተገኙ ሁሉ የአንድ አካል አባላት ናቸው።" የውርስ ኃጢአት ውጤት ብዙ ነው። ከነዚህ ውስጥ የሰው ፍቃድ

ከእግዚአብሔር ፍቃድ መለየቱ፥ የነፍስ ኃይላት ሥርዓት ማጣትና ለቅጣት መጋለጣቸው ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

አኩናስ የወገነበት ሊቃዊነት ታላላቅ ኃጢአቶች፥ ትዕቢት፥ መጎምጀት የሥጋ አምሮት፥ ቁጣ፥ ሆዳምነት፥ ቅንዓትና ስንፍና መሆናቸውን ተቀብሏል። እነዚህንም ኃጢአቶች ከባድ እና ቀላል በማለት ይከፍሏቸዋል። "ከባድ ኃጢአት" የእግዚአብሔርን ሕግጋት ሆን ብሎ መተላለፍን ሲመለከት፥ ይህ ኃጢአት ሰውን ከእግዚአብሔር የለየው ነው። "ቀላል ኃጢአት" ተብለው የተመደቡት ግን፥ በነገሩ ብዙ ሳያስቡ ከእግዚአብሔር ፍቃድ አፈንግጦ መገኘትን ይመለከታል። ቀላል ኃጢአቶች በጊዜያዊ ቅጣት ይሰረዩ ይሆናል።

## የማርያም ኃጢአት የለሽነት (ቅድስና)

ለማርያም የሚሰጠው ክብር እያደገ ሲመጣ፥ ቤተ ክርስቲያን ማርያም ኃጢአት የለሽ ናት በማለት ታስተምር ጀመር። አከራካሪው ጥያቄ፥ ማርያም የተወለደችው ያለ ኃጢአት ነው ወይስ እሷም እንደማንኛውም ሰው በውርስ ኃጢአት ተበክላ ሳለ፥ ከመወለዷ በፊት ግን ፍጹም ንጹሕ ወይም እንከን የለሽና ኃጢአት የለሽ የመሆን ዕድል አገኘች? የሚለው ነበር። ራድበርተስ የተባለው ሰው፥ ማርያም በማሕፀን ውስጥ ያለ ኃጢአት ነበረች፤ ወደ ዓለምም የመጣችው በኃጢአት ሳትበከል ነው በማለት አስተማረ። በ1140 ዓ.ም. ማርያም ያለምንም ኃጢአት ወይም እንከን ነው የተፀነሰችው የሚለው አስተምህሮ ለመጀመሪያ ጊዜ በግልጥ ሲነገር፥ የክሌርቮው በርናርድ [Bernard of Clairvoux] እና ቶማስ አኩናስ የተባሉት ምሁራን ትምህርቱን በጥብቅ ተቃወሙት። ነገር ግን እምነቱ ቀስ በቀስ ተቀባይነት አገኘና በ1854 ዓ.ም. ትክክለኛ ትምህርት ተባለ።

## መደምደሚያ

የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አመለካከት የሆነው፥ ሥነ-ሰብእነት የተከሰተው በመካከለኛው ዘመን ነበር። ሰው በመጀመሪያ ጽድቅን ያገኘው፥ በልዑል ኃይል አማካይነት ስለሆነ፥ በሥነ-ምግባር ገለልተኛ አልነበረም። በውድቀት ሳቢያ ሉዓላዊ ጽድቅ ቢርቀውም፥ ተፈጥሮአዊ ችሎታውን አላጣም ነበር። ውድቀት በሰው ላይ ያስከተለው ፍጹም ጥፋተኛነት፥ ሳይሆን፥ ምግባራዊ ገለልተኛነትን ነው። ከዚህም የተነሣ ሰው በደኅንነት አማካይነት ከእግዚአብሔር ጋር የመተባበር ብቃትን ሊያገኝ ቻለ። ይህ አመለካከት ከፊል-ፔላጊዩሳዊነት ይባላል።

# የመካከለኛው ዘመን አስተምህሮ ደኅንነት

## ሥርየት

አንሰለም፥ ሰው በኃጢአት ድርጊቱ ምክንያት ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር ነፍጎታል በማለት አስተማረ። እግዚአብሔር ከሁለት አንዱን ማለት፥ ኃጢአትን መቅጣት፥ ወይም ልጁን በመስጠት በኃጢአት ምክንያት የተገፈፈውን ክብሩን ከማስመለስ አንዱን ለመምረጥ ይችል ነበር። በዚሁ መሠረት ሁለተኛውን መረጠና፥ ክርስቶስ በሞቱ አማካይነት የእግዚአብሔርን ክብር አስመለሰ። ክርስቶስ ለዚህ ሥራው ሽልማት ተቀብሏል። ይህንንም ለኃጢአት ማስተሰሪያ አድርጎ ያስተላልፈዋል።

አበላርድ የተባለው ሰው የአንሰለምን ንድፈ አሳብ በመቃረን፥ እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቅር ለማለት የክርስቶስን ሞት አልጠየቀም ብሏል። ይልቁንም በክርስቶስ ሞት አማካይነት ፍቅሩን ገለጠ። እንደ አበላርድ አባባል እግዚአብሔር በክርስቶስ ሞት አማካይነት ከገለጠው ፍቅሩ የተነሣ፥ ኃጢአተኞችን ይቅር ይላቸዋል። ይህ የአበላርድ አመለካከት "የግብረ ገብ ተጽዕኖ" አመለካከት በመባል ይታወቃል።

የክሌርቮው በርናርድ ከላይ የተጠቀሰውን የአበላርድ ንድፈ አሳብ ከተቃወመ በኋላ፥ ቤዛነት ለአማኞች የጸናው በክርስቶስ ሞት እንጂ፥ በክርስቶስ ምሳሌነት አይደለም የሚል አስተያየት አቀረበ። ፒተር ሎምባርድ [Peter Lombard] የተባለው ሰው በበኩሉ፥ የአንሰለምንና የአበላርድን አመለካከቶች አንድ ላይ በማጣመር፥ ክርስቶስ የሞተው ለኃጢአተኞች ነው ብሎ አስተማረ።

እንደ ፒተር ሎምባርድ አስተያየት፥ የክርስቶስ ሞት፥ ኃጢአተኞች እግዚአብሔርን እንዲያፈቅሩትና በዚህም ከኃጢአት እስራት እንዲፈቱ ያደርጋቸዋል።

ቶማስ አኲናስም የአንሰለምንና የአበላርድን አመለካከቶች አስተጋብቷል። አኲናስ ክርስቶስን የሚያየው፥ የሰው ዘር ራስ እንደሆነና ጽድቁን ለሰው ዘር እንዳስተላለፈ አድርጎ ነው። በተጨማሪም ክርስቶስን "በትምህርቱ፥ በሥራውና በሥቃዩ የሰው ዘር መምህርና ምሳሌ ነው። ሥቃዮቹ በተለይ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመግለጥና የሰዎችንም ልብ ለዚህ ፍቅር ለማነሣሣት ችለዋል" ብሏል።

*መደምደሚያ፡-* መካከለኛው ዘመን የአስተምህሮ ሥርየትን ግንዛቤ በማስፋት ረገድ ያደረገው ጥረት አነስተኛ ነው።

## የእግዚአብሔር ጸጋ

ምንም እንኳ የመካከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያን ለአውግስጢኖስ አስተምህሮዎች አፍአዊ አምንታ ብትሰጥ፥ ትምህርቷ በእጅጉ የሚጠጋው ግን፥ ከፊል-ፔላጊዩሳዊ ወደተባለው አስተምህሮ ነበር። የሰው ፈቃድ በውድቀት ጊዜ ጨርሶ አልጠፋም፤ ሰው ደኅንነትን ለማግኘት አሁንም ከእግዚአብሔር ጋር የመተባበር አቅም አለው፥ የሚል አስተያየት በጊዜው ሰፍኖ ነበር። በአጠቃላይ ሲታይ ሊቃውንት ጸጋን በተለያየ መንገድ ቢተረጉሙትም፥ ደኅንነትን ለማግኘት ግን ጸጋ ያስፈልጋል የሚል አመለካከት ነበራቸው። ቶማስ አኩናስ፥ ደኅንነትን ለማግኘት ጸጋ መሠረታዊ ነገር መሆኑን አስተማረ። ሰው ያለ እግዚአብሔር ጸጋ ከወደቀበት ኃጢአት ወደ ጽድቅ ለመመለስ እንደማይችልም በግልጥ አስረዳ። "ነጻ ጸጋ" እና "ቅድስናን ሰጭ ጸጋ" በማለትም በሁለቱ መካከል ልዩነትን አበጀ። ነጻ በሆነው ጸጋ ውስጥ እውቀት (እምነትና ማስተዋል)፥ በግብር የሚታዩ ነገሮች (ፈውስ፥ ተአምራትና ትንቢት)፥ የርስ በርስ ግንኙነት (ልሳንና በልሳን የተነገረውን መተርጎም) ተካተዋል። ቅድስናን ሰጭ በሆነው ጸጋ ውስጥ ደግሞ፥ ሠሪ ጸጋንና ተባባሪ ጸጋን አጣምሮ ይዟል። ሠሪ ጸጋ ቀዳሚ ሲሆን፥ ተባባሪ ጸጋ ደግሞ ተከታይ ነው። ቶማስ አኩናስ ተባባሪ ጸጋ የሚለውን አሳብ የሚረዳው፥ ሰው የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመቀበል፥ ከእግዚአብሔር አሠራር ጋር መተባበር አለበት በሚለው መልኩ ነው።

ፒተር ሎምባርድ በበኩሉ በሠሪ ጸጋና በተባባሪ ጸጋ መካከል መሠረታዊ ልዩነት እንዳለ ተናግሯል። ሎምባርድ ሠሪ ጸጋ ብሎ የሚጠራው፥ ሰውን መለወጥና ወደ እግዚአብሔር መመለስ የሚችለውን ጸጋ ሲሆን፥ ተባባሪ ጸጋ (ሠሪ ጸጋን ተከትለው የሚመጡትን ሌሎች ጸጋዎች ሁሉ ያካትታል) በማለት የሚጠራው ደግሞ፥ ሰው የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመቀበል ከእግዚአብሔር ጋር መተባበር እንዳለበት የሚያመለክተውን ጸጋ ነው። ዝንባሌው የሊቃዊነት አመለካከት ቢሆን እንኳ ከፊል-ፔላጊዩሳዊነት ነው።

## እምነትና ሥራዎች

ሊቃውንቱ እምነትን የሚፈርጁት በሁለት ነው። አንደኛው የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ በቃል ማወቅን የሚመለከት ነበር። ሁለተኛው ደግሞ የፍቅር ሥራን የሚያፈራው ሲሆን ደኅንነትና ጽድቅ የሚገኙት ከዚሁ እምነት ነው። ሆኖም ግን ሃይማኖታዊ ሕይወት የሚማከለው፥

በፍቅርና በመልካም ሥራ ላይ እንጂ በእምነት ላይ ብቻ አይደለም። ሊቃውንቱ እንዲህ ያሉበት ምክንያት በእነርሱ አመለካከት የሰው ጽድቅ ከእግዚአብሔር ጋር አዲስ ሕብረት የሚፈጥርለት ሳይሆን፥ መልካም ሥራ መሥራትን ብቻ የሚያስችለው ስለሆነ ነው።

## ጽድቅ

ሊቃውንቱ እንደሚያስተምሩት፥ ጽድቅ የሚገኘው፥ እግዚአብሔር እንደሚሰጠው ፍርድ ሳይሆን፥ እርሱ ቅድስና ሰጭ የሆነውን ጸጋ ለሰዎች እንደሚሰጥ በመተማመንና ከዚያም አሳብ ጋር በመተባበር ነው። በተጓዳኝ፥ ሰው በነጻ ፍቃዱ በንስሐና በእምነት ወደ እግዚአብሔር ይመለሳል። ይሁን እንጂ፥ በሊቃውንቱ አመለካከት ጽድቅ የደኅንነት ዋስትናን አይጨምርም፤ ያ የሚገኝ አይደለም።

# የመካከለኛው ዘመን አስተምህሮ ቤተ ክርስቲያን

## የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች

በመካከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፥ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ለሁለት ዓላማ ይከናወን ነበር። ሥርዓቶቹ ደኅንነትን ለግለሰቦቹ በሚታይ መልክ ሊያስገኙ እና የግለሰቦችን ደኅንነት ከቤተ ክርስቲያን ጋር ሊያስተሳስሩ ይችላሉ በሚል እምነት ነበር የሚከናወኑት። በዚህ ምክንያት የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች ጸጋን ለግለሰቦች በመስጠት ረገድ ዓይነተኛ ምልክት ሆነዋል።

የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች ብዛት አልተወሰነም ነበር። አንዳንዶች ስድስት፥ ሌሎች ሰባት፥ የቀሩት ደግሞ እንዲያውም ወደ አሥራ ሁለት ያደርሷቸዋል። ፒተር ሎምባርድ የተባለው መንፈሳዊ መሪ ሥርዓታቱን ለመጀመሪያ ጊዜ በሰባት እንዲወሰኑ አደረገ። እነርሱም፤ ጥምቀት፥ ሥርዓተ ቁርባን፥ ሥርዓተ ሜሮን [Confirmation]፥ ሥርዓተ ቀንዲል [Extreme unction]፥ ሥርዓተ ንስሐ [Penance]፥ ሥርዓተ ክህነት [Ordination] እና ሥርዓተ ተክሊል [Marriage] ናቸው። እነዚህ ሰባት ሥርዓቶች ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ ተቀባይነት ያገኙት በ1439 ዓ.ም. በፍሎሬንስ ጉባኤ ነው።

የመካከለኛው ዘመን ሥነ-መለኮት አስተምህሮ፥ ሰዎች ደኅንነትንና ጽድቅን የሚያገኙት፥ በእግዚአብሔር ጸጋ ሳይሆን፥ በሥራ ነው የሚል ይመስላል።

| የመካከለኛው ዘመን ቅዱሳት ምስጢራትና መንፈሳዊ ጥቅማቸው | |
|---|---|
| ቅዱስ ምስጢር | ጥቅሙ |
| ሥርዓተ ጥምቀት | ዳግም ልደትና መንፈሳዊ ሕይወትን ይሰጣል |
| ሥርዓተ ሜሮን | መንፈሳዊ ሕይወትን ያጠነክራል |
| ሥርዓተ ቁርባን | መንፈሳዊ ሕይወትን ይመግባል |
| ሥርዓተ ንስሐ * | መንፈሳዊ ሕይወት በኃጢአት ሳቢያ ቢቆሽሽና ቢጠፋ ወደ ቀድሞ ቦታውና ሁኔታው ይመልሰዋል |
| ምስጢረ ቀንዲል | ነፍስን ይፈውሳል፤ አንዳንዴ ሥጋዊ አካልንም ጭምር |
| ሥርዓተ ክህነት | የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ያስገኛል |
| ሥርዓተ ተክሊል | የእግዚአብሔር ቡራኬ በቤተሰብ ላይ፤ ልጆች ይወለዳሉ፤ መንግሥተ ሰማይ በምርጦች ትሞላለች |

* ሥርዓተ-ንስሐ፤ በሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ውስጥ፥ ሁለት ዓይነት ኃጢአቶች አሉ፡- "ቀላል" እና "ከባድ"። ቀላል ኃጢአቶች በደረጃቸው አነስተኛ የሆኑ እና ኃጢአተኛውን ደኅንነቱን እስከ ማጣት የማያደርሱት ናቸው። ለዚህ ዓይነት ኃጢአት፥ እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን በዚህ ምድር ላይ በመሰቃየት ወይም ከሞት በኋላ በፐርጋቶሪ ("የንስሐ ቦታ") ፍርድ ይቀጣዋል። ከባድ ኃጢአቶች ግን ዋና ኃጢአቶች ሲሆኑ፥ ኃጢአተኛውን ደኅንነቱን እስከ ማጣት ያደርሱታል። ለዚህ ዓይነት ከባድ ኃጢአቶች ቤተ ክርስቲያን ያወጣችው ድንጋጌ በሥርዓተ-ንስሐ ውስጥ ይገኛል።

ሥርዓተ-ንስሐ ሶስት ክፍሎች አሉት፡- (1) ኃጢአተኛው በሠራው ኃጢአት ከልቡ መፀፀት፥ (2) ኃጢአቱን ለቄስ መናዘዝ፥ (3) ስለ ኃጢአቱ እግዚአብሔርን የሚያረካ "ክፍያ" ማድረግ ናቸው። ይህ ክፍያ የሚያመለክተው ስለ ኃጢአቱ በዚህ ምድር ባለው የሕይወቱ ዘመን ወይም በፐርጋቶሪ በመሰቃየት የሚቀጣውን ቅጣት ነው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ከዘላለም ቅጣት ነጻ ቢያወጣውም ስለሠራው ኃጢአት ጊዜያዊ የሆነ ቅጣት መክፈል አለበት። ኃጢአተኛው ወይም ሌላ ሰው በኃጢአተኛው ፈንታ በመፆም፥ በመፀለይ፥ የበጎ አድራጎት ሥራን በመሥራት፥ ምፅዋትን በመስጠት እና ይህንን በመሳሰሉ መልካም ድርጊቶች ለኃጢአቱ የሚከፈለውን ቅጣት እንዲቀር ወይም የቅጣቱ መጠን እንዲቀነስ ለማድረግ ይቻላል።

## ጳጳስና

በሊቃዊነት ዘመንና የዚሁ አሳብ ደጋፊዎች በነበሩት ቶማስ አኩናስ፥ እንዲሁም በክሌርቮው በርናርድ አይዟችሁ ባይነት፥ የሮም ጳጳሳት በዓለም ላይ መንፈሳዊ እና ምድራዊ ልዕልና አለን ይሉ ጀመር። ይህ አመለካከት የመነጨው፥ ክርስቶስ ለጴጥሮስ ሥልጣን ሰጥቶታል፥ በሌሎቹ ሐዋርያት ላይም ሾሞታል ከሚለው አመለካከት ነው። በዚሁ መሠረት ጴጥሮስ የመጀመሪያው የሮም ጳጳስ ሆኗል። ይህም ሥልጣን ከእርሱ በኋላ ለሚነሡት የሮም ጳጳሳት ይተላለፋል አሉ።

ግሬሽን [Gratian] የተባለው ጸሐፊ ደግሞ፥ ለሮም ጳጳሳት አለመታዘዝ እግዚአብሔርን እንዳለመታዘዝ ነው ሲል አስተማረ። ቶማስ አኩናስ በበኩሉ፥ የሮሙ ጳጳስ ከሁሉም በላይ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደመሆኑ መጠን፥ ንጹሕ ምግባርና ትምህርት በቤተ ክርስቲያን እንዲሰፍን የማድረግ ከፍተኛ ሥልጣን አለው፤ ሊታመን የሚገባውን ማስተማር ያለበት እርሱ ነው በማለት አስተምሯል። ኢኖሰንት ሦስተኛው (1198-1216 ዓ.ም.) የተባለው የሮም ጳጳስ፥ ጳጳሳት "የክርስቶስ እንደራሴ" ናቸው በማለት ጽኑ ድንጋጌ አወጣ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሮም ጳጳሳት "ቅዱስ" ወይም "ብፁዕ ወቅዱስ" በመባል ይጠሩ ጀመር። ይኸው ኢኖሰንት ሦስተኛ [Innocent III] የተባለ የሮም ጳጳስ፥ መልከ ጼዴቅ የሮም የጳጳሳት ምሳሌ ነው በማለት አስተምሯል። የሮሙ ጳጳስ የመንግሥተ ሰማይን ቁልፍ ይዟል፥ የማሰርም ሆነ የመፍታት ሥልጣን አለው፥ ተብሎ ስለሚታመን፥ ለእርሱ ሥልጣን የማይገዛ ሁሉ እንደ መናፍቅ ይቆጠራል። በዚህ አመለካከት መሠረት ከሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ውጭ ደኅንነት የለም ማለት ነው።

የሮሙ ጳጳስ ሥልጣን ወደ የመንግሥት ሥልጣን ይገባኛልነት ደረጃ ደረሰ። ከላይ የተጠቀሰው የሮም ጳጳስ በግልጥ እንደተናገረው፥ ጴጥሮስ ምድርን ሁሉ የመግዛትን ሥልጣን ከጌታ ተቀብሏል። ስለዚህ ማንኛውም ምድራዊ ባለሥልጣን ለሮም ጳጳሳት መታዘዝ አለበት። የሮም ጳጳሳት ነገሥታትን ከሥልጣን የማውረድ፥ ግብርን የመቀበል፥ ግዛትን የመስጠት፥ ተቃዋሚዎችን የመቅጣትና የአገሪቱን ሕገ መንግሥት የመሻር ሥልጣን ነበራቸው። ጎርጎርዮስ ሰባተኛ [Gregory VII] (1073-1085 ዓ.ም.) የተባለው የሮም ጳጳስ ዓለምን የመግዛትና የማስተዳደር ኃላፊነት እንደነበረበት ገልጦ፥ ይህን ሳያደርግ ቢቀር እግዚአብሔር እንደሚቀጣው ተናግሯል። በ1302 ዓ.ም. ቦኒፌስ ስምንተኛ [Boniface VIII] የተባለው

የሮም ጳጳስ፤ አንድ የሮም ጳጳስ በሁለት ዓለማት ላይ ሥልጣን አለው፥ መንፈሳዊ ሰይፍን፥ እንዲሁም ዓለማዊ ሰይፍን ይቆጣጠራል፥ በማለት ጳጳሳዊ ድንጋጌ አወጣ።

## የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ

ቤተ ክርስቲያንን ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር የማገናኘቷ አዝማሚያ ያደገው በመካከለኛው ዘመን ነው። አስተሳሰቡ ሊመነጭና ሊያድግ የቻለው፥ ከሁለት የተጭበረበሩ መዛግብት ማለት "የቆስጠንጢኖስ ልገሣ" [Donation of Constantine] (በስምንተኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ላይ የተጻፈ) እና "የኢዚዶር ድንጋጌዎች" [Decretals of Isidore] (በዘጠነኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ላይ የተጻፈ) ላይ በመመሥረት ነው። የመጀመሪያው መዝገብ፥ በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ተጽፏል ተብሎ የሚነገር ሲሆን፥ ንጉሡ ቤተ መንግሥቱን፥ ሮምንና ሌሎቹን ከተሞች ለጳጳሱና እርሱን ለሚተኩ ሁሉ መስጠቱን ይጠቁማል። ውሎ ሲያድር ማንኛውም እንቅስቃሴ በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ይሽከረከር ጀመር። ከቤተ ክርስቲያን ጋር የማይዛመዱ ነገሮች ሁሉ እንደ ዓለማዊና እንደ ሥጋዊ ተቆጠሩ። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ራሷ ዓለማዊና ሥጋዊ ሆና ነበር። ምክንያቱም ራሷን እንደ እግዚአብሔር መንግሥት በመቁጠሯ፥ ለሰዎች ደኅንነት ከመጋደል ይልቅ በፖለቲካ ሥራ ተጠመደች።

በመካከለኛው ዘመን፥ ስለ ቤተ ክርስቲያን የነበረው ፅንሰ አሳብ የሚከተሉትን ነገሮች አዳብሯል፦ (1) የሚታየው የቤተ ክርስቲያን ምንነት ጎልቶ ነበር፤ ክርስቶስ በሥጋ ስለተገለጠ፥ ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ ራሷን በግልጥ ታስፋፋለች። ጳጳሳት በዓይን የሚታዩ የጴጥሮስ ምትክ በመሆ ናቸው፥ ፍጹም ሥልጣን አላቸው፤ (2) በአስተማሪዎች (ካህናትን ሁሉና የእነርሱም ራስ የሆነውን ጳጳሱን ጨምሮ) እንዲሁም በሰሚዎች (ካህናትን የሚያከብሩ ታማኞች) መካከል መሠረታዊ ልዩነት አለ፤ (3) ቤተ ክርስቲያን የአካልና (እውነተኛውን እምነት የሚመሰክሩ) የነፍስ (በመለኮታዊ ስጦታና ጸጋ ከክርስቶስ ጋር አንድ የሆኑ) ስብስብ ናት፤ (4) ቤተ ክርስቲያን በካህናት አማካይነት የክርስቶስን ጸጋዎች ታድላለች፤ (5) ቤተ ክርስቲያን "የደኅንነት ተቋምና የሕይወት መርከብ ናት።" እውነተኛውን እምነት ታስተምራለች፥ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አማካይነት ቅድስናን ትሰጣለች፥ ምዕመናንንም በምታወጣቸው ሕግጋት አማካይነት ታስተዳድራለች።

# - 4 -

# የዘመነ ተሐድሶ (የሪፎርሜሽን) ሥነ-መለኮት

## የተሐድሶ መሠረቶች

ተሐድሶ በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ እድገት ላይ ከፍተኛ ለውጥ አስከትሏል። ከተሐድሶ ዘመን በፊት በነበሩት አንድ ሺህ ዓመታት፥ ሰዎች ሊያምኑት የሚገባቸው ነገር በሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ወግና በሮም ጳጳሳት ሥልጣን እስከሚወሰንላቸው ጊዜ ድረስ፥ የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን በየጊዜው ለማደግ ችሎ ነበር። በኋላ ግን ያን ሁሉ፥ ተሐድሶ ለወጠው።

የፕሮቴስታንት ተሐድሶን ያቀጣጠሉ አያሌ ምክንያቶች ነበሩ። አንደኛው ፖለቲካዊ ምክንያት ነው። እስልምና በ1453 ዓ.ም. ቁስጥንጥንያን ድል በማድረጉ፥ ለምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን መውደቅ ምክንያት ሆነ። በዚህ ሳያበቃ ፊቱን ወደ ምዕራብ በመመለስ፥ ለሮሙ ጳጳስ ሥልጣን ሥጋት እየሆነ አውሮፓን አጥለቀለቃት። በሥነ-ጽሑፍ አማካይነትም በሮም ጳጳሳት ላይ ተጽዕኖ ያደርግ ጀመር። ከዚህ ጋር የብሔራዊ መንግሥታትና የነጻ ከተሞች አውሮፓ ውስጥ መፈጠር፥ የሮምን ፖለቲካዊ ሥልጣን ይፈታተነው ጀመር። በጠንካራ የክልል የፖለቲካ መሪዎች አማካይነት የተቀሰቀሰው ብሔራዊ ስሜትም የተሐድሶ እንቅስቃሾችን ረድቷል።

ሁለተኛው ምክንያት፥ "ዘመነ ሬነዛንስ" [Renaissance]* ያመጣው ትምህርት ነው። ዘመነ ሬነዛንስ፥ ሰዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ ጥንታዊ ሥነ-ጽሑፎችን ያጠኑ ዘንድ አእምሯቸውን ከፈተ።

---

* "ሬነዛንስ"። ይህ ቃል የሚያመለክተው በአውሮፓ ታሪክ ውስጥ በግምት ከ1350 እስከ 1650 ዓ.ም. ያለውን ጊዜ ሲሆን፥ የቃሉ ቀጥተኛ ትርጉም "አዲስ ልደት" ማለት ነው። ይህ ታሪካዊ ጊዜ ይህንን ስያሜ ያገኘበት ምክንያት፥ የምሁራን እንዲሁም የሕዝቡ አስተሳሰብና የሚያተኩሩበት አመለካከት በጣም የተለወጠበት ጊዜ ስለነበር ነው። 1. በግለሰብ ሥጋዊ አኗኗር ላይ ማተኮር፥ በቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ አኗኗር ላይ በማተኮር ፈንታ ተተካ። 2. የሰው ሥራን ማውራትና ለሰው ክብርን መስጠት፥ የእግዚአብሔርን ሥራ በማውራትና ለእግዚአብሔር ክብርን በመስጠት ፈንታ ተተካ። 3. የዓለምና በምድር ባሉ ነገሮች ላይ ያለ ፍላጎት፥ በእግዚአብሔርና በመንግሥተ ሰማይ ባሉ ነገሮች ላይ ያለውን ፍላጎት ተካ። 4. መለኮታዊው የእግዚአብሔር መገለጥ በሰው አእምሮ ላይ በተመሠረተ ማስተዋል ተተካ።

በዚህ ትምህርታዊ እንቅስቃሴ፥ ክርስቲያን ሰብአውያን* ግንባር ቀደም ሲሆኑ፥ በተለይ የአዲስ ኪዳንን ቅጂ በግሪክኛ ያዘጋጀው ኢራስመስ [Erasmus] (1466-1536 ዓ.ም) ቀዳሚውን ሥፍራ ይይዛል። የዚህ ሰው ሥራ አዲስ ኪዳንን ቮልጌት በተባለው የላቲንኛ ትርጉም** ሳይሆን፥ መጀመሪያ በተጻፈበት ግሪክኛ ለማጥናት ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል። የማተሚያ መሣሪያ መፈጠርም አያሌ ሰዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን በየግላቸው እንዲያጠኑ አስችሏል።

ዘመነ ሬነዛንስ፥ ሰውን ማዕከላዊ ዓላማው ለሚያደርግ ትምህርት ጽኑ ድጋፍ በመስጠቱ፥ ተሐድሷውያን [Reformers/ሪፎርመርስ] ስለ ግል እምነትና ደኅንነት ከሚያስተምሩት ጋር በመጠኑም ቢሆን አመሳስሎታል።

ለተሐድሶ እንቅስቃሴ መቀጣጠል ምክንያት የሆኑት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችም ነበሩ። ከመካከለኛው ዘመን ፍጻሜ ጋር በከተሞችና በቅኝ ግዛቶች ሳቢያ በተፈጠሩ ገበያዎች አማካይነት ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት መጣ። በዚህ ጊዜ አንድ አዲስ መካከለኛ የኅብረተሰብ መደብ ተፈጠረና፥ ለሮም የሚሰጠው የገንዘብ ፈሰስ እንዲቋረጥ ተቃውሞውን ያሰማ ጀመር።

ያም ቢሆን ከሌሎቹ ምክንያቶች ሁሉ ሃይማኖታዊው ምክንያት ያለምንም ጥርጥር ከፍተኛውን ሥፍራ ይዟል። አዲስ ኪዳንን በቋንቋቸው ለማንበብ ዕድል ያገኙ አንዳንድ ተሐድሷውያንና ክርስቲያን ሰብአውያን፥ በአዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን አሠራርና በሮም ቤተ ክርስቲያን አሠራር መካከል መሠረታዊ ልዩነት መኖሩን አስተዋሉ። በሮማዊቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከካህናት እስከ ጳጳሳት ድረስ ሁሉም በማይገባ አሠራር ውስጥ ተዘፍቀው ነበር፤ አንዳንዶች ሥርዓተ ክህነትን ይገዙና ይሸጡ ነበር። የሮም ቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ከፍሎ የኃጢአት ይቅርታ ማግኘት*** ይቻላል የሚል ትምህርት ስለነበራት፥ ማንኛውም ሰው ወደፊት ለሚሠራውም ኃጢአት እንኳ አስቀድሞ ገንዘብ በመክፈል የኃጢአት ይቅርታ ማረጋገጫ ያገኝ ነበር። ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ከሚደረጉ ማናቸውም ነገሮች ማርቲን ሉተርን ያስቆጣውና ከቤተ ክርስቲያኒቱ እንዲለይ ያደረገው ይህ ድርጊት ነበር።

---

* በዚህ ርእስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት አባሪ አንድን ይመልከቱ።

---

** ይህ በ388 ዓ.ም. ገደማ በጀሮም [Jerome] የተተረጐመ ነው።

---

*** “ኢንደልጀንስ” [Indulgence] በሕይወት ያሉ ሰዎች ከጊዜያዊ ቅጣት እንደሚድኑ ተስፋ የሚሰጥ፥ ለሞቱ ደግሞ ከፐርግቶሪ በቶሎ ነጻ እንዲሆኑ የሚያደርግ በቤተ ክርስቲያን የሚሸጥ የምስክር ወረቀት ነው።

በዚህ ጊዜ እንደ ሉተር ያሉ ሰዎች ሥልጣንን ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት መለሱ። ምን ማመንና እንዴት መኖር እንዳለብን የመጨረሻውን መመሪያ የመስጠት ሥልጣኑ የመጽሐፍ ቅዱስ መሆኑንም አሳወቁ። በቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣንና፥ መጻሕፍቱንም ማጥናት አስፈላጊ በመሆኑ ላይ አጽንኦት በመስጠቱ፥ ጽድቅ በእምነት ነው የሚለውና ሌሎቹም ጥንታዊ አስተምህሮዎች አዲስ ግንዛቤ አገኙ። ሉተር ጀርመን ውስጥ፥ ዝዊንግሊ እና ካልቪን ደግሞ ስዊዘርላንድ ውስጥ፥ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት በስብከትና በጽሑፍ ያስፋፉ ነበር። ይህ ድርጊት በዓለም ላይ አዲስ ብርሃን እንዲበራና የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀትም እንዲሠራጭ አደረገ።

## የዘመነ ተሐድሶ መሪዎች

### *ማርቲን ሉተር (1483-1546)*

የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ፈር ቀዳጅ የሆነው ማርቲን ሉተር፥ በ1483 ዓ.ም. አይስሌበን ሳክሶኒ [Eisleben፥ Saxony] በተባለው ስፍራ ከአንድ የገበሬ ቤተሰብ ተወለደ። ለሥነ-መለኮታዊ ጉዳዮች ያለው ፍላጎት ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀሰቀሰው ምናልባት የኤርፉርት [Erfurt] ዩኒቨርስቲ ተማሪ ሳለ ለሕይወቱ መለኮታዊ ድጋፍና እርዳታ እንደሚያስፈልገው አጥብቆ በተሰማው ጊዜ ሳይሆን አይቀርም። ሉተር ከትልቅ የመብረቅ አደጋ ከተረፈ በኋላ ለቅድስት አን [Saint Anne] በመሳል፥ መነኩሴ ለመሆን ወደ አንድ የሮም ካቶሊካዊት ገዳም ገባ። ይሁን እንጂ ወደ ሮም በመጓዝ ላይ እያለ፥ የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የተዘፈቀችበትን ብልሹ አሠራር አስተውሎ ግራ ተጋባ። ስለዚህ ወደ ዊተንበርግ [Wittenberg] በመመለስ በሥነ-መለኮት የዶክትሬት ዲግሪውን ተቀበለና እዚያው መጽሐፍ ቅዱስን ያስተምር ጀመር። ሉተር መጽሐፍ ቅዱስን፥ በተለይም ሮሜ 1፡17 ላይ ያለውን ቃል በሚያጠናበት ወቅት፥ ጽድቅ የሚገኘው በእምነት ብቻ መሆኑን ተረዳ። ይህ የሥነ-መለኮት ግንዛቤው መሠረት ከመሆኑም በላይ፥ ካቶሊካዊቱን ቤተ ክርስቲያን የመቃወሚያ ምክንያት ሆነው። በመሆኑም ጥቅምት 31 ቀን 1517 ዓ.ም. ዘጠና አምስት መግለጫዎችን በመጻፍ ዊተንበርግ በሚገኝ አንድ የቤተ ክርስቲያን መዝጊያ ላይ ለጠፈ። እነዚህ መግለጫዎች ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጋር የማይስማማባቸውን ጉዳዮች የሚያመለክቱ ነበሩ። ሉተር 'ሶላ ስክሪፕቱራ' ማለትም፥ ለሰዎች ብቸኛ መመሪያ ቅዱሳት መጻሕፍት እንጂ ቤተ ክርስቲያን ወይም ጉባኤዎች አይደሉም በማለት በጽኑ አስገነዘበ።

ይህ ሰው አያሌ ሥነ-መለኮታዊ ቅርሶችን ትቶልናል። ከሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፥ የውኃ ጥምቀትና የጌታ እራት ብቻ ተገቢዎች ናቸው በማለት አስተማረ። የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ በመንቀፍም አያሌ ጽሑፎችን ጽፏል። በምትኩም የራሱን መሠረታዊ የክርስትና አስተምህሮ አኖረ። ታላላቅ መዝሙሮች ለምሳሌ "እግዚአብሔር ኃያል መጠጊያችን ነው" የሚለውንና የመሳሰሉትን ደርሷል። እንዲሁም ለመጀመሪያ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን የአገሩ ሕዝብ ቋንቋ ወደ ሆነው ጀርመንኛ ተርጉሟል።* ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብና ለማጥናት እንዲችሉ የመማሪያ ዘዴዎችንም ቀይሷል።

## *ጆን ካልቪን (1509-1564)*

በዘመነ ተሐድሶ እንቅስቃሴ ውስጥ የተከበረና አንደበተ ርቱዕ የሥነ-መለኮት ሰው የነበረው ጆን ካልቪን፥ በ1509 ፈረንሳይ ውስጥ ተወለደ። ትምህርቱን ፓሪስ ዩኒቨርስቲ ጀመረ። በሰብአዊነት አስተሳሰብ አራማጆች ተጽዕኖ ሥር የገባውም እዚያው ነው። በኋላ በኦርሊየንስ [Orleans] ዩኒቨርስቲ ገብቶ የሕግ ትምህርት አጠና፤ ቡርዠ [Bourges] ዩኒቨርስቲ ገብቶም ተጨማሪ ትምህርት ተከታትሏል። በ1534 የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴን በሙሉ ልቡ በመቀበሉ ከፈረንሳይ ተባረረ። ከዚያም ስዊዘርላንድ ወደሚገኘውና ባዝል [Basel] ወደተባለው ሥፍራ በመሄድ ገና የሃያ ስድስት ዓመት ወጣት ሳለ "የክርስትና ሃይማኖት ድንጋጌዎች" [Institutes of the Christian Religion/ኢንስቲቲዩትስ ኦፍ ዘ ክርስቲያን ሪሊጂን] የተባለውን ታላቅ መጽሐፍ ጻፈ። ይህ መጽሐፍ የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ ትክክለኛ መሆኑን በማብራራት ለፈረንሳይ ንጉሥ መልስ የሚሰጥ ነበር። ይህ ታላቅ መጽሐፍ በየጊዜው ብዙ ማሻሻያዎችና ማስተካከያዎች ከተደረጉለት በኋላ፥ የአራት መድበሎችና የሰማንያ ምዕራፎች ጥራዝ ሊሆን ችሏል።

ካልቪን ስትራስበርግ [Strasbourg] ውስጥ ጥቂት ከቆየ በኋላ፥ በ1541 ጄኔቫ [Geneva] ስዊዘርላንድ ውስጥ ለመኖር ወደዚያ ተመለሰ። እዚያም መጋቢ በመሆን በየቀኑ ይሰብክና ያስተምር ነበር። ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥም በሃያ ሰባቱ ላይ ማብራሪያዎችን ጽፏል። እንዲሁም ከዮሐንስ ራእይ በስተቀር በቀሩት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ላይ ማብራሪያዎችን አቅርቧል። ካልቪን ጄኔቫ በነበረበት ጊዜ አብያተ ክርስቲያናዊና ፖለቲካዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ፥ የሐሰት አስተማሪዎችን በመቅጣት (አንዳንዴም ሞት እስከመፍረድ) ሥልጣን ነበረው። የሴርቪተስ

* ለሉተር ትርጉም ከፍተኛ ቦታ ያሰጠው፥ ለመጻፍ የተጠቀመበት ጀርመንኛ፥ በብዙ ሕዝብ ዘንድ የሚነገር የተለምዶ ቋንቋ መሆኑ ነበር።

[Servetus] አስተምህሮ ሥላሴን አስመልክቶ ተቃርኖ በማሳየቱ በእሳት በመቃጠል እንዲሞት የተበየነበት ፍርድ በአሁኑ ጊዜ በካልቪን ማንነት ላይ ጥቁር ነጥብ ሆኗል። ይሁን እንጂ ካልቪን በሥልጣን ላይ በነበረበት ወቅት፥ በጄኔቭና በሌሎችም ቦታዎች የነበሩ መሪዎችና መናፍቃን እንኳን ሳይቀሩ፥ የሴርቪተስ ዓይነቱ ትምህርት ከባድ ክህደት መሆኑንና የሞት ቅጣት የሚያስከትል መሆኑን ያውቁ ነበር። ካልቪን የሴርቪተስን ሕይወት ለማዳን ብዙ ታግሎ ሳይሆንለት ቢቀር፥ በጣም እያዘነ ፍርዱ እንዲጸናበት አደረገ።

ካልቪን መጽሐፍ ቅዱስን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የተረጎመ የመጀመሪያው ሰው ተብሎ ነበር። በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ላይ የተመሠረተው የሥነ-መለኮት አስተምህሮው፥ በአውሮፓና በስኮትላንድ የሚገኙ "ተሐድሷዊ አብያተ ክርስቲያን"* በዚሁ ጎዳና እንዲጓዙ አድርጓቸዋል።

## *ኡልሪክ ዝዊንግሊ (1484-1531)*

ካልቪን ስዊዘርላንድ ውስጥ የሚኖሩ ፈረንሳይኛ ተናጋሪዎችን በሚያገለግልበት ጊዜ፥ በ1484 የተወለደው ኡልሪክ ዝዊንግሊ ደግሞ በዚያችው አገር የሚኖሩ ጀርመንኛ ተናጋሪዎችን ያገለግል ነበር። ዝዊንግሊ በመጀመሪያ በርን [Berne]፥ ቪዬና [Vienna] ቀጥሎም ባዘል በተባሉ ሥፍራዎች ትምህርቱን ከተከታተለ በኋላ ከ1506-1518 በነበረው ጊዜ የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ካህን በመሆን አገልግሏል። ዝዊንግሊ ክርስቶስንና የተሐድሶን አመለካከት የተቀበለው ካህን ሆኖ ባገለገለባቸው የመጨረሻ ዓመታት፥ ኢራስመስ የተባለው ተርጓሚ በግሪክኛ ያዘጋጀውን የአዲስ ኪዳን ቅጂ በሚያጠናበት ወቅት ነበር። ዝዊንግሊ በ1519 ዙሪክ [Zurich] ውስጥ የአንድ ታዋቂ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሆኖ ሲያገለግል፥ መጽሐፍ ቅዱስን በግልጥ ያስተምርና የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን አሠራር ያወግዝ ነበር። ዙሪክ ከተማ ውስጥ የከተማው ከንቲባ በተገኙበት

---

* "ተሐድሷዊ ቤተ ክርስቲያኖች"። ይህ ቃል የሚያመለክተው የካልቪንንና የዝዊንግሊንን ትምህርተ እምነትና ልምምድ የሚከተሉትን የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያኖች ከሉተር፥ ከአናባፕቲስትና ከሌሎች ተኃድሷዊ የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያኖች ጋር በማነፃፀር ነው።

እነዚህ ቤተ ክርስቲያኖች በእንግሊዝኛ የሚጠሩበት ስም "Reformed Churches" የሚል ሲሆን፥ ትምህርታቸው ደግሞ "የተሐድሶ ትምህርት" ["Reformed Theology"] ይባል ነበር። ይሁን እንጂ፥ በቃሉ ምክንያት ሊመጣ የሚችል መደናገርን ለመከላከል በፋንታው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ "ካልቪናዊ" የሚለውን ቃል እንጠቀማለን።

በተካሔደ አንድ ሕዝባዊ ጉባኤ ላይ በተደረገ ክርክር የዝዊንግሊ አመለካከት (አቋም) ተቀባይነት አገኘና የተሐድሶ ሥነ-መለኮት እንዲሁም አሠራር እንዲስፋፋ ምክንያት ሆነ። በዚህም ምክንያት ካህናት እንዲያገቡ፥ የምስል አምልኮ እንዲወገድ፥ የቅዳሴ ሥርዓት እንዲቆምና የቤተ ክርስቲያንም ንብረት ለትምህርት አገልግሎት እንዲውል ተደረገ።

ዝዊንግሊ፥ የጌታ እራት፥ መታሰቢያ ብቻ ነው የሚለውን አቋም በመያዙ፥ ምንም እንኳ ደኅንነት የሚገኘው በጸጋ ነው በሚለው ፅንሰ አሳብ ላይ ቢስማሙም ሉተር ከዝዊንግሊ ጋር የነበረውን ኅብረት አቋረጠ። ዝዊንግሊ በ1531 ከአንዲት የሮም ካቶሊካዊት ግዛት ከሆነች አውራጃ ጋር በተደረገው ጦርነት ተገደለ። ዝዊንግሊ በአንዳንድ የሃይማኖት ትምህርቶቹ ከካልቪንና ከሉተር የሃይማኖት ትምህርቶች ርቆ በመሄድ የአናባፕቲስቶችን አቅጣጫ ተከትሏል።

## የዘመነ ተሐድሶ ትምሕርተ ቅዱሳት መጻሕፍት

### *የሉተር አስተምህሮ*

ለማርቲን ሉተር፥ በእምነትና በደኅንነት ጉዳዮች ላይ ብቸኛውና እውነተኛው ባለሥልጣን መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ሉተር ወደዚህ አመለካከት ከመጣ በኋላ የሊቀ ጳጳሳቱን ሥልጣን፥ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎችን፥ የኃጢአት ይቅርታ ለማግኘት ገንዘብ መክፈል ያስፈልጋል [Indulgence/ ኢንደልጀንስ] የሚለውን ትምህርትና፥ የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን ሥርዓታት ክፉኛ ተቃውሟል። "ከእግዚአብሔር ቃል በቀር የእምነት አንቀጾችን የሚወስን የለም፤ መላእክት እንኳ አይችሉም" አለ። ከዚህም ሌላ ቅዱሳት መጻሕፍት የመንፈስ ቅዱስ ምስክር እንደመሆናቸው ሥልጣን ያላቸው መሆኑን ገልጧል። ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ሲናገርም፥ "በእግዚአብሔርና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ መጽሐፍ ነው" ብሏል። ስለ ዘፍጥረት መጽሐፍ በጻፈው ማብራሪያ መግቢያ ላይ መጽሐፉን፥ "የመንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ" ብሎታል።

ሉተር ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚያገናኛቸው ስለ ክርስቶስ ከሚገልጡት ነገር ጋር ነው። በመሆኑም የያዕቆብን መልእክት "ገለባ መልእክት" ሲለው፥ ለሮሜ፥ ለገላትያና ለኤፌሶን መልእክቶች ግን የላቀ ቦታ ሰጥቷቸዋል። በርሱ አባባል እነዚህ መልእክቶች፥ ንጹሕ ወንጌልና ስለ ክርስቶስም መሠረታዊ ግንዛቤ የሚያስገኙ ናቸው። መጽሐፈ መክብብ በሰለሞን መጻፉን ይጠራጠራል፤ መጽሐፈ አስቴር ደግሞ፥ ብሉይ ኪዳን ካኖን ውስጥ መጨመር አልነበረበትም ባይ ነው።

ሉተር ስለ ቅዱሳት መጻሐፍት አፈታት ጠቃሚ መመሪያዎችን ሰጥቷል፦ (1) የሕጉ ቃል ብቻ ሳይሆን፥ የመንፈስ ቅዱስም አብርሆት ያስፈልጋል፥ (2) ታሪካዊ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያሻል፥ (3) ሕግ በሆነው ብሉይ ኪዳንና፥ ወንጌል በሆነው አዲስ ኪዳን መካከል መሠረታዊ ልዩነት እንዳለ ማጤን ተገቢ ነው፥ (4) ለቅዱሳት መጻሕፍት ውሁድነትን የሚሰጣቸው ክርስቶስ ነው፥ (5) ቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል በቃል መተርጎም ወይም መፍታት መልካም ነው፤ ተምሳሌታዊ አፈታት ወይም አተረጓጎም ግን "የጦጣ ብልጣብልጥነት" ነው ብሏል።

## የዝዊንግሊ አስተምህሮ

ኡልሪክ ዝዊንግሊ የተባለው ጸሐፊ፥ ቅዱሳት መጻሕፍት እንከን የለሾችና ባለሥልጣን መሆናቸውን ሲያጸና፥ "የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረውን በማድረግ ረገድ እርግጠኛ ነው" ብሏል። ዝዊንግሊ ኢራስመስ የተባለው ሰው በግሪክኛ ያዘጋጀውን የአዲስ ኪዳን ቅጂ አንብቦ ከተለወጠ በኋላ፥ የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን ሥልጣን እንደማያምን በግልጥ አስታወቀ። ደኅንነትን በተመለከተ የመጨረሻው ሥልጣን የመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው ብሏል።

ዝዊንግሊ ጊዜውን ሁሉ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማጥናት ያሳልፍ ነበር። የቅዱሳት መጻሕፍትንም ሥልጣን በማረጋገጥ፥ ከማቴዎስ ወንጌል ጀምሮ የእያንዳንዱን ምዕራፍና ቁጥር ፍቺ በቅደም ተከተል እያብራራ ሰብኳል። የተሐድሶ መሪ እንደመሆኑ፥ ሥራዎቹን ሁሉ፥ አከራካሪ ነጥቦች በእግዚአብሔር ቃል መወሰን አለባቸው በሚለው መርህ ላይ ይመሠርት ነበር። ዝዊንግሊ ሥራውን ሁሉ በቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ ላይ ለመመሥረት ዘወትር ይጥር ነበር። ከሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን፥ ከሉተራዊ ወይም ከአናባፕቲስት ተከታዮች ለሚቀርብለት ተቃውሞ ሁሉ፥ መጽሐፍ ቅዱስን አብነት እያደረገ ነበር መልስ የሚሰጠው። ከሉተር ባላነሰ ሁኔታም በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ ሥነ-መለኮትና ቤተ ክርስቲያን ይሻ ነበር።

ዝዊንግሊ አጽንኦት ከሰጣቸው ነገሮች ውስጥ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ለማንኛውም አንባቢ ግልጥ ነው፤ ማንኛውም አንባቢ መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ ለመረዳት ይችላል የሚሉት ዐቢይ ስፍራ ይይዛሉ። በግልጥ እንደተናገረው፥ መጽሐፍ ቅዱስ "በራሱ ፍጹም ነው፤ ለሰው ልጆችም ጥቅም ተገልጧል።" በመሆኑም መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ ለመረዳት ጳጳስ፥ ካህን ወይም የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ አያስፈልጉትም። መጽሐፍ ቅዱስን መግለጥ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ነው። ትሑት በሆነ ልብ፥

በጸሎትና ባልተበረዘ መንፈስ የሚያነቡት ሁሉ መልእክቱን ሊረዱ ይችላሉ። እነዚህ ሁኔታዎች ሲሟሉ፥ መንፈስ ቅዱስ የመልእክቱን ፍቺ ይገልጥላቸዋል ብሏል።

## የካልቪን አስተምህሮ

ጆን ካልቪን ሃይማኖታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የመጨረሻው ሥልጣን የመጽሐፍ ቅዱስ እንጂ፥ የቤተ ክርስቲያን አይደለም በማለት አረጋግጧል። መጽሐፍ ቅዱስንም የሚመለከተው፥ በማንኛውም ጊዜና በሁሉም ሰው ላይ የመጨረሻው ከፍተኛ ባለሥልጣን እንደሆነ አድርጎ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እስትንፋስ መለኮት ነው የሚለውን አመለካከት እንደሚቀበል ያረጋገጠውም፥ ሰዎች ሁሉ "በቅዱሳት መጻሕፍት አማካይነት የተላለፈውን ነገር፥ አንድም ሳያስቀሩ መቀበል አለባቸው" በማለት ነበር።

አንዳንድ ሰዎች ካልቪንን፥ "የተንታኞች ንጉሥ"፥ "የአሥራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት ተንታኝ"፥ እንዲሁም "የእውነተኛ ትንታኔ ፈጣሪ" ብለውታል። ሌሎች ደግሞ፥ የመጀመሪያው ሳይንሳዊ ተንታኝ ብለውታል። ካልቪን በሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ላይ ጠለቅ ያሉ ትንታኔያዊ ማብራሪያዎችን ከመጻፉም በላይ፥ "የክርስትና ሃይማኖት ድንጋጌዎች" በተሰኘው መጽሐፉ ላይ የራሱን ሥነ-መለኮታዊ አስተምህሮ በተመለከተ ሰፊ ማብራሪያ ሰጥቷል። የቅዱሳት መጻሕፍት አፈታት መርህን አስመልክቶም ከዚህ የሚከተሉትን መመሪያዎች ገልጧል፡-

(1) የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚ ወይም ፈቺ የመንፈስ ቅዱስ አብርሆት ያስፈልገዋል፥ (2) ተምሳሌታዊ አተረጓጎም ሰዎችን ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የሚያርቅ በመሆኑ ሰይጣናዊ ነው፤ በመሆኑም ሊወገድ ይገባል፥ (3) መጽሐፍ ቅዱስ በራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ይተረጎማል። ይህ አባባል ለካልቪን ብዙ ነገሮችን ያካትትለታል። መጽሐፍ ቅዱስን ቃል በቃል መተርጎም መጽሐፉ የሚለውንና፥ ደራሲው ለማለት የሚፈልገውን ማድመጥ ማለት ነው። የቅዱሳት መጻሕፍትን ሰዋሰው፥ የቃላትን ፍቺና አገባቡን (ዐውደ ንባቡን)፥ እንዲሁም በተመሳሳይ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከቅዱሳት መጻሕፍት ማነጻጸር ማለት ነው።

## የዘመነ ተሐድሶ ትምህርተ ክርስቶስ

ትምህርተ ክርስቶስን አስመልክቶ ካልቪንና ዝዊንግሊ ትክክለኛውን አመለካከት ተከትለዋል። ክርስቶስ አንድ አካል በሁለት ባሕርይ ነው። ሁለቱ ባሕርያት እርስ በርስ አይቀላቀሉም። ሉተር ከዚህ

አኳያ የተለየ አመለካከት ነበረው። የክርስቶስ ሰብአዊ ባሕርይ እንደ ሁሉን አዋቂነት፥ በሁሉ ሥፍራ መገኘትና ሁሉን ቻይነት የመሳሰሉ የመለኮት ባሕርያት ስላሉት፥ በጌታ እራት ጊዜ በአካል ይገኛል ብሎ አስተምሯል። የዚህ አመለካከት ችግር፥ በክርስቶስ ሁለት ባሕርያት መካከል ያለውን ልዩነት አለመጠበቁ ነው።

## የዘመን ተሐድሶ ሥነ-ሰብአዊነት

### *የተሐድሷውያን አመለካከት*

ሉተርና ካልቪን የሰውን በኃጢአት መውደቅ አስመልክቶ ከሞላ ጎደል አንድ ዓይነት አመለካከት አላቸው። በነርሱ አመለካከት ሰው በኃጢአት ከወደቀበት ፍርድ ይድን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር ጸጋ ያስፈልገዋል። ዝዊንግሊም ከዚህ አመለካከት ጋር ይስማማል። ከ1519-1605 የኖረውና ካልቪንን ጄኔቭ ውስጥ የተካው ቴዎዶር ቤዛ [Theodore Beza] የተባለው መምህር እንዲህ በማለት አስተማረ:- አዳም የሰው ዘር ሁሉ ቀዳሚ አባት ነው፤ ስለዚህ አዳም ኃጢአት ሲሠራ እርሱ የሰብአውያን ሁሉ ወካይ እንደመሆኑ፥ የሰው ዘር በሙሉ በኃጢአት ወደቀ፥ ተበከለም። በዚህም ሳቢያ ከያኔ ወዲህ የሚወለድ ሕፃን ሁሉ በኃጢአት የተበከለ ነው።

ሰው በኃጢአት የተበከለ ነው ከሚለው አመለካከት የተነሣ፥ ካልቪን ሰው ነጻ ፍቃድ አለው የሚለውን አመለካከት አልተቀበለውም። በርሱ አባባል፥ ሰው በውድቀቱ ጊዜ ነጻ ፍቃዱን አጥቷል። በእርሱ ትምህርት መሠረት የሰው ፍቃድ ወደ ክፉ ከሚያመራው አቅጣጫ በስተቀር ወደየትም እንዳይሄድ ተጠፍሯል። በሌላ በኩል ደግሞ፥ ሰው በኃጢአቱ ምክንያት ተጠያቂነቱ አይቀሬ ነው። ምክንያቱም ከውጪ በሆኑ ሁኔታዎች ሳይሆን በገዛ ፍቃዱ ኃጢአትን ሠርቷል በማለት አስተምሯል። በተጨማሪም ሰው ማመዛዘኛ አእምሮው ቢጎዳም ክፉና ደጉን ለመለየት ይችላል። ስለዚህ መልካሙን ትቶ ክፉውን በመምረጡ ተጠያቂ ነው ብሏል።

ሰው በኃጢአት ተበክሏል የሚለው አስተምህሮ ውጤት፥ አስቀድሞ የመወሰን [Predestination] አመለካከት ነው። ይህ አሳብ በሉተር፥ በካልቪንና በዝዊንግሊ ተቀባይነት አግኝቷል። ሰው በኃጢአት በመውደቁ ሳቢያ፥ በቀና መንገድ ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ስለማይችል፥ እግዚአብሔር የተወሰኑትን ለደኅንነት ይመድብ ዘንድ ፈልጓል።

## ሱስንዮሳዊው አመለካከት

ከ1539-1604 የኖረውና ፋውስተስ ሱስንዮስ [Faustos Socinus] የተባለው ሰው፥ የፔላጊዩሳውያንን አመለካከት ተከትሎ፥ ሰው በኃጢአት ተበክሏል የሚለውን አመለካከት አልተቀበለም። ሱስንዮስ ሲያስተምር፥ ሰው በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩ፥ የምግባር ፍጹምነቱን የሚያሳይ ሳይሆን፥ ከሱ ያነሱ ፍጥረታትን ለመግዛት መቻሉን ነው። ምንም እንኳ አዳም ኃጢአት ቢፈጽም፥ የርሱ ኃጢአት በዝርያዎቹ ላይ ክፉ ጠንቅ አላስከተለም። ምክንያቱም የሰው ምግባራዊ ተፈጥሮ በዘር ተከታዮቹ ዘንድ የሚተላለፈው ሳይበከልና ሳይበላሽ ነው። ሰዎች አሁን ኃጢአትን የሚፈጽሙት በውርስ ካገኙት ኃጢአት ሳቢያ ሳይሆን፥ ከሚያዩት መጥፎ ምሳሌ የተነሣ ነው። ሱስንዮስ ከዚህ በተቃራኒው ሲያስተምር፥ ሰዎች ሁሉ አዳም ከውድቀት በፊት ከነበረው ባሕርይ (ተፈጥሮ) ጋር ስለሚወለዱ፥ ኃጢአትን ለመከላከል ወይም ለማስወገድ ይችላሉ ብሏል።

## አርሚኒዮሳዊ አመለካከት

ከ1560-1609 የኖረውና ጀኮበስ አርሚኒዮስ [Jacobus Arminius] የተባለው ሰው ጄኔቫ ውስጥ የቴዎዶር ቢዛ ተማሪ ስለነበር፥ አክራሪ ካልቪናዊ ሆነ። ነገር ግን ከተቃዋሚዎቹ ጋር በገጠመው ክርክር፥ ከእርሱ አሳብ ይልቅ የተቃዋሚዎቹ ጠንካራ መሆኑን በማመን አመለካከቱን ለወጠና፥ ለሰው ዘር በሙሉ ሁሉን አቀፍ ጸጋና ነጻ ፍቃድ ተሰጥቷል የሚለውን አስተምህሮ ደገፈ። በመሠረቱ ግን ሰው የኃጢአት ውርስ አለበት የሚለውንና፥ የአዳም በደልና ኃጢአት ለዘር ተተኪዎቹ ተላልፏል የሚለውን አስተምህሮ በመቃወሙ አቋሙ ከፊል ፔላጊዩሳዊ ነው። እንደ አርሚኒዮስ አሳብ የሰው ዘር ከአዳም የወረሰው የኃጢአት ብክለትን ብቻ ነው። ይህ ብክለት ደግሞ በዝርያዎቹ ላይ እየተላለፈ ደካማ አደረገው እንጂ ለኃጢአት ፍርድ አልዳረገውም። ኃጢአት ያስከተለው ጉዳት ከዚህ ይልቅ፥ ሰው በጥረቱ የዘላለም ሕይወት እንዳያገኝ ደካማ ማድረጉ ነው። ይሁን እንጂ፥ የሰው ውድቀት ወደ እግዚአብሔር የመቅረቢያ ኃይል አላሳጣውም። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ቀስቃሽ ጸጋ በመስጠት፥ የኃጢአት ብክለት ያስከተለው ውጤት እንዲደመሰስና እርሱ ከዘጋጀለት ደኅንነት ጋር እንዲተባበር ያስችለዋል።

## የዘመነ ተሐድሶ ትምሕርተ ደኅንነት

### *አስቀድሞ መወሰን [Predestination]*

ካልቪን ደኅንነት በጸጋ ይገኛል በማለት አስተማረ። ይህ ደኅንነት የተመሠረተው በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ድንጋጌ ወይም ውሳኔ ላይ ነው። እግዚአብሔር ሉዓላዊ ከመሆኑ የተነሣ፥ የሚሆኑት ነገሮች ሁሉ በእርሱ የተወሰኑ ናቸው። በዚሁ መሠረት ካልቪን ሁለትዮሽ አስቀድሞ መወሰንን አስተማረ። “በትምህርቱ ‘አስቀድሞ መወሰን’ ብለን የምንጠራው፥ እግዚአብሔር በዘላለም ዕቅዱ መሠረት የእያንዳንዱን ሰው ዕድል የወሰነበትን ነው። ሰዎች በአንድ ዓይነት ሁኔታ አልተፈጠሩም። ለአንዳንዶች የዘላለም ሕይወት፥ ለአንዳንዶች የዘላለም ጥፋት ተመድቦ ላቸዋል። ስለዚህ የእያንዳንዱ ሰው ፍጻሜ ከሁለት ለአንዱ ነገር ተወስኗል። ወይ ለዘላለም ሕይወት፥ አለዚያም ለዘላለም ሞት” ብሏል። የአስቀድሞ መወሰን አስተምህሮ፥ ለዘላለም ሕይወት መመረጥንና ለፍርድ መመደብን ያጠቃልላል። ካልቪን የሁለቱንም አስፈላጊነት አበክሮ ገልጧል። ለደኅንነት መመረጥ በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ የተመሠረተ ሲሆን፥ ኩነኔ ደግሞ ከኃጢአትና ከበደል የተነሣ የሚመጣ ነው።

ሉተርም፥ የሰውን በኃጢአት መበከልና አቅመ ቢስነት መሠረት በማድረግ፥ አስቀድሞ ስለመወሰን አስተምሯል። ዝዊንግሊም የአስቀድሞ መወሰን እምነቱን በእግዚአብሔር ቸርነት ላይ መሥርቷል።

### *ሥርየት*

የተሐድሷውያኑ አመለካከት። ምንም እንኳ ፕሮቴስታንቶችም ሆኑ ካቶሊኮች የክርስቶስን የሥርየት ዋጋ ቢገነዘቡ፥ የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ከቶማስ አኩናስ የተገኘውን አስተምህሮ ስትከተል፥ የተሐድሷውያን አመለካከት ደግሞ በአንሰለም የሥርየት አመለካከት ላይ የተመሠረተ ነው። ይሁን እንጂ፥ አንሰለም ሰው ኃጢአት በመሥራቱ የተነሣ የእግዚአብሔር ክብር ተወስዶበታል፤ በመሆኑም ይህን የእግዚአብሔር ክብር ለማስመለስ ክርስቶስ መሞት ነበረበት፥ በማለት አስተማረ። በተሐድሷውያን አመለካከት ግን፥ ክርስቶስ የሞተው የእግዚአብሔርን የፍትሕ ጥያቄ ለማርካት ነው። ስለዚህም ክርስቶስ ለኃጢአት የሚገባውን ቅጣት በመሸከምና በመስቀል ላይ በመሞት የእግዚአብሔርን ፍትሕ አረካ። ይህ የክርስቶስ ሥራ ውጤታማ የሚሆነው፥ አማኙን ከእርሱ ጋር አንድ በሚያደርገው እምነት ብቻ ነው። እንዲህ ሲሆን

አማኙ የክርስቶስን ጽድቅ ይለብሳል። ሉተርም በበኩሉ እንዲህ አለ፦ ክርስቶስ "በመንግሥቱ ኖሬ የእርሱ እሆን ዘንድ በክቡር ደሙ፥ ያለ ኃጢአት በሆነው ሞቱና ሥቃዩ ዋጀኝ።" ካልቪን ደግሞ የክርስቶስ የሥርየት ሞት ለተመረጡት ብቻ ነው ብሏል።

የሱስንዮሳውያን አመለካከት። ሱስንዮስ የእግዚአብሔር ፍትሕ የክርስቶስን ሞት ጠይቋል፥ የሚለውን አሳብ አልተቀበለውም። እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ያለ ክርስቶስ የሥርየት ሞት ይቅር ሊለው ይችላል በማለት አስተማረ። እንደርሱ አባባል እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ይቅር የሚለው፥ ከምሕረቱ የተነሣ እንጂ፥ ከክርስቶስ ሞት የተነሣ አይደለም። እርሱ ከሰው የሚፈልገው ንስሐ መግባትንና ለሕግጋቱ የመታዘዝ ፍላጎት ማሳየትን ብቻ ነው። የክርስቶስ ኢየሱስ ሞት የመታዘዝ ምሳሌ በመሆን ሌሎችን ያነሣሣል። የሱስንዮስ አመለካከት ከታሪክ አኳያ ሲታይ፥ ከፔላጊዩሳዊነት፥ በቅርቡ ደግሞ ከዩኒተሪያኒዝም* ጋር ተፈርጇል።

ግሮቲየሳዊ አመለካከት። ከ1583-1645 ዓ.ም. የኖረውና ሁጎ ግሮቲየስ የተባለው የሥነ-መለኮት ሰው፥ የሱስንዮስን አስተምህሮ ተቃውሟል። ይሁን እንጂ ከተሐድሶውያን የተለየ አቋም ነበረው። ግሮቲየስ

| *ተሐድሶውያን (ሪፎርመርስ) በኃጢአት ሥርየት ላይ ያላቸው አመለካከት* | | |
|---|---|---|
| *ሰዎች* | *የክርስቶስ ሞት* | *የእግዚአብሔር ሥራው* |
| ሱስንዮስ | አያስፈልግም | ይቅርታው ከምሕረቱ የተነሣ ነው፥ ከክርስቶስ ሞት የተነሣ አይደለም |
| ግሮቲየስ | "የምልክት ዓይነት ክፍያ" ነው፤ ሙሉ ክፍያ አላስፈለገም | የሕግን ጥያቄ አስቀረ |
| አርሚኒዮስ | ለኃጢአት ዕዳ ሙሉ ክፍያ አይደለም፥ ግን ለቅጣቱ ምትክ ነው | በክርስቶስ ሞት በኩል ምሕረትን ያደርጋል፤ የፍትሕን ጥያቄ ይተዋል |
| ሉተር | ለኃጥዑ ምትክ ሥርየት፤ የእግዚአብሔርን ቁጣ ያበረደ | ለሚያምኑ ጽድቅን ይሰጣል |
| ካልቪን | ለኃጢአት ምትክ ሥርየት፤ የእግዚአብሔርን ቁጣ ያበረደ | ለሚያምኑ ጽድቅን ይሰጣል |

* በዚህ ርእስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት አባሪ አንድ ይመልከቱ።

በትምህርቱ አጉልቶ ይገልጥ የነበረው፥ እግዚአብሔር ለሰው ኃጢአት ሙሉ የበደል ክፍያ አልጠየቀም፤ የክርስቶስ ሞት የሕግን ጥያቄ ለማስወገድ የተደረገ የምልክት ዓይነት ክፍያ ነው በማለት ነበር። የአዲስ ኪዳን አስተምህሮ ግን፥ የክርስቶስ ኢየሱስ ሞት፥ ሕግ የሚጠይቀውን ሁሉ በበቂ ያሟላል የሚል ነው። በመሆኑም ግሮቲየስ እጅግ ተሳስቷል።

የአርሚኒዮሳውያን አመለካከት።* የአርሚኒዮሳውያን ሥነ-መለኮት አስቀድሞ የተመሠረተው የሱስንዮሳዊነትን ስሕተቶች ለማረም በጻፉት፥ ኩርሲሊየስ [Curcelaeus] እና ሊምቦርክ [Limborch] በተባሉ ሰዎች ነው። እነዚህ ሰዎች የክርስቶስን ሞት የሚመለከቱት በደለኛውን ነጻ የማውጣት ዓላማ ካለው የብሉይ ኪዳን የእንስሳት መሥዋዕት ሥርዓት ጋር በማመሳሰል ነው። የክርስቶስ ሞት መሥዋዕት ቢሆን እንኳ፥ መሥዋዕት የዕዳ ክፍያ ወይም በኃጢአት የተነሣ የተፈጠረውን የፍትሕ ጉድለት ማሟያ አይደለም። በብሉይ ኪዳን የመሥዋዕት ሥርዓት ምሳሌ መሠረት ሕጉ የሚጠይቀውን የእንስሳ መሥዋዕት የሚያቀርብ የብሉይ ኪዳን አማኝ፥ የኃጢአት ይቅርታን ያገኛል። በተመሳሳይ ሁኔታ ምንም እንኳ ክርስቶስ በቀጥታ (ሙሉ በሙሉ) ኃጢአተኛው ይቀበለው የነበረውን ቅጣት ባይቀበል፥ እግዚአብሔር በእርሱ ሞት ምክንያት ኃጢአተኛውን ይቅር ለማለት ተስፋ ሰጥቷል። ይህንንም ያደረገው የፍትሕን ጥያቄ ይቅር ብሎ በመተው ነው። ክርስቶስ በሞቱ ሰው ሊቀበለው የተገባውን መከራ ያህል አልተቀበልም። ይልቁንም የክርስቶስ ሞት የሰው ቅጣት ምትክ ነው።

በአርሚኒዮሳውያን አመለካከት መሠረት፥ የክርስቶስ ሞት ለሰው ከሚገባው ቅጣት ጋር እኩል ስላልሆነ፥ የርሱ ሞት ለእኛ ኃጢአት ሙሉ ክፍያ አይደለም። የክርስቶስ ሞት (ሰው በኃጢአቱ ምክንያት ሊቀበለው ይገባው ለነበረው ቅጣት)፥ እግዚአብሔር የሰጠው የምትክ ቅጣት ብቻ ነው። ስለዚህ የአርሚኒዮሳውያን አመለካከት ክርስቶስ ለኃጢአት ሙሉ ክፍያ አላደረገም ከሚለው የግሮቲየስ አመለካከት ጋር ይመሳሰላል።

## *እምነትና ሥራ*

ሉተራዊ አመለካከት። ለማርቲን ሉተር የጸጋ እሳቤ ብርሃን የፈነጠቀለት፥ ከ1517 ዓ.ም. በፊት ሮሜ 1፥17ን ባነበበ ጊዜ ነበር። ከዚያን ጊዜ አንስቶ ከሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ በመለየት ደኅንነት በእምነት ብቻ የሚገኝ መሆኑን በጽኑ አመነ። ይህም በላቲን 'ሶላ

---

* በዚህ ርእስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት አባሪ አንድን ይመልከቱ።

ፊዴ' ("እምነት ብቻ") ይባላል። ሉተር ዘጠና አምስቱን የእምነት መግለጫ ነጥቦች [theses] በዊተንበርግ ቤተ ክርስቲያን በራፍ ላይ የለጠፈበት እ.አ.አ. ጥቅምት 31 ቀን 1517 ዓ.ም. ትክክለኛው የዘመነ ተሐድሶ ጅማሬ ጊዜ ሆኖ ሊወሰድ ይችላል። በእምነት መግለጫው ውስጥ፥ ሰው ከኃጢአት ፍርድ ለመዳን የራሱን አስተዋጽኦ ማድረግ አለበት ከሚለው የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አመለካከት ተጻራሪ የሆነውና ደኅንነት የሚገኘው በጸጋና በእምነት ብቻ ነው የሚለው አሳብ ተገልጧል። ከዚህም የተነሣ በሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን እምነት፥ ሰው ለሠራው ኃጢአት ራሱን በማሠቃየት በ"ሥርዓተ ንስሐ"* ዋጋ መክፈል አለበት፥ "በኢንደልጀንስ"**፥ እና በቀሳውስት በኩል ይመጣል የሚባለውን ይቅርታ፥ ባጠቃላይ በሰዎች በኩል ይገኛል የሚባለውን ደኅንነት ሁሉ ተቃወመ። ለሰው ልጅ መዳንና መጽደቅ የሚያስፈልገው፥ የእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው ከሚል ድምዳሜም ላይ ደረሰ። የኃጢአት ይቅርታ የሚያስገኝና ለሚያምን ሁሉ የክርስቶስን ጽድቅ የሚሰጥ፥ የእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው አለ።

በትምህርቱ ያስገነዘበው ሌላ ነገር፥ ሥራ፥ በደኅንነት ውስጥ አንዳችም ድርሻ የለውም የሚል ነበር። መልካም ሥራ የደኅንነት ውጤት ወይም ፍሬ እንጂ፥ በፍጹም የደኅንነት አንዱ ክፍል አይደለም ካለ በኋላ፥ ሥራን በሁለት በመክፈል "የሕግ ሥራ" ባለማመን ጊዜ የሚፈጸምና ለደኅንነትም ድርሻ የሌለው ሲሆን፥ ሌላው የጽድቅ ምልክት የሆነው "የእምነት ሥራ" ነው ብሏል። እነዚህ ትክክለኛና በጎ ሥራዎች በአሥርቱ ትእዛዛት ውስጥ እንደሚገኙ ሲገልጥ፦ "በዚህ ሁኔታ አሥርቱ ትእዛዛት አሉ፥ እነርሱም የመለኮትን አስተምህሮ በአጭሩ የዘገቡ ናቸው። እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት የሚቻለን ትእዛዛቱን ስንፈጽም ነው...ከአሥርቱ ትእዛዛት ውጪ ምንም ሥራ ወይም መልካም ነገር እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኘው አይችልም" ብሏል።

ካልቪናዊ አመለካከት። ጆን ካልቪን መዳን በእምነት ብቻ ነው በሚለው ጉዳይ ላይ ከሉተር ጋር ሙሉ በሙሉ ይስማማል። ለጉዳዩ አጽንኦት በመስጠትም ጽድቅን የሕግ ክንውን እንደሆነ በመቁጠር፥ እግዚአብሔር በእምነት የቀረበውን ኃጢአተኛ እንዲሁ በጸጋው ጸድቀሃል ብሎ ያውጅለታል ይላል። ይሁን እንጂ፥ ከሉተር አስተምህሮ ጋር ሲነጻጸር፥ የካልቪን የደኅንነት አስተምህሮ የሚጀምረው፥ እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ከመረጠበት ሁኔታ ነው። እንደ ካልቪን ግንዛቤ፥

* በገጽ 56 ላይ የሚገኘውን የግርጌ ማስታወሻ ይመልከቱ።

** በገጽ 60 ላይ የሚገኘውን የግርጌ ማስታወሻ ይመልከቱ።

እግዚአብሔር ለደኅንነት በሚያደርገው ምርጫ ምንም ቅድመ ሁኔታ አያስፈልገውም። ምክንያቱም፥ ምርጫ በሰው እምነትና በጎ ሥራ ላይ የተመሠረተ ከሆነ፥ ጸጋነቱ ይቀራል።

ከያዕቆብ መልእክት 2፡20 ጋር በተገናዘበ ሁኔታ ካልቪን ሲያስተምር፥ በሥራ መጽደቅ የሚለው፥ ጽድቅ በሥራ ይገኛል ለማለት አይደለም፤ ይልቁንም ሉተር እንዳስተማረው መልካም ሥራ የጽድቅን እውነትነት ይገልጣል ብሏል። ስለዚህ ካልቪን ስለ ጽድቅ "ጥንድ ግንዛቤ" ነበረው። አንደኛውና ቀዳሚው፤ መጽደቅ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትን ማግኘት ሲሆን ይህም የሚሆነው ጽድቅን በመልበስ አማካኝነት ነው። የሚገኘውም በእምነት ብቻ ነው። ሁለተኛውና የዚህ ውጤት የሆነው ጽድቅ ደግሞ፥ በሰዎች ፊት የሚገለጥ የእምነት ጽድቅ ነው። ይህ ነው በሥራ መጽደቅ ብሏል።

የካልቪን የደኅንነት አስተምህሮ ጽድቅንና ቅድስናን ያዛመደ በመሆኑ አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል። ሁለቱም ማለት፥ ጽድቅና ቅድስና ያላቸው ልዩነት እንደተጠበቀ እንዲሆን በማድረግ ከደኅንነት ጋር አዛምዷቸዋል። ክርስቶስ ሰውን ሳይቀድስ አያጸድቅም። ካልቪን እንደሚለው፥ ጽድቅ ወደ ቅድስና ይገፋፋል። ምንም እንኳ ጽድቅ ነጻ ስጦታ ቢሆን፥ ቅድስና ግን እማኙ የሚሰጠው የምሥጋና አጸፋ ይሆናል። ካልቪን "ማንም ቢሆን የወንጌልን ጸጋ ተቀብሎ ከቀደመው የስሕተት ሕይወቱ የማይለይ፥ ወደ ትክክለኛው መንገድ የማይገባና፥ ራሱን ለንስሐ ሕይወት የማያስገዛ ሊሆን አይገባም" በማለት ገልጧል።

አርሚኒዮሳዊ አመለካከት። እግዚአብሔር ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ሰዎችን ይመርጣል፥ ከሚለው የካልቪን አስተምህሮ በተቃራኒ፥ አርሚኒዮሳውያን እግዚአብሔር ሁኔታን አይቶ ይመርጣል፤ ማለትም በክርስቶስ የሚያምኑት እነማን እንደሆኑ በማወቅ ለደኅንነት ይመርጣቸዋል ይላሉ። ይሁን እንጂ የደኅንነት ዕድል ለሰው ሁሉ ተሰጥቷል። ምክንያቱም ክርስቶስ ለተመረጡት ብቻ ሳይሆን፥ ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት ሞቷልና። ሰው ከኃጢአቱ የተነሣ ለእግዚአብሔር በጎ አጸፋ መስጠት ባይችል እንኳ፥ ለሰው ሁሉ ነጻ ምርጫን በመጠቀም ክርስቶስን ለመምረጥም ሆነ ላለመምረጥ የሚያስችለው ቀስቃሽ ጸጋ ከእግዚአብሔር ተሰጥቶታል ይላሉ። ይሁን እንጂ አማኝ መንፈስ ቅዱስን ሊቃወም፥ ወደ ዓለም ሊመለስና ደኅንነቱንም ሊያጣ ይችላል። የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት ጽናት ወሳኝ ነው ብለዋል።

# የዘመነ ተሐድሶ ትምሕርተ ቤተ ክርስቲያን

## *ሉተራዊ አመለካከት*

ቤተ ክርስቲያን። ማርቲን ሉተር ከሮም ካቶሊካዊነት በመውጣት የቤተ ክርስቲያንን ስሕተት የለሽነት እና የልዩ ካህንነትን አስተሳሰብ ተቃውሟል። አማኞች ሁሉ ካህናት እንደሆኑም አስተምሯል። ይህ የመጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነት ማንሰራራት ሂደት ነበር። ሉተር "ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ያሉ አማኞች ሁሉ ጉባኤ ናት" ብሎ አስተማረ። እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን፡- በክርስቶስ በማመን አንድ የሆኑትን

| *ተሐድሷውያን ስለ ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ሕጎች ያላቸው አመለካከት* | | | |
|---|---|---|---|
| *ቡድን* | *ቤተ ክርስቲያን* | *ጥምቀት* | *የጌታ እራት* |
| ሉተራውያን | የማትታየው ቤተ ክርስቲያን በምድር ያሉ አማንያን ሁሉ ስብስብ ናት። የምትታየው ቤተ ክርስቲያንን በወንጌል ቃል አገልግሎትና በምትፈጽማቸው ሥርዓቶች ትገለጣለች። | ለደኅንነት አስፈላጊ ነው። ደኅንነትን ያስገኛል። የሕፃናት ጥምቀት አስፈላጊ ነው፤ እግዚአብሔር እምነትን በውስጣቸው ይሠራል። | "ኮንሰብስታንዩሽን" [Consubstantiation] ክርስቶስ በሕብስቱና በወይኑ ውስጥ፥ "አብሮ እና ከበታቹ" ይገኛል። |
| ካልቪናውያን | ሁሉ አቀፋዊት ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ምጽአት ትሟላለች። ደኅንነት ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ይቻላል። | የአማንያን እምነት ምልክት ነው። የሕፃናት ጥምቀት አስፈላጊ ነው፤ የኪዳን ምልክት ነው። | ክርስቶስ በመንፈስ ይገኛል፥ ለተካፋዮቹም ፀጋን ያስተላልፋል። |
| አናባፕቲሳውያን | ቤተ ክርስቲያን አማኞችን ብቻ ያቀፈች ናት (ሕፃናት የቤተ ክርስቲያን አካል አይደሉም)። ራስን በመግዛት እማካይነት ቤተ ክርስቲያን ንጹሕ መሆን እንደሚገባት በአጽንኦት አስገንዝበዋል። | ጥምቀት ለአማኞች ብቻ ነው። የሕፃናት ጥምቀትን ይቃወማሉ። | መታሰቢያ ብቻ ነው። ኅብስቱና ጽዋው የክርስቶስና የሞቱ ተምሳሌቶች ናቸው። ምንም ፀጋ አይተላለፍም። |

አማኞች ያቀፈች ናት። ሉተር "ክርስቲያን ወይም ክርስትና" የሚለውን ስያሜ የሚጠቀምበት፥ የቤተ ክርስቲያንን ሁሉ አቀፋዊነት ለማጉላት ነው። የቤተ ክርስቲያንን አንድ መሆን ጠብቆም፥ የምትታየውና የማትታየው በማለት በሁለት ይከፍላታል። የምትታየው ቤተ ክርስቲያን፥ የወንጌል ቃል አገልግሎትና ሥርዓት በምድር የሚፈጸምባት ስትሆን፥ የማትታየው ደግሞ ደኅንነትን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ያገኙና ከክርስቶስም ጋር የተለየ ኅብረት ያላቸው ምዕመናን ስብስብ ናት።

ጥምቀት። ሉተር የጌታ እራትና ሥርዓተ ጥምቀት፥ የእግዚአብሔር ጸጋ መተላለፊያ ናቸው በማለት አስተምሯል። እነዚህ ሥርዓታት በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ እንጂ፥ በተቀባዩ ሰው እምነትም ሆነ ማንነት ላይ የሚመሠረቱ አይደሉም። በዚህ መሠረት ነው የኋላ ኋላ ሉተር የማያምኑም እንኳ ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ጥቅም ያገኛሉ ብሎ ያስተማረው።

ሉተር ስለ ጥምቀት የነበረው አስተሳሰብ ከሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አመለካከት እምብዛም የተለየ አልነበረም። የሥርዓተ ጥምቀቱ አፈጻጸም ከካቶሊካዊው ሥርዓት ጋር የተዛመደ ነበር። ሉተር ጥምቀት ለደኅንነት አስፈላጊ መሆኑን፥ እንደውም ዳግም ልደትን የሚያስገኝ መሆኑን አስተምሯል። በመቀጠልም ጥምቀት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የሚደረግ ስምምነት ሲሆን፥ እግዚአብሔር የተጠማቂውን ኃጢአት ይቅር እንደሚልና ቀጣይ ጸጋ እንደሚሰጥ ተስፋ ሲሰጥ፥ ተጠማቂው ደግሞ በኃጢአቱ ተጸጽቶ ሕይወቱን በምሥጋና ለእግዚአብሔር በመስጠት ቃል የሚገባበት ነው ብሏል። በተጨማሪም "እንጠመቅ ዘንድ ትክክለኛ ትእዛዝ አለብን፥ አለበለዚያ አንድንም . . . ይህ በመጀመሪያ ወደ ክርስቲያኑ ጉባኤ የገባንበት ሥርዓት ነው" ብሏል።

ሉተር የሕፃናትን ጥምቀትም ይደግፋል። ሕፃናት እምነትን መለማመድ ባይችሉም፥ እግዚአብሔር በቀስቃሽ ጸጋው አማካይነት በአእምሯቸው የእምነትን ሥራ ይሠራል በማለት አስተምሯል። ሕፃናትን የማጥመቅ ትምህርቱን የመሠረተውም፥ አሕዛብን ሁሉ አጥምቁ በሚለው ትእዛዝ ላይ ነው (ማቴዎስ 28፥19)።

የጌታ እራት። ሉተር በጌታ እራት ጊዜ የሚወሰደው ወይንና የሚቆረሰው ኅብስት በቀጥታ ወደ ጌታ ሥጋና ደምነት ይቀየራል የሚለውን ካቶሊካዊ አስተምህሮ ተቃውሟል። በጌታ እራት ጊዜ ክርስቶስ በአካል ይገኛል የሚል አመለካከት ስለነበረው፥ አሳቡን ከሚቃወመውና ዝዊንግሊ ከሚባለው ሰው የከረረ ተቃውሞ ገጥሞታል። ይህ የሉተር አመለካከት፥ ምንም እንኳ ወይኑና ኅብስቱ ወደ ጌታ ሥጋና ደምነት ባይቀየርም፥ የጌታ

እራት በሚወሰድበት ጊዜ፤ ክርስቶስ በኅብስቱና በወይኑ "ውስጥ፥ አብሮ እና ከበታቹ" ይገኛል የሚል ነው። ይህ አመለካከት "ኮንሰብስታንሺዬሽን" [Consubstantiation] ይባላል።

## ካልቪናዊ አመለካከት

ቤተ ክርስቲያን። ሉተራውያንና ካልቪናውያን አብያተ ክርስቲያናት* ከሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ከመለየት አንጻር አንድ ቢሆኑም፥ ሊወገዙና እንዳሉ ሊቀጥሉ በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ በመካከ ላቸው አበይት ልዩነቶች ነበሩ። ሉተራዊነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጥ የተከለከሉ የመሰሉትንና የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የምታከናውናቸውን ሁኔታዎች ይቃወማሉ። ካልቪናዊ አብያተ ክርስቲያን ግን ከዚያም አልፈው የመጽሐፍ ቅዱስ ማረጋገጫ አለው የሚሉትን ነገር ብቻ ነው ከሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የሚቀበሉት።

ሉተር፥ ቤተ ክርስቲያን የምትታየው በምትፈጽማቸው ሥርዓቶች መሆኑንና ደኅንነትንም በዚህቹ በገሃዱ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት እንደሚገኝ በአጽንኦት ሲያስገነዝብ፤ ካልቪናውያን ግን ደኅንነት ከገሃዱ ቤተ ክርስቲያን ውጪም ይገኛል ብለው ያምናሉ። መንፈስ ቅዱስ በፈቀደው ጊዜ፥ በታና ሁኔታ ሊሠራና ሰዎችን ሊያድን ይችላል በማለት አስተምረዋል። ካልቪናውያን፥ የማትታየው ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ማብራሪያ ከዚህም ሰፋ በማድረግ፥ የማትታየው ቤተ ክርስቲያን ሁሉ አቀፋዊት ናት፤ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያንን በአንድ ጊዜ በሁሉም ቦታ ማየት የሚችል ማንም የለም፤ እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽዓት ወደ ሙላቷ አትደርስም፤ ያመኑና ያላመኑትን መለየትም አይቻልም ይላሉ።

ጥምቀት። ካልቪናውያን ቅዱስ ሥርዓታት ለእምነታቸው ምልክት ይሆኑ ዘንድ ለአማኞች ብቻ ነው ሊሰጡ የሚገባ በማለት አስተምረዋል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በእነዚህ ሥርዓታት አማካይነት ጸጋውን ያስተላልፋል። ካልቪናውያን፥ ጥምቀትን መውሰድ ያለባቸው የሚያምኑ ሰዎች ብቻ ቢሆኑም እንኳ፥ ሕፃናትም የኪዳኑ ተጋሪዎች መሆናቸውን ለማሳየት መጠመቅ ይኖርባቸዋል፤ ጥምቀት፥ ልጆቻቸው ወደ ኪዳኑ እንደሚገቡ ለወላጆች የመተማመኛ ምልክት ነው። ልጆችም በኪዳኑ ሥር ስለሚሆኑ የመጠመቅ መብት አላቸው ይላሉ።

የጌታ እራት። ጆን ካልቪን በጌታ እራት ጊዜ ክርስቶስ በኅብስቱና በወይኑ ውስጥ ይገኛል፥ የሚለውን የሉተር አስተሳሰብ ይቃወማል። መታሰቢያ ብቻ ነው የሚለውን የዝዊንግሊንም አሳብ ይቃወማል። በርሱ አስተምህሮ መሠረት፥ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን መካፈል የሚችሉት

* በገጽ 62 ላይ የሚገኘውን የግርጌ ማስታወሻ ይመልከቱ።

አማኞች ብቻ ሲሆኑ፥ ክርስቶስም በመንፈስ በመገኘት ሥጋወደሙን ለሚወስዱ ምዕመናን ጸጋውን ይሰጣል። ካልቪን አንድ አማኝ በጌታ እራት ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ይሳተፋል ቢልም፥ኅብስቱና ወይኑ ውስጥ ሳይሆን በእምነት ነው። የማያምን ሰው ሥጋ ወደሙን ቢወስድ እንኳ አማኙ የሚያገኘውን ጥቅም አያገኝም።

## የአናባፕቲስቶች [Anabaptists] ወይም የዳግማዊ መጥምቃውያን አመለካከት

ቤተ ክርስቲያን። አናባፕቲስቶች ስለ ቤተ ክርስቲያን ያላቸው አመለካከት የሮም ካቶሊኮችን አመለካከት ከመቃወም አንጻር ከሌሎች ተሐድሷውያን ይልቅ ይለያል። "አናባፕቲስት" የሚለው ስያሜ እራሱ "በድጋሚ ማጥመቅ" ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያን የአማኞች ስብስብ መሆኗን አናባፕቲስቶች አጥብቀው ይገልጣሉ። በመሆኑም ሕፃናት ማመን የሚችሉ ስላልሆኑ የቤተ ክርስቲያን አካላት አይደሉም ይላሉ። ከሉተርና ከካልቪን በተለየ መልኩ፥ አናባፕቲስቶች በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል ልዩነት እንዲኖር አድርገዋል። በዚሁ መሠረት ውጤት አስገኝቶ የነበረው ነገር፥ በጦርነት ጊዜ የጦር መሣሪያ መያዝንና መመከትን የሚከለክለው ነበር። አንዳንዶቹ እንደውም ለአናባፕቲስቶች በፖሊስ ሠራዊት ውስጥ እንዳይቀጠሩና የዳኝነት ኃላፊነትም እንዳይሰጣቸው ጠይቀዋል።

ጌታ በተራራው ስብከት ባስተማረው መሠረት ለመኖር በመሞከርም ቀላል ዓይነት የኑሮ ዘይቤን ይከተላሉ። ለቤተ ክርስቲያን ቅድስና ከፍተኛ አትኩሮት በመስጠትም፥ ሚስቶቻቸውን በሚያጉላሉ ባሎች ላይ የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ይወስዳሉ። በሌሎች ጉዳዮችም እንዲሁ ቤተ ክርስቲያናዊ የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ይወስዳሉ። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ አሳዛኙ ምዕራፍ፥ አናባፕቲስቶችን እስከሞት ድረስ በማሳደዱ ተግባር የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳትሆን፥ ሉተራውያንና ካልቪናውያን መሳተፋቸው ነው።

ጥምቀት። አናባፕቲስቶች፥ መጠመቅ ያለባቸው ያመኑ ሰዎች ብቻ ናቸው የሚል ጠንካራ እምነት አላቸው። ከዚህም የተነሣ የሕፃናትን ጥምቀት ዋጋ ቢስ እንደሆነ በመቁጠር ይቃወሙታል። በመሆኑም በሕፃንነታቸው የተጠመቁትን ሰዎች በድጋሚ እንዲጠመቁ ያደርጓቸዋል። ይህን በማድረጋቸው፥ የሕፃናትን ጥምቀት ከሚደግፈውና ዝዊንግሊ ከተባለው ሰው ጋር ይለያያሉ። ጥምቀት ሊሰጥ የሚገባው በሀሊናቸው በክርስቶስ ያላቸውን እምነት በግልጥ ለማሳየት ብቃት ላላቸው ብቻ ነው በማለት ነው የሚያስተምሩት። "አናባፕቲስት" የሚለው ስም ("አና" የሚለው ባዕድ

መነሻ በላቲንኛ "እንደገና" ማለት ነው)፥ የእምነቱ ተከታዮች በሕፃንነታቸው የተጠመቁ ሰዎችን በድጋሚ እንዲጠመቁ በመጠየቃቸው የወጣላቸው ስም ነው። የሚያስገርመው ነገር በማጥመቅ ጊዜ አንዳንዶቹ በማጥለቅ ብዙዎቹ በመርጨት ሲያጠምቁ፥ ለአናባፕቲስቶች ግን ይህ የጎላ ጉዳይ አለመሆኑ ነው።

የጌታ እራት። በጌታ እራት ጉዳይ ሉተር ከዝዊንግሊ ጋር የነበረው ግጭት በሚገባ የታወቀ ነው። ሉተር በኅብስቱና በወይኑ ዙሪያ ጌታ ይገኛል የሚለውን አሳብ ሲቀበል፥ እና ካልቪናውያን በወይኑና በኅብስቱ አማካይነት ጸጋ ይተላለፋል ብለው ሲያምኑ፥ ዝዊንግሊ ግን የጌታ እራት የክርስቶስ ሞት መታሰቢያ ብቻ ነው በማለት አስተምሯል። ሉተር፥ ክርስቶስ "ይህ ሥጋዬ ነው" ብሎ የተናገረውን ቃል በቃል ሲወስደው፥ ዝዊንግሊ ግን ኅብስቱ የክርስቶስ ሥጋ ምሳሌ ነው ብሎ ይገነዘባል። አናባፕቲስቶችም የጌታን እራት በተመለከተ የዝዊንግሊን አሳብ ይከተላሉ። ይሁን እንጂ፥ የጌታ እራት ለአናባፕቲስቶች እጅግ ታላቅ ነገር ነው። በወንድማማች ኅብረት አብሮ መብላትና መጠጣት ብርታትና መጽናናትን፥ ከዳኑ ነፍሳት ጋር መሆን ደግሞ እርግጠኛነትን እንዲሁም "የእውነተኛው የክርስቶስ አካል" የመሆንን እምነት ሰጥቷቸዋል። የጌታ እራት በአማኞች መካከል ያለው ውስጣዊ ኅብረት ማረጋገጫ፥ እንዲሁም እርስ በርስ መንፈሳዊ ጸጋ የመካፈል አንድነት የሚገኝበት ነው።

| *የተሐድሶውያን ሥነ-መለኮት* | | | |
|---|---|---|---|
| *አስተምህሮ* | *ሉተር* | *ካልቪን* | *ዝዊንግሊ/ አናባፕቲስቶች* |
| ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት | ለእምነትና ለደኅንነት ስሕተት የለሽ ብቸኛ ባለሥልጣን ናቸው። ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ክርስቶስ ያመለክታሉ። | ቤተ ክርስቲያን ሳትሆን መጽሐፍ ቅዱስ ነው የመጨረሻው ባለሥልጣን። ሳይንሳዊ ትንታኔ ለመስጠት የመጀመሪያው ሰው ነው። | ዝዊንግሊ፡- ስሕተት የለሽ ባለሥልጣን፡- ሁሉንም ድርጊት መወሰን አለበት። ቅዱሳት መጻሕፍት ይፈጸማሉ። ተራ ሰዎች ሊረዱ ይችላሉ። |
| አስቀድሞ-መወሰን | ሁሉም ሁኔታዎች በእግዚአብሔር ተወስነዋል። ሁለትዮሽ አስቀድሞ መወሰንን አስተማረ። | ሰው አቅመ ደካማ በመሆኑ የእግዚአብሔር አስቀድሞ መወሰን አስፈላጊ ነው። | አስቀድሞ መወሰን በእግዚአብሔር ጥበቃ ላይ የተመሠረተ ነው። |

| የተሐድሶውያን ሥነ-መለኮት | | | |
|---|---|---|---|
| አስተምህሮ | ሉተር | ካልቪን | ዝዊንግሊ/አናባፕቲስቶች |
| ክርስቶስ | በጌታ እራት ጊዜ፥ ሰብአዊ ተፈጥሮው -እንደ በሁሉ ቦታ መገኘት- ያለውን መለኮታዊ ባሕርይ ይወስዳል። | ቀጥተኛ አመለካከት፤ አንድ አካል በሁለት ባሕርይ፥ ምንም ውሕደት ሳይኖር። | ቀጥተኛ አመለካከት፤ አንድ አካል በሁለት ባሕርይ፥ ምንም ውሕደት ሳይኖር። |
| ሰውና ኃጢአት | ሰው በኃጢአት የተበከለና ራሱን ነጻ ማድረግ የማይችል ነው። በኃጢአት የተነሣ ጸጋ አስፈላጊ ነው። | ሰው በኃጢአት የተበከለና ራሱን ነጻ ማድረግ የማይችል ነው። በኃጢአት የተነሣ ጸጋ አስፈላጊ ነው። | ሰው በኃጢአት የተበከለና ራሱን ነጻ ማድረግ የማይችል ነው። በኃጢአት የተነሣ ጸጋ አስፈላጊ ነው። |
| ሥርየት | ክርስቶስ ስለ ሰው ዘር ሁሉ የምትክ ሞት ሞተ። | ክርስቶስ ስለ ሰው ዘር ሁሉ የምትክነት ሞት ሞተ። | ክርስቶስ ስለ ሰው ዘር ሁሉ የምትክነት ሞት ሞተ። |
| ደኅንነት | ጽድቅ በእምነት ብቻ ነው፥ በሥራ አይደለም። | በእምነት መጽደቅ ለአማኙ ጽድቅን በማልበስ የሚመጣ የእግዚአብሔር የፍትሕ ሥራ ነው። መሠረቱ ቅድመ ሁኔታ የሌለበት ምርጫ ነው። | ክርስቶስ የምትክነት ሞት ሞተ፤ የውርስና የግል ኃጢአቶችን ከፈለ። ደኅንነት በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ምርጫ ላይ የሚመሠረት ነው። |
| ቤተ ክርስቲያን | ሁሉም አማኞች ካህናት ናቸው፥ በዓለም ላይ ያሉ አማንያንን ሁሉ ያቀፈች ናት። | ደኅንነት ከቤተ ክርስቲያን ውጭም ይገኛል። ቤተ ክርስቲያን የምትታይም የማትታይም ናት። | አናባፕቲስቶች፦ ቤተ ክርስቲያን አማኞችን ብቻ ያቀፈች ናት፤ ሕፃናት አይካተቱም። ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ለየብቻ ናቸው። አማኞች የጦር መሣሪያን ፈጽሞ የማይዙ ናቸው። |
| ጥምቀት | ጸጋን ያስተላልፋል። የኃጢአት ይቅርታን ያስገኛል፤ ለደኅንነት አስፈላጊ ነው። ሕፃናት ይጠመቃሉ። | ለአማኞች ብቻ ነው፥ ሕፃናት ግን በኪዳኑ ውስጥ ያሉ መሆናቸውን ለማሳየት ይጠመቃሉ። | ዝዊንግሊ፦ ሕፃናት ይጠመቃሉ። አናባፕቲስቶች፦ አማኞች ብቻ፤ የሕፃናትን ጥምቀት ይቃወማሉ። |
| የጌታ እራት | ክርስቶስ በጌታ እራት ጊዜ በእውን ይገኛል። ያላመኑም ቢወስዱት ጥቅም ሊያገኙበት ይችላሉ። | ጸጋን ያስተላልፋሉ። አማኝ በእምነት አማካይነት ከክርስቶስ ጋር ይሳተፋሉ። | ዝዊንግሊ፦ መታሰቢያ ብቻ ነው። ኅብስቱ የክርስቶስ ሥጋ ምሳሌ እንጂ እውነተኛው አካሉ አይደለም። |

# - 5 -

# ዘመናዊ ሥነ-መለኮት

ምንም እንኳ ከአሥራ ሰባተኛው እስከ ሃያኛው ምዕተ ዓመት ያለውን እድገት ዘመናዊ ብሎ መጥራት ግር የሚያሰኝ ቢመስል፥ በሺህ የሚቆጠሩ ዓመታትን ታሪክ ከማጥናት አኳያ ሲታይ ግን ተገቢ ስያሜ ይሆናል። ይህ ርእስ ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠውም ከዚህ አንጻር ነው።

በዘመናዊቱ ቤተ ክርስቲያንና በጊዜው (በሀያኛው ምዕተ ዓመት) ትምህርተ-መለኮት እድገት መካከል ድርብርቦሽ ይታያል። በመሆኑም ይህ ምዕራፍ ተሐድሶውን ተከትለው የመጡትን ዋና ዋና ሥነ-መለኮታዊ አመለካከቶች ባጭሩ ይቃኛል።

## ኪዳናዊ ሥነ-መለኮት

ኪዳናዊ ሥነ-መለኮት፥ ከተሐድሶ እንቅስቃሴ የወጣ ወይም ያደገ ሲሆን፥ በተለይም እንደ ዝዊንግሊ፥ ቡሊንጀር፥ ካልቪንና ኮሲየስ የመሳሰሉ ሰዎች ሥነ-መለኮታዊ መጣጥፎች ውጤት ነው። እነዚህ ሰዎች፥ ዛሬ ኪዳናዊ ሥነ-መለኮት [Covenant Theology] በመባል ለሚታወቀው ትምህርት መሠረት ጥለዋል። ከ1586-1629 የኖረውና፥ ካልቪናዊው የትምሕርተ መለኮት ምሁር የባዘሉ ዮሐንስ ዎሊቢየስ [Johannes Wollebius]፥ እንዲሁም ከ1576-1633 የኖረው ፒዩሪተኑ ዊሊየም ኤምዝ [William Ames] ለኪዳናዊው ሥነ-መለኮት እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ከ1603-1669 የኖረውና ኤምዝ የተባለው ሰው ደቀመዝሙር የነበረው ዮሐንስ ኮሲየስም [Johannes Cocceius] ለኪዳናዊው ሥነ-መለኮት በሥርዓት መቀናጀት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ኪዳናዊ ሥነ-መለኮት ሁለት ዋና ዋና መልኮች ያሉት ሲሆን፥ እነርሱም የሥራ ኪዳንና የጸጋ ኪዳን በመባል ይታወቃሉ። የሥራ ኪዳን ብሉይ ኪዳን ውስጥ በግልጥ ባይጠቀስም አሳቡ ነበር። እንደ ኪዳናዊ ሥነ-መለኮታዊያን አባባል፥ እግዚአብሔር ከአዳም ጋር ኪዳን የገባው፥ ከውድቀት በፊት ነው። በዚህም ኪዳናዊ የሙከራ ጊዜ አዳም ቢታዘዝ የዘላለም ሕይወት እንደሚያገኝ ተስፋ ተገባለት፤ ባይታዘዝ ግን፥ ሞት የተገባው ሊሆን። በዚህ ሙከራ አማካይነት አዳም የሰው ዘር ሁሉ ተጠሪ ሆነ። ቢታዘዝ ኖሮ ለሰው ዘር በሙሉ የጽድቅ በረከት ይሆን ነበር። አዳም ባለመታዘዙ በኃጢአት ወደቀ፥ የርሱ አለመታዘዝ ለሰው ልጆች ሁሉ እንደውርስ የሚተላለፍ ሆነና ሁሉም በኃጢአትና በኃጢአት ሥልጣን ሥር ሆኖ ይወለድ ጀመር።

እግዚአብሔር ከውድቀት በኋላ የሰውን ዘር በሙሉ ከሚወክለው አዳም ጋር ሌላ ቃል ኪዳን ገባ። በዚሁ መሠረት ከምህረቱ ባለጠግነት የተነሣ በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ የዘላለም ሕይወትን ተስፋ ሰጣቸው። ይህ "የጸጋ ኪዳን" የተመሠረተው፥ በዋነኛነት "በቤዛነት ኪዳን" ላይ ሲሆን፥ ዓለም ሳይፈጠር በፊት በሥላሴ ዘንድ አብ በሞቱ ለዓለም ደኅንነት ለመስጠት የወደደውን ወልድን በቤዛነት ወከለው። ይህ የጸጋ ኪዳን የቤዛነት ኪዳን መፈጸሚያ በመሆኑ፥ ተፈጻሚነቱም ለተመረጡት ብቻ ይሆናል የሚል ግንዛቤ ነው ያገኘው።

## ሉተራዊ ሥነ-መለኮት

በአሥራ ስድስተኛው መቶ ምዕተ ዓመት፥ የሉተራዊነትን መመሥረት ከተል ብሎ፥ በጀርመን ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ገና ሥር መስደድ የጀመረው የአዲሱ-አርስጣጣሊስ አስተሳሰብ በሉተራዊው ሥነ-መለኮት ተጽዕኖ ተደርጎበት ነበር። ሉተራዊውን አስተምህሮ ለማጥፋት አልነበረም። ከ1635-1705 በኖረውና ፊሊፕ ያዕቆብ ስፔነር [Phillip Jacob Spener] በተባለ ጀርመናዊ መጋቢ የተመራው የሃይማኖተኛነት እንቅስቃሴ የሊቃዊነትን ሥነ-ዘዴ በመቃወም ሕዝቡን ለግልና ለመንፈሳዊ ልምምድ [Pietism]* አነሣሣ። ከ1679-1754 የኖረውና ክርስቲያን ዎልፍ [Christian Wolff] የተባለ ጀርመናዊ የሂሳብ ሊቅና ፈላስፋ፥ ማንኛውም ነገር ያለማረጋገጫ እውቅና ሊያገኝ አይገባም በማለት ሉተራዊውን ሥነ-መለኮት ወደ "አመዛዛኝነት" [ራሽነሊዝም/Rationalism]* መራው። ከዚህ አስተሳሰቡ በመነሣትም አመክንዮንና እምነትን ለማስማማት ሞከረ። ውጤቱ ግን ለአመክንዮ የበለጠ ዋጋ የሚሰጥ ሆነ።

ዘመነ-ተሐድሶን ተከትሎ እራሱን የቻለ ሉተራዊ ሥነ-መለኮት ብቅ አለ። የዚህ ሥነ-መለኮት መሠረቱ፥ ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ ['sola scriptura'] የሚለውና በክርስቲያኖች ላይ አስተማማኝ ሥልጣን ሊኖረው የሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው የሚለው ነው። ይህ እውነት ነበር፥ በ1517 ሉተርን ከሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን እንዲወጣ ያደረገውና ለሉተራዊው ሥነ-መለኮት ወደ 1600 ዓ.ም. ሁኔታ መሸጋገር ምክንያት የሆነው። የዘመነ-ተሐድሶን እንቅስቃሴ ተከትሎ፥ ለሉተራዊው ሥነ-መለኮት ወሳኝ የሆነው ሁለተኛ አስተምህሮ፥ የእግዚአብሔር ሰውን ማጽደቅ ሥራ የተመለከተ ነበር። እንደ ሉተርና ተከታዮቹ ከሆነ፥ የዚህ ጽድቅ መሠረቱ የኃጢአት ሥርየት የሚያስገኘው የክርስቶስ ሞት ብቻ ነው። በ1530 ዓ.ም. አውግስበርግ [Augsburg] በተባለው ሥፍራ የወጣው

* በዚህ ርእስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት አባሪ አንድን ይመልከቱ።

መግለጫም ማጽደቅ ማለት "አንድን ሰው ጻድቅ ብሎ ማወጅ፥ በሌላ ሰው ጽድቅ (ማለት በክርስቶስ ጽድቅ) በደለኛውን ነጻ ማውጣት ማለት ነው" ብሏል።

ሦስተኛውና ወሳኙ ሉተራዊ አስተምህሮ ደግሞ፥ 'ሶላ ፊዴ' ['sola fide']፦ ሰው ደኅንነትንና የእግዚአብሔርን ጽድቅ ለማግኘት እምነት ብቻ ነው የሚያስፈልገው የሚለው ነው።

## ካልቪናዊ ሥነ-መለኮት

ካልቪናዊው አስተምህሮ፥ ከሉተራዊውና ከአናባፕቲስታዊው ይለያል። ካልቪናዊው ሥነ-መለኮት "የክርስትና ሃይማኖት ድንጋጌዎች" [Institutes of the Christian Religion/ኢንስቲቲውትስ ኦፍ ዘ ክርስቲያን ሪሊጅን] በተሰኘው በራሱ በጆን ካልቪን መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ ነው። ቢሆንም በትምህርቱ ደጋፊዎች ዘንድ ልዩነቶች አሉ። በጥያቄና መልስ የተዘጋጁ አንዳንድ ትምህርቶችና የእምነት መግለጫዎች [Catechism/ካተኪዝም] የዚያ ዘመን ውጤቶች ናቸው። ከ1504-1575 በኖረውና ዝዊንግሊ የተባለውን የሥነ-መለኮት ሰው በተካው ጆሃን ቡሊንጀር [Johann Bullinger] በ1536 ዓ.ም. የተዘጋጀው መግለጫ ("የመጀመሪያው ሄልቬቲክ መግለጫ") እና ሌሎች ጽሑፎች የስዊዘርላንድ ትናንሽ ከተሞች ካልቪናውያን የተሳተፉባቸው ናቸው። በዚሁ ቡሊንጀር በተባለ ሰውዬ በ1566 ዓ.ም. የተዘጋጀው "ሁለተኛ መግለጫ" በላቲንኛ፥ በጀርመንኛና በፈረንሳይኛ ታትሞ ከበፊቱ የላቀ ተጽዕኖ አሳድሯል። በ1563 ሄይድበርግ [Heidelberg] በተባለችው ከተማ የተዘጋጀው የካታኪዝም ትምህርትም እስከ ዛሬ ሰፋ ያለ ተጽዕኖ አለው።

ከላይ የተጠቀሰው "የክርስትና ሃይማኖት ድንጋጌዎች" የተሰኘው የካልቪን ጽሑፍ፥ እንግሊዝ ውስጥ ባሉ ፒዩሪተኖች* እና ፕሬስቢቴሪያኖች** ዘንድ ተቀባይነትን አገኘ። ሌላው ቀርቶ አንዳንድ "የተለዩ ባፕቲስቶች" በመባል የሚታወቁ አናባፕቲስቶች፥ ደኅንነት ለተመረጡ ነው የሚለው አሳብ ተከታዮች መሆናቸውን ለመግለጥ ሲሉ የካልቪናዊው ሥነ-መለኮት ተከታዮች ሆነዋል። "የዌስትሚኒስተር

* በዚህ ርእስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት አባሪ አንድን ይመልከቱ።

** "የፕሬስቢቴሪያን [Presbyterian] ቤተ ክርስቲያን" በሁለት ባሕርያቶቿ ትታወቃለች፦ (1) በሥነ-መለኮት፥ ካልቪናዊት ናት። (2) በመተዳደሪያ ሥርዓቷ፥ በሽማግሌዎች (በግሪክ፥ 'ፕሬስቡቲየስ') በሚባሉት በጉባኤ አባላት በሚመረጡ ሽማግሌዎች ትተዳደራለች። በተጨማሪም ከተመረጡት ሽማግሌዎች አንዱ እና "አስተማሪ ሽማግሌው" (መጋቢው) በከፍተኛ፥ አውራጃ ደረጃ ቤተ ክርስቲያኒቱን ይወክላሉ።

የእምነት መግለጫ" [Westminster Confession of Faith/ ዌስትሚንስተር ኮንፌሽን ኦፍ ፌይዝ] የተሰኘው የእምነት መግለጫ፥ እንግሊዝ ውስጥ ባሉ የካልቪናዊ እምነት ተከታዮች ዘንድ የአስተምህሮ መለኪያ ሆኗል።

ካልቪናዊው ሥነ-መለኮት እስከ ኒዘርላንድ ድረስ ተስፋፍቶ ነበር። እንዲያም በመሆኑ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የነበሩ ታላላቅ ተከታዮችን አፍርቷል። ከእነዚህም ውስጥ ኸርመን ባቪንክ [Herman Bavinck] (1895-1964) እና አብርሃም ካይፐር [Abraham Kuyper] (1837-1920) የተባሉት ይገኙበታል። ካይፐር "አምስተርዳም ፍሪ ዩኒቨርስቲ" የተሰኘውን ተቋም የመሠረተና የሆላንድ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረ ነው። ሌሎችም የካልቪንን አስተምህሮ የተከተሉ የ20ኛው ክፍለ ዘመን ታላላቅ ሰዎች ነበሩ። እነዚህ ውስጥ የስኮትላንዱ ጀምስ ኦር [James Orr] እና ቢንያም ዋርፊልድ [Benjamin Warfield]፥ ግሬሽም ሜቸን [Gresham Machen] እና ቆርኔሌዎስ ቫን ቲል [Cornelius van Til] የተሰኙ አሜሪካውያን ይገኙባቸዋል።

የካልቪን ሥነ-መለኮት ዋና አሳብ በ1619 ዓ.ም. በወጣው "የዶርት ሲኖደስ ቀኖናዎች" [Synod of Dort] ውስጥ ሊጠቃለል ይችላል። ይህም ለጀኮበስ አርሚኒዮስ "ሪሞንስትረንስ" [Remonstrance] የአስተምህሮ ማረጋገጫ፥ የተሰጠ ምላሽ ነበረ። በዶርቱ ሲኖድ ካልቪናዊነትን በአጭሩ የሚገልጡ አምስት አዎንታዊ መግለጫዎች ተሰጥተዋል፡- (1) የሰው አጠቃላይ ጎዶሎነት፤ (2) እግዚአብሔር ሰዎችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መርጧል፤ (3) የክርስቶስ ደም የፈሰሰው ለተመረጡት ብቻ ነው፤ (4) የሚድኑት ሊገድቡት የማይቻላቸው ጸጋ ተሰጥቷቸዋል፤ (5) የጻድቃን ጽናት።

## ለዘብተኛ ሥነ-መለኮት

ለዘብተኛ ሥነ-መለኮት በአሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ጀርመን ውስጥ ተጀመረ። እንደ ለዘብተኛ የሃይማኖት አባት የሚታወቀው፥ ከ1724-1804 የኖረው አማኑኤል ካንት [Immanuel Kant] ነው። ካንት፥ ስለ እግዚአብሔር ህልውና የሚቀርቡ ማረጋገጫዎችን በመካድ፥ ሰው እግዚአብሔርን ለማወቅ የሚችለው በአመክንዮ ዘዴ ብቻ ነው ብሏል። ይህ ዓይነቱ የሥነ-መለኮት አቀራረብ "ዘመነ አብርሆት" የተሰኘ ሲሆን የጊዜው የሳይንስ እውቀትና ፍልስፍናዊ እንቅስቃሴ ውጤት ነው። ይህ አመለካከት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣን ባሕልና የቅዱሳት መጻሕፍትን ሥልጣን በጥርጣሬ በማየት በምክንያታዊነት ላይ ብቻ ያተኩራል። ከ1768-1834 የኖረውና ፍሬድሪክ ሽለይርማከር በመባል የሚታወቀው ሰው

"በስሜት" ላይ በማትኮር ለሥነ-መለኮት አዲስ መልክ ሰጥቶታል። ሽለይርማከር ሥነ-መለኮትን ከዘመኑ አስተሳሰብ ጋር ተስማሚ ለማድረግ ሞክሯል። በትምህርቱም ሃይማኖት በእምነት መግለጫ አይወሰንም፥ ይልቁንም ስሜትን በሚገልጡ ሥዕል፥ ሥነ-ጽሑፍና በመሳሰሉት እንጂ ብሏል። ሽለይርማከር ሃይማኖትን የሚገልጠው "የፍጹም ጥገኝነት ስሜት" በማለት ነው። ኃጢአትን ደግሞ በራስ ወዳድነት ስሜት ከዚህ ዓለም ጋር መያያዝ ብሎታል።

ከ1770-1831 የኖረው ጆርጅ ሄገል [George Hegel] ደግሞ ለዘብተኛነትን ወደ ሌላ አቅጣጫ ወስዶታል። ሄገል የአዝጋሚ ለውጥን እሳቤ ወደ ታሪክና ወደ ሃይማኖት በማምጣት፥ ታሪክ ማለት የሁለት ተቃራኒ እንቅስቃሴዎች መገናኛ ነው፤ የሁለቱም ውጤት በአንድ ላይ ጥምር ይሆናል ብሏል። ብዙ ሰዎች ከ1792-1860 የኖረው ፈርዲናንድ ባወር [Ferdinand Baur] እና ከ1844-1918 የኖረውን ዩሊየስ ዌልሃውዝ [Julius Wellhausen]፥ መጽሐፍ ቅዱስን በሂሳዊ ትችት እንዲያጠኑ ያደረጋቸው፥ የሄገላዊው ፍልስፍና ተጽዕኖ መሆኑ ይሰማቸዋል። በዚህ ሳቢያ ቅዱሳት መጻሕፍትን የጻፏቸውን ሰዎች ማንነት አስመልክቶ የነበረውን አመለካከት የሚፈታተን "ጥልቅ የትንተና ጥናት" ["Higher Criticism"/"ሀየር ክሪቲሲዝም"]* ተፈጠረ።

የለዘብተኛ ሥነ-መለኮት ዋነኛ ትምህርቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ። ለሰብአዊ አመክንዮና ለልምድ አጽንኦት መስጠት፡- ሃይማኖታዊ እምነቶች በሰብአዊ የምክንያት ሚዛንነትና በሳይንስ ተፈትነው ማለፍ አለባቸው፤ ክርስትናም ከዘመናዊው ዓለም ጋር መስማማት አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ ስሕተት አልባና ሥልጣናዊ መጽሐፍ አይደለም፡- የሌሎች ሰዎች ልምምድ ዘገባ ነው፤ ከአርአያነት ያለፈ ዘላለማዊ ዋጋና ጥቅም ያለው አይደለም። በተፈጥሯዊና በልዕለ ተፈጥሯዊ ክስተቶች መካከል ልዩነት የለም፡- በአምላክና በተፈጥሮ፥ በሰውና በእንስሳት፥ በክርስቶስና በሰው መካከል ያለውም ልዩነት ዝቅ ብሏል። የዚህ ሂደት አመክንዮአዊ ውጤት ሁሉ፥ ፓንቲይዝም [Pantheism]* ነው።

ለዘብተኛነት መጪው ዘመን በሰው ጥረት መልካም ይሆናል፥ የሚል ተስፈኛ አመለካከት ነበረው። ይሁን እንጂ በአንደኛው የዓለም ጦርነትና ሃይማኖትን በአዲስ መልክ በማየት ብቅ ባለው አዲሱ ቀጥተኛ ሃይማኖት ምክንያት በጊዜው ተቀባይነትን አጥቷል።

---

* በዚህ ርእስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት አባሪ አንድን ይመልከቱ።

## የአዲሱ ቀጥተኛ ሃይማኖት ሥነ-መለኮት

ምንም እንኳ የአዲሱ ቀጥተኛ ሃይማኖት ሥነ-መለኮት አዲስ ቢሆን ቀጥተኛነት የለውም። ይህ ሥነ-መለኮት ለለዘብተኛነት መውደቅ የተሰጠ አጸፋ ነው። የአንደኛው የዓለም ጦርነት መቀስቀስ፥ የኃጢአትን ነባራዊነት በመካድ ስለ ሰው ጥሩነት ይሟገት የነበረውን የለዘብተኛነት ሥነ-መለኮታዊ ስሕተት አጋልጧል። ከ1886-1968 የኖረው ካርል ባርት [Karl Barth]፥ ለዘብተኛ አመለካከቱን ትቶ ቅዱሳት መጻሕፍትን በአግባቡ ማጥናት ጀመረ። በ1919 የታተመው የባርት "የሮሜ መልእክት ማብራሪያ" ከለዘብተኛነት የተለየና የአዲሱ ቀጥተኛ ሃይማኖት ሥነ-መለኮት ጅማሬ ነው ተብሎ ይገመታል። ይሁን እንጂ በዚህ ውስጥ ሰፊና የተለያየ ሥነ-መለኮታዊ አስተያየቶች አሉት።

ከ(1813-1855) የኖረው ዴንማርካዊ የሥነ-መለኮት ሊቅና ፋላስፋ፥ ሶረን ኪርከጋርድ [Soren Kierkegaard] ለሥነ-መለኮት ልምምድ አስፈላጊ ነው በሚለው አሳብ ላይ አተኮረ። ይህን አመለካከት በኋላ የአዲሱ ቀጥተኛ ሃይማኖት ሥነ-መለኮታዊያን አዳበሩት። ኪርከጋርድ የአገሩ ተወላጆች የቤተ ክርስቲያንን የእምነት መግለጫ በቃላቸው በማነብነብ ወዲያው ክርስቲያንና የብሔራዊቱ ቤተ ክርስቲያን አባል ሆነው የሚቆጠሩበትን የይስሙላ ሃይማኖት ተቃወመ። በርሱ አስተምህሮ መሠረት፥ የክርስትና ሕይወት አስተምህሮን ማመን ብቻ ሳይሆን፥ ልምምድንና ራስን መስጠት ይጠይቃል። አምላክ ቅርብና በሁሉ ነገር ውስጥ የሚገኝ ነው ከሚለው የለዘብተኞች አመለካከት ተቃራኒ በሆነ መንገድ፥ የአምላክን ምጡቅነትና በቃላት የማይታወቅ መሆን አስተማረ። ሰው አምላክን ለማወቅ "የእምነት እመርታ" ያስፈልገዋል አለ። የዚህ ሰው አስተምህሮ ሥነ-መለኮት፥ "ተስፋየለሽ ሥነ-መለኮት" በመባል ይታወቃል። የእውነት መለኪያ የግል ልምምድ ነው፥ በሚለው አስተሳሰብ ላይ የሚያተኩረው ህልውነት [Existentialism]* የተፈጠረውም ከኪርከጋርድ የሥነ-መለኮት አስተምህሮ ነው።

ካርል ባርት የአምላክን ምጡቅነትና በሃይማኖት የግል ልምምድን አስፈላጊነት በመቀበል የኪርከጋርድ ተከታይ ሆነ። እግዚአብሔር ምጡቅ ከመሆኑ የተነሣ በተጨባጭ ልናውቀው አይቻለንም፤ ልናውቀው የምንችለው ሕሊናዊ በሆነ ልምምድ ነው በማለትም አስተማረ። ከ1889-

---

* ህልውነት [Existentialism] ከ1813-1855 ዓ.ም. በኖረው ዴንማርካዊ ፈላስፋ በሶረን ኪርከጋርድ የተጀመረ ፍልስፍና ነው። ይህ ፈላስፋ፥ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖረው ስለሚገባ መንፈሳዊ ግጥምጥሞሽ አስፈላጊነት አፅንኦት የሰጠና፤ ዝም ብሎ እውነታዎችንና ድንጋጌዎችን ከማመን ይልቅ በግላዊ መሰጠት ላይ አጥብቆ ያተኮረ ሰው ነው።

1966 የኖረውና ኤሚል ብሩነር [Emil Brunner] የተባለው ሰው ደግሞ የሚታወቀው፥ ለአስተምህሮ ክርስቶስ በሰጠው አጽንኦት ነው። ይህ ሰው የለዘብተኛነት አስተምህሮ ለክርስቶስ ያለውን አመለካከት በመቃወም፥ እግዚአብሔርን ለማወቅ ከእግዚአብሔር ጋር በግል መገናኘት እንደሚያስፈልግ አስተማረ። እግዚአብሔር ሰውን የሚገናኘው ሰው መከራና ጣጣ ሲገጥመው ነው ከሚለው ትምህርቱ በመነሣት ለዚህ ሰው አስተምህሮ "የጣጣ ሥነ-መለኮት" [Crisis Theology] የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። ከ1892-1971 የኖረው ራይንሆልድ ኒቡር [Reinhold Niebuhr] በዲትሮይት (አሜሪካ) ውስጥ የሠራተኞች መደብ መጋቢ እንደመሆኑ፥ ማሕበራዊ ሥነ-ምግባር ላይ ነበር ያተኮረው። ከ1884-1976 የኖረው ሩዶልፍ በልትማን [Rudolf Bultmann] የተባለው ሰው ደግሞ፥ የመጽሐፍ ቅዱስን ተአማኒነት ከዷል። በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያን ስለ እግዚአብሔርና ስለ ክርስቶስ እውነቱን ባለማስተማሯ ምክንያት ሰዎች ግራ እንዲጋቡ አድርጋለች ብሏል። አስተሳሰቡም በብዙ ሥነ-መለኮታውያን ላይ ተጽዕኖ በማሳደሩ "በልትመናዊነት" በመባል የአዲሱ ቀጥተኛ ሃይማኖት አንድ ክፍል ሆነ።

የአዲሱ ቀጥተኛ ሃይማኖት ዋነኛ አስተምህሮዎች የሚከተሉት ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ በራሱ የመለኮት አሳብ የተገለጠበት ሳይሆን፥ ስለተገለጠው ነገር የተሰጠ ምስክር ነው። ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አቻነት የለውም፥ እግዚአብሔር በቃላት አይገለጥምና። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር መገለጥ የትኩረት ነጥብ ነው። ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሊገናኝ የሚችለው፥ ከክርስቶስ ጋር በግሉ በሚያደርገው ልምምዳዊ ግንኙነት አማካይነት ይሆናል። እንደ ክርስቶስ ትንሣኤ ዓይነት የቅዱሳት መጻሕፍት ሁነቶች ታሪክ ሳይሆኑ አፈ-ታሪክ ናቸው። በዚህ ጽሑፍ አገባብ መሠረት፥ አፈ-ታሪክ ምጡቅ የሆነውን፥ በልምምድ ብቻ የሚገኘውንና ምድራዊው የታሪክ መመዘኛ እውነት ወይም ሐሰት ብሎ ተጽዕኖ የማያደርጉበትን የእግዚአብሔር እውነት ያመለክታል። ታሪክ ከታሪክ አኳያ ማረጋገጫ ይገኝለታል። በዚህ መሠረት ዝቅተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስሕተት ሊገኝበት ይችላል፥ ተገኝቶበታልም። አፈ ታሪክ ግን በታሪክ የሚረጋገጥ አይደለም። በመሆኑም የቅዱሳት መጻሕፍት ከፍተኛው ክፍል ስሕተት አይገኝበትም። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት ታሪኮች በተጠቀሰው ጊዜና ሥፍራ ሆነዋል፥ ወይስ አልሆኑም የሚለው ክርክር ጥቅም የለውም። የመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ክንውኖች አፈ-ታሪክ መሆናቸው ያላቸውን ከፍተኛ ትርጉምና ተቀባይነት አይሽረውም። እግዚአብሔር ምጡቅ ነው። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ፍጹም ልዩነት ስላለ፥ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ለማድረግ የሚቻለው "በእምነት እመርታ" ብቻ ነው።

## መደምደሚያ

ይህ እንግዲህ ታሪካዊው ሥነ-መለኮት ነው። ያለፉ ሥነ-መለኮታውያንን ጠንካራ ጎን መውሰድና፥ ስሕተታቸውን አለመቀበል የወቅቱ ክርስቲያን ኃላፊነት ይሆናል። እንዲያ ለማድረግ የሚቻለውም አስተምህሮዎችን በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን በመመዘን ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠን ለዚህ ጥቅም ነውና (2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡ 16-17)።

| ሥነ-መለኮታዊ አመለካከት፥ በዘመናዊ ቤተ ክርስቲያን | | |
|---|---|---|
| ንጽጽሮች | ተከታዮች | መለያ ባሕርያት |
| ኪዳናዊ ሥነ-መለኮት | ዮሐንስ ዎሊቢየስ፥ ዊሊየም ኤምዝ፥ ዮሐንስ ኮሲየስ፥ ዘመናዊ ተከታዮች | የሥራ ኪዳን ማለት፥ በታዛዥነት አማካይነት የሚኖር ሕይወት ማለት ነው። የፀጋ ኪዳን ማለት፥ በእምነት አማካይነት የሚኖር ሕይወት ማለት ነው። |
| ሉተራዊ ሥነ-መለኮት | ማርቲን ሉተር፥ ሉተራዊ ሥነ-መለኮታውያን | ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ። እምነት ብቻ።አማኞች በክርስቶስ ሞት ላይ በተመሠረተ እምነት አማካይነት ጽድቅን ያገኛሉ። |
| ካልቪናዊ ሥነ-መለኮት | ጆን ካልቪን፥ አብርሃም ካይፐር፥ ቢንያም ዋርፊልድ፥ ዘመናዊ ካልቪናዊ ሥነ-መለኮታውያን | የሰው አጠቃላይ ጎዶሎነት። ቅድመ ሁኔታ የሌለበት ምርጫ። ሥርየት ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ። የማይገታ ፀጋ። የቅዱሳን ጽናት። |
| ለዘብተኛ ሥነ-መለኮት | አማኑኤል ካንት፥ ፍሬድሪክ ሽለይርማከር፥ ጆርጅ ሄገል፥ ሌሎች ለዘብተኞች | ለሰው ምክንያታዊነት እና ለልምምድ አጽንኦት ይሰጣል። መጽሐፍ ቅዱስ እንከን የለሽ አይደለም። ስለ ሰው ተፈጥሮ አመለካከት አለው። |
| የአዲሱ ቀጥተኛ ሃይማኖት | ካርል ባርት፥ ሶረን ከርከጋርድ፥ ሩዶልፍ በልትመን፥ ሌሎች የአዲሱ ቀጥተኛ ሃይማኖት ሥነ-መለኮታውያን | በልምምድ ላይ አጽንኦት ማድረግ። መጽሐፍ ቅዱስ እንከን የለሽ አይደለም፤ የመገለጥ ምስክር ብቻ ነው።የመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ሁነቶች "አፈ ታሪክ" ናቸው። |

# አባሪ 1

## የተለያዩ የሥነ-መለኮት ትምህርቶች መግለጫ

ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘረው የተለያዩ የሥነ-መለኮት ትምህርቶችን የሚያመለክቱ ቃላትና ፅንሰ-አሳቦች አጫጭር መግለጫ ነው። በእርግጥ መግለጫው የተሟላ ነው ለማለት አይቻልም። ለዓመታት በተለያዩ ሰዎች ለአንዳንድ የሥነ-መለኮት ትምህርቶች መግለጫ ቢሰጥም፥ በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ትክክለኛ አለመሆናቸው በይፋ ተገልጧል።

*ሂዩማኒዝም/Humanism*። ይህ ትምህርተ-ሃይማኖት ሰው በራሱ ጥረት የራሱን ችግር የመፍታት ችሎታ ያለውና ከተፈጥሮ ውጭ የሆነ ኃይል እንደማያስፈልገው አጥብቆ የሚያምን ነው።

*ማርቅያን/Marcion*። በ2ኛው ምዕተ ዓመት፥ ከፓንተስ የተነሣው ኑፋቄ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙት አሥር የጳውሎስ መልእክቶች፥ እንዲሁም ከሉቃስ ወንጌል ከፊሉን በቀር ያልተቀበለ ነበር። ማርቅያን ክፉ አድርጎ በወሰደው በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርና ራሱን በክርስቶስ በገለጠው በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር መካከል ልዩነት እንዳለ ያመለክታል። ማርቅያን፥ የኢየሱስን የሰው ልጅነት ባለመቀበል ኢየሱስ በድንገት በ15ኛው ዓመት በቲበርስ ቄሳር ጊዜ ሙሉ ሰው ሆኖ ተገለጠ በማለት ያስተምራል።

*ምንታኑሳዊነትMontanism*። በ2ኛው ክፍለ ዘመን አሁን የቱርክ ክፍል በሆነችው በፍርግያ ይኖር የነበረውና ክርስቶስ እልከዋለሁ ያለው አጽናኝ ነኝ ያለው ሞንታኑስ ትምህርት ነው። እርሱና ተከታዮቹ የዓለም መጨረሻ በቅርቡ ይሆናል ብለው ተናግረዋል። ጥብቅና ጠንካራ የሆነ ዲሲፕሊን ያስፈልጋል ብለውም ያምኑም ነበር። ትምህርቶቹ በ381 ዓ.ም. በቁስጥንጥንያ ጉባኤ ተወግዘዋል።

*ራሽንሊዝም/Rationalism*። ከሁሉ ይበልጥ ከፍ ያለ የእውቀት ምንጭ አእምሮ ነው፤ ሰው በዚህ የማሰላሰል ችሎታው ሙሉ እውነትን ወደ ማወቅ ይደርሳል፤ ማሰላሰል የሃይማኖትን እውነት ለመወሰን መሠረታዊ ነገር መሆኑን ሰዎች ሊተማመኑበት ይችላሉ የሚል እምነት ነው።

*ሰባልዮሳዊነት/Sabelianism*። በሦስተኛው ምዕተ ዓመት በግብፅ ይኖር የነበረው ሰባልዮስ እግዚአብሔር ሦስት አካላት ያሉት ሳይሆን፥ ሦስት መገለጫዎች ያሉት አንድ አምላክ ነው በሚል ያስተማረው ትምህርት ነው። ትምህርቱ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን እንደ አብ፥ ኢየሱስ በምድር ይኖር በነበረበት ዘመን እንደ ልጅ፥ ከትንሣኤ በኋላ ደግሞ እንደ መንፈስ ቅዱስ ሆኖ መታየቱን ይገልጣል። ይህ ትምህርት በ263 ዓ.ም. በሮም ጉባኤ ተወግዟል።

*ሱስንዮሳዊነት/Socinianism*። ይህ በኢጣልያ ይኖር የነበረው የሌሊዮ ሱስንዮስ (1525-1562)፥ እና በፖላንድ የኖረው የፋውስቶ ሱስንዮስ (1539-1604) ትምህርት ነው። በትምህርታቸው ሰው ከአዳም የወረሰው ኃጢአት መኖሩን፤ የክርስቶስን መለኮታዊነት፥ እና ሥላሴን ክደዋል። ኢየሱስ "መለኮታዊነትን" የተቀዳጀው ከፍ ያለ ኑሮ ስለኖረ ሲሆን፥ ሞቱም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ያሳየው ታዛዥነት እንጂ ሌላ ነገርን አያመለክትም ብለዋል። ሱስንዮሳዊነት የዩኒተሪያኒዝም መሠረት ነው ሊባል ይቻላል።

*ስኮላስቲሲዝም/Scholasticism*። በ11ኛውና 12ኛው ምዕተ ዓመታት የክርስቲያን እምነት ትክክለኛ መሆኑን በራሽነል አመለካከት ለማሳየት በገዳም ትምህርት ቤቶች የተደረገ እንቅስቃሴ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አዳዲስ እውነቶችን ፈልጎ ከማግኘት ይልቅ፥ የቤተ ክርስቲያን የእምነት መግለጫዎችን መሠረት በማድረግ ያሉትን እምነቶች በማጥናት ላይ ያተኩራል።

*የቅድመ-ሺህ ዓመታውያን አመለካከት [Premillennialism/ ፕሪሚሌኒያሊዝም]*። ቅድመ-ሺህ ዓመታውያን የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ከሺህ ዓመት በፊት እንደሚሆንና፥ መንግሥቱን የሚመሠርተውም ክርስቶስ እንደሆነ (እንደ ድህረ ሺህ ዓመታውያን እምነት ቤተ ክርስቲያን አይደለችም) ይናገራሉ። ክርስቶስ በምድር ይነግሣል፤ በዚህ የሺህ ዓመታት አገዛዝ ወቅት የአይሁድ ሕዝብ የአብርሃምንና የዳዊትን ቃል ኪዳን ሙሉ በሙሉ ይለማመዱታል። በዚህ አመለካከት መሠረት፥ የአሁኗ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ላይ ክህደት እየጨመረ ሲሄድ ታያለች፤ በጣምም የሚከፋው ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በፊት የሚደርሰው የፍዳ ዘመን ይሆናል። ክርስቶስ ሲመጣም መንግሥቱን ለሺህ ዓመታት ይመሠርታል። ከዚያም የሙታን ትንሣኤ ተከናውኖ ላልዳኑ ሰዎች ፍርድ ይሰጥና ዘላለማዊ ግዛቱ ይቀጥላል።

*ኒዮ-ኦርቶዶክሲ/Neo-orthodoxy*። እግዚአብሔር ከፍጥረት በላይና ውጭ ነው በሚል እምነት፥ ከለዘብተኛ/ራሽኒሊዝም አመለካከት ወደ ርቱዕ ሃይማኖት የተመለሱ እምነቶችን ያጠቃልላል። እግዚአብሔር ራሱን ለሰዎች በቀጥታ የሚገልጠው በመንፈስ ቅዱስ ሥራ አማካይነት መሆኑን ያስተምራሉ። ይህም ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነቡ፥ የፀሐይን መጥለቅ ሲመለከቱ፥ ወይም በሌሎች የተለያዩ መንገዶች ሊፈጸም ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች በእግዚአብሔር ተመርተው የጻፉት ሳይሆን፥ እግዚአብሔር አልፎ አልፎ በልባቸው በተናገራቸው ታማኝ ሰዎች የተጻፈ ነው። ኒዮ-ኦርቶዶክስ መሪዎቹ ሁሉ የሚስማሙበት የተወሰነ የእምነት ትምህርት የሌለው እምነት ነው።

*የአልቦ-ሺህ ዓመታውያን አመለካከት [Amillennialism/ አሚሌኒያሊዝም]*። ይህ አመለካከት ሺህ ዓመት የሚባል ነገር ጨርሶ

የለም ብሎ ነው የሚያስተምረው። መንግሥት ቢኖር ያለው አሁን ነው፤ ይህም መንግሥት በቤተ ክርስቲያን ላይ ያለው ሰማያዊ አገዛዝ ነው ይላል። ይህ የቤተ ክርስቲያን ዘመን እስከሚያበቃና ክርስቶስ ዳግም እስኪመጣ ድረስ፥ አሁን ያሉ ሁኔታዎች እየተባባሱ ይሄዳሉ። ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በኋላ ወዲያውኑ ትንሣኤ ሙታንና ፍርድ ተከታትለው ይፈጸማሉ፤ ከዚያም ዘላለማዊ ግዛት ይመሠረታል ነው የሚለው ትምህርታቸው።

ስለ እስራኤል መንግሥትነት የተገባውን ቃል ኪዳን ሲተረጉሙም፥ ትንቢቶቹ በቤተ ክርስቲያን በኩል እየተሟሉ ነው በማለት ምሳሌያዊ (ቀጥተኛና ቃል በቃል ትርጉም ያልሆነ) ይዘት ይሰጧቸዋል። በዚህ አመለካከት መሠረት፥ ራእይ 20 የሚገልጠው በክርስቶስ የመጀመሪያና ዳግም ምጽአት መካከል በሰማይ ስላሉት ነፍሳት ሁኔታ ነው።

*አርዮሳዊነት/Arianism።* አርዮስ (በ4ኛ ምዕተ ዓመት በእስክንድርያ ይኖር የነበረ) የክርስቶስንና የመንፈስ ቅዱስን ሕልውና በሚመለከት ያስተማረው ትምህርት ነው። አርዮስ፡- 1. ክርስቶስ ዘላለማዊ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር የተፈጠረ ነው፤ 2. ከእግዚአብሔር የተለየ ባሕርይ ያለው ነው፤ 3. መንፈስ ቅዱስ ሰብዓዊነት ያለው ሳይሆን፥ በዓለም ላይ የሰፈነ የእግዚአብሔር ኃይል ነው በሚል አስተምሯል። የአርዮስ ትምህርት በኒቅያ ጉባኤ (በ325 ዓ.ም.)፥ በቁስጥንጥንያ ጉባኤ (በ381 ዓ.ም.)፥ በኬልቄዶን ጉባኤ (በ451 ዓ.ም.) ተወግዟል።

*አርሚኒዮሳዊነት/Arminianism።* የሆላንዱ ጀኮበስ አርሚኒዮስ (1559-1609) በእግዚአብሔር ደኅንነትና በሰው ኃጢአተኛነት መካከል ያለውን ግንኙነት በሚመለከት ያስተማረው ትምህርት ነው። አርሚኒዮስ እግዚአብሔር ጥቂት ሰዎች እንዲያምኑና እንዲድኑ አስቀድሞ መርጧል የሚለውን እምነት ያልተቀበለ ሲሆን፥ ሰው ከዳነ በኋላም ቢሆን ደኅንነቱን ሊያጣ ይችላል በማለት አስተምሯል። የአርሚኒዮስን የሥነ-መለኮት ትምህርት ከሚከተሉት አንዷ የመቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ናት።

*አቡሊናርዮሳዊነት/Apollinarianism።* በ4ኛው ምዕተ ዓመት በሎዶቂያ (በአሁኑ ቱርክ ውስጥ) ይኖር የነበረ አቡሊናርዮስ የተባለ ጳጳስ እምነት ነው። አቡሊናርዮስ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ሙሉ ሰው አልነበረም፤ ሙሉ ሰው ቢሆን ኖሮ፥ ነጻ ፈቃድ ስለሚኖረው ኃጢአት ለመፈጸም ይችል ነበር በማለት ያስተምር ነበር። ኢየሱስ እውነተኛ አካልና ነፍስ ነበረው፤ ነገር ግን መንፈሱ በ'ሎጎስ' ተተክቷል በሚልም ያምናል (ዮሐ. 1፡1)። ትምህርቱ በ362 ዓ.ም. በእስክንድርያ ጉባኤ፥ በ381 ዓ.ም. ደግሞ በቁስጥንጥንያ ጉባኤ ተወግዟል።

*ዩኒታሪያኒዝም/Unitarianism*። ይህ የሥላሴን ሕልውና የሚክድ ትምህርት ነው። ይህ ትምህርት፥ የሰው ዘር በመሠረቱ መልካም ነው፤ ክርስቶስ በጣም ጥሩ የሆነ ሰው ብቻ ነው፤ በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ እግዚአብሔር ይኖራል፤ ደኅንነት የሚገኘው ራስን በግብረገብነት በማሻሻል ነው በሚል ያስተምራል። ዩኒተሪያኒዝም በቀጥታ ከሱስንዮሳዊነት የመጣ ነው።

*ጥልቅ የትንተና ጥናት ("ሀየር ክሪቲሲዝም")*። ይህ መጽሐፍ ቅዱስን መልእክቱን ለመረዳት ሳይሆን በሥነ-ጽሑፍነቱ ረገድ የማጥናት መንገድ ሲሆን፥ ሦስት ዋና ዋና ትኩረቶችም አሉት፡- 1. ምንጮቹ፥ 2. የሥነ-ጽሑፉ ዓይነቶች፥ 3. የእያንዳንዱ መጽሐፍ ጸሐፊና የተጻፈበት ቀን። በእርግጥ ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ ጠቃሚ አሳቦች ቢሆኑም፥ የ19ኛውና የ20ኛው ምዕተ ዓመታት ለዘብተኛ ምሑራን ዋና ትኩረት ሆኗል። ይህ ትኩረታቸው መጽሐፍ ቅዱስ እስትንፋሰ-እግዚአብሔር መሆኑን እንዳይቀበሉና፥ መጽሐፍ ቅዱስ የጥንት ሃይማኖታዊ ታሪኮች ስብስብ ብቻ ነው ብለው እንዲያምኑ አድርጓቸዋል።

*ዶሲቲዝም/Docetism*። ክርስቶስ የእውነት ሰው ሳይሆን፥ አእምሮ የፈጠረው ምስል ነው በማለት ክርስቶስ በሥጋ መገለጡን የሚክዱ የተለያዩ የኖስቲክ ቡድኖች የሚያምኑበት ትምህርተ ሃይማኖት ነው።

*ኖስቲካዊነት/Gnosticism*። ከክርስቶስ በኋላ ለመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕተ ዓመታት ብዙ የተለያዩ ቡድኖች ያስተማሯቸውን የተወሳሰቡ የእምነት አቋሞችን ያመለክታል። መሠረታዊ እምነቶቹም፡- 1. ማንኛውም ነገር በመሠረቱ መጥፎ ነው፤ መንፈስ ደግሞ በመሠረቱ መልካም ነው፤ 2. ክርስቶስ ሰው ሳይሆን፥ ሀ) ሰውን የሚመስል መንፈስ ወይም ለ) ለሦስት የክርስቶስ አገልግሎት ዓመታት ክርስቶስ በውስጡ ያደረበት ሆኖ በመጨረሻ በመስቀል እንዲሞት ክርስቶስ ትቶት የሄደ ተራ ሰው ነው፤ 3. በሰማይ እንዲኖሩ የተፈቀደላቸው ወገኖች በልዩ ሁኔታ የተባረኩ ሰዎች ብቻ ናቸው፤ 4. ኃያሉ አምላክ ይህን ምድር ሊፈጥር አይችልም (እርሱ ኃጢአት የሌለበት ሆኖ ሳለ ዓለም ደግሞ ኃጢአተኛ በመሆኑ)፤ ፍጥረትን ያከናወነው በብሉይ ኪዳን ያህዌ በመባል የታወቀውን የእርሱ የበታች የሆነ አምላክ በመላክ ነው።

*ፓንቲይዝም/Pantheism*። እግዚአብሔር ሰብአዊነት ያለው ሳይሆን፥ በፍጥረት የሚገኙትን ኃይላትና ሕጎችን የሚያጠቃልል ነገር ነው የሚል እምነት ነው።

*ፓየቲዝም/Pietism*። በ17ኛ ምዕተ ዓመት በጀርመን አገር የተጀመረ፥ በእምነታቸው ቀጥተኛ ሆነው ሳለ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ግን በጣም የቀዘቀዙና የሞቱ ቤተ ክርስቲያኖችን የተቃወመ እንቅስቃሴ

ነው። ይህ እምነት በግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ በጸሎት፥ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን በአማኞች የግል ሕይወት ላይ በማሳየት፥ እና የቅድስና ሕይወትን በማሳደግ ላይ አትኩሯል።

*ፒዩሪታኒዝም/Puritanism*። በ16ኛው ምዕተ ዓመት አዲሲቷ የእንግሊዝ መንግሥት ቤተ ክርስቲያንን (የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን) ከሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከወረሰችው ሥርዓት ነጻ ለማድረግ በእንግሊዝ አገር የተነሣ እንቅስቃሴ ነው።

*ፔላጊዩሳዊነት/Pelagianism*። በ5ኛ ምዕተ ዓመት ፔላጊዩስ የተባለ እንግሊዛዊ መነኩሴ ያስተማረው ትምህርት ነው። ይህ ሰው፥ 1. እያንዳንዱ ሰው ልዩ የእግዚአብሔር ፍጡር እስከሆነ ድረስ፥ መልካም ወይም መጥፎ ነገር ለማድረግ ራሱ የመምረጥ ችሎታ አለው፤ 2. ኃጢአተኛ የሚያደርገውን የኃጢአት ባሕርይ ከአዳም ባይወርስም፥ ኃጢአት ሊሠራ የሚያስችለው ድክመት አለው በሚል አስተምሯል። ይህ ትምህርተ ሃይማኖት በ431 ዓ.ም. በተደረገው የኤፌሶን ጉባኤ ቢወገዝም፥ ባለፉት ዘመናት በብዙ የቤተ ክርስቲያን ክፍሎች ዘንድ ተቀባይነት አግኝቷል።

# አባሪ 2

## በዚህ መጽሐፍ የተጠቀሱ የእንግሊዝኛ ቃላት

### — የሰው ስሞች —


ሂፖሊተስ ........Hippolytus ............ 44
ሄግል፥ ጆርጅ .Hegel፥ George 17፥ 84
ሉተር፥ ማርቲን ...Luther፥ Martin .. 15
ሊምቦርክ ..........Limborch ............. 71
ልዮ ..................Leo ...................... 47
ሎምባርድ፥ ፒተር ............................
...........Lombard፥ Peter ............ 53
ሐድርያን ........Hadrian.................. 23
መቅዶንዮስ ......Macedonius............ 34
ሚልቲያደስ ......Miltiades................ 23
ማርቅያን ..........Marcion ................ 12
ማርከስ አውሬሊዮስ ............................
..........Marcus Aurelius.............. 23
ሜሊቶ .............Melito.................. 23
ሜቸን፥ ግሬሽም ............................
Machen፥ Gresham ............ 83
ሞንታኑስ ..........Montanus ............. 12
ራድበርተስ .......Radbertus ............. 49
ሰባልዮስ ..........Sabelius ............... 32
ሱስንዮስ፥ ፋውስተስ ............................
Socinus፥ Faustus............. 16፥ 68
ሴርቪተስ .......Servetus ............ 63
ስፔነር፥ ፊሊፕ ያዕቆብ ............................
Spener፥ Philipp Jakob ........ 81
ሽለይርማከር፥ ፍሬድሪክ ............................
Schleiermacher፥ Friedrich ....... 17
ቀላውዴዎስ አቡሊናርዮስ ............................
Claudius Apollinarius.............. 23
ቀሌምንጦስ .......Clement................ 18
ቅድስት አን .......Saint Anne............ 61
ቆስጠንጢኖስ ...Constantine ........... 58
ቆድራቶስ ........Quadratus............... 23
በልትማን፥ ሩዶልፍ ............................
Bultmann፥ Rudolf .......... 86
በርናባስ ............Barnabas............. 22
ቡሊንጀር፥ ዮሐን ............................
Bullinger፥ Johann.........82
ቤዛ፥ ቴዎዶር ....Beza፥ Theodore...67
ባርት፥ ካርል .....Barth፥ Karl .. 17፥ 85
ባወር፥ ፈርዲናንድ ............................
Baur፥ Ferdinand.......... 84
ባቪንክ፥ ኸርመን ............................
Bavinck፥ Herman............ 83
ብሩነር፥ ኤሚል Brunner፥ Emil...... 86
ቦናቬንቱራ ......Bonaventura ........... 50
ቦኒፌስ ስምንተኛ ....Boniface VIII .. 58
ተርቱሊያን ........Tertullian ............. 44
ታላቁ ባስልዮስ .Basil the Great...... 47
ቴዎዶስዮስ .....Theodosius ............. 34
ቴዎዶተስ ......Theodotus............... 31
ቴዎፍሎስ ......Theophilus ............. 23
ታቲያን ...........Tatian ............ 23፥ 44
ትራይፎ ..........Trypho ................. 23
ኒቡር፥ ራይንሆልድ ............................
Niebuhr፥ Reinhold.............. 86
ንስጥሮስ .........Nestorius .............. 36
አምብሮዝ ........Ambrose................ 39
አርሚኒዮስ፥ ጃኮበስ ............................
Arminius፥ Jacobus.......... 16፥ 68
አርስታዴስ ......Aristides ............... 23
አርጌንስ ..........Origen ................... 42
አርስጣጣሊስ ...Aristotle.................. 50
ኦር፥ ጀምስ ......Orr፥ James ........... 83
አርዮስ ............Arius ..................... 13
አበርላንድ ........Abelard .................. 50
አቴናጎራስ .......Athenagoras ............ 23
አትናቴዎስ .......Athanasius ............. 13
አንቶኒነስ ፒዮስ ...Antoninus Pius ... 23
አንሰለም ..........Anselm................... 50
አኩናስ፥ ቶማስ ............................
Aquinas፥ Thomas ................ 15
አውግስጢኖስ ......Augustine ............. 13

አውጣኪ ............Eutyches............. 36
አግናጥዩስ ..........Ignatius .............. 18
አቡሊናርዮስ ......Apollinarius ......... 35
ኢራስመስ ..........Erasmus ............. 60
ኤሬኔዎስ ............Irenaeus ............. 43
ኢኖሰንት ሦስተኛው ...Innocent III.. 57
ኢዘዶር .............Isidore................. 58
ኤምዝ፥ ዊሊየም Ames፥ William.... 80
ከርከጋርድ፥ ሶረን ..............................
Kierkegaard፥ Soren ................ 85
ኩርሴሊየስ .........Curcellaeus .......... 71
ካልቪን፥ ጆን .......Calvin፥ John..... 15
ካንት፥ አማኑኤል ...............................
Kant፥ Immanuel.............. 17፥ 83
ካይፐር፥ አብርሃም .............................
Kuyper፥ Abraham.................. 83
የክሌርቮው በርናርድ .........................
Bernard of Clairvaux............... 52
ኮሲየስ፥ ዮሐንስ ..................................
Cocceius፥ Johannes ................ 80
ዋርፊልድ፥ ብንያም ............................
Warfield፥ Benjamin................ 83
ዌልሃውዝን፥ ዮሊዮስ ........................
Wellhausen፥ Julius.................. 84
ዎሊቢየስ፥ ዮሐንስ ..............................
Wollebius፥ Johannes .............. 80
ዎልፍ፥ ክርስቲያን .............................
Wolff፥ Christian...................... 81
ዝዊንግሊ፥ ኧልሪክ ...............................
Zwingli፥ Ulrich....................... 16
ዳዮኒተስ ............Diognetus ............ 23
ዲዮናስዮስ .........Dionysius ............ 45
ጀሮም ...............Jerome ................ 60
ጁስቲን ማርቲር ....Justin Martyr ..... 23
ግሬሽን ...........Gratian ................... 57
ግሮቲየስ፥ ሁጎ ....Grotius፥ Hugo.... 16
ጎርጎርዮስ ቀዳማዊ ......Gregory I ..... 46
ጎርጎርዮስ ሰባተኛ ....Gregory VII .... 57
ጎትሻክ ..........Gottschalk............... 48
ፎቲየስ ...........Photius................... 44
ፓፒያስ ..........Papias..................... 18
ፔላጊዩስ .........Pelagius ................. 13
ፕሌቶ .............Plato .............. 39፥ 50
ፕራክሲየስ .......Praxeus.................. 32
ፖሊካርፕ ........Polycarp ................ 18
ቫን ቲል፥ ቆርኔሌዎስ ..........................
Van Til፥ Cornelius.................. 83

## — የቦታ ስሞች —

ሃይድልበርግ ......Heidelberg........... 82
ሂሪያፖለስ .........Hieropolis............ 18
ማንዝ ...............Mainz.................. 49
ሚላን ...............Milan ................... 39
ሚሌቬ .............Mileve................. .40
ሳምሳጢ ...........Samosota ............. 31
ሳክሶኒ ..............Saxony ................. 61
ስትራስበርግ ......Strasbourg............ 62
በርን ................Berne................... 63
ቡርዠ ...............Bourges................ 62
ቢዛንቲየም ........Byzantium............ 31
ባዘል ................Basel .................... 62
ቶሌዶ ..............Toledo.................. 48
ኒቅያ ................Nicea.................... 13
ኦርሊየንስ ..........Orleans ................ 62
አውግስበርግ ....Augsburg............... 81
አይስሌበን ........Eisleben ................ 61
ኤርፈርት ..........Erfurt.................... 61
ኬልቄዶን .........Chalcedon............. 13
ኮርቢ ...............Corbie .................. 49
ዊተንበርግ .........Wittenberg........... 61
ዙሪክ ...............Zurich................... 63
ዶርት ...............Dort ..................... 83
ጂኔቫ ...............Geneva ................. 62
ቪዬና ...............Vienna .................. 63

## - ልዩ ቃላት -


ህልውነት ........Existentialism ......... 85
'ሆሞሲዮን' ...'homoousion' . 33፥ 34
ልዕለ ተፈጥሮ .....supernatural......... 17
መንፈሳዊ ልምምድ ....Pietism.......... 81
የውርስ ኃጢአት .....original sin ...... 38
ሞናርኪያኒዝም ....Monarchianism... 31
ሞኖቴላይት .......Monothelite .......... 37
ሞኖፎሳይት .......Monophysite ........ 36
ሞዳላዊነት .........Modalistic............ 32
ሥርዓተ ሜሮን ....Confirmation ...... 55
ሥርዓተ ቀንዲል ..Extreme unction. 55
ሥርዓተ ተክሊል ...Marriage............ 55
ሥርዓተ ንስሐ .......Penance............ 55
ሥርዓተ ክህነት ....Ordination .......... 55
ሥነ-ሰብእነት ....Anthropology........ 51
ሬሞንስትረንስ ....Remonstrance....... 83
'ሶላ ፊዴ' ..........'sola fide' .......... 82
ቅርጻዊ ሞናርኪያኒዝም ........................
....Modalistic Monarchianism... 32
ቅድመ-ሺህ ዓመታውያን ......................
...........Premillennialist ............ 44
ቅዱስ ቁርባን በሚወሰድበት ግዜ ኅብስቱና ወይኑ በቀጥታ ወደ ጌታ ሥጋና ደም ይቀየራል .........................................
......Transubstantiation/
ትራንሰብስታንሺዬሽን... 14፥ 43፥ 49
'ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ' . ..................
..........'sola scriptura'............... 81
የቆስጠንጢኖስ ልገሣ .........................
....Donation of Constantine...... 58
በላኤሰብነት .........cannibalism ........ 22
ቢሾፕ.................Bishop ................ 11
ቢዛንቲን ............Byzantium........... 31
ተሐድሶአውያን .....Reformers......... 60
የተሐድሶ ትምህርት ............................
........Reformed Theology.......... 63
ተሐድሷዊ ቤተ ክርስቲያን ....................
........Reformed Church ............. 63
ትምህርቶችና የእምነት መግለጫዎች
..........Catechism........................ 82
ተገቢነት ........reasonableness......... 23
ኃያል ሞናርኪያኒዝም .........................
..Dynamic Monarchianism 31፥ 32
ነጠላ ሥርጸት ...single procession... 48
የኒቅያ ጉባኤ.....Council of Nicea.... 13
ናዝራዊ ..........Nazarenes............... 26
አልቦ-ሺህ ዓመታውያን .........................
........Amillennianialism............ 44
አመክንዮ ......reason........ 17፥ 32፥ 50
አመዛዛኝነት ........Rationalism ......... 81
አርችቢሾፕ.........Archbishop........... 11
የአስቀድሞ መወሰን አስተምህሮ............
....Predestination........ 48፥ 67፥ 69
አሳብ የሚያቀነቅኑ .....Nominalists ... 50
የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ትምህርት.........
'ዲዳኬ'....Didache...... 18፥ 21፥ 42
የአረዳድ ትንታኔ ..Deductive Logic 50
አብርሆት ......Enlightenment........... 17
አናባፕቲስት.....Anabaptist....... 16፥ 77
አንብሮ .......theses.................. 15፥ 72
አዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት ትምህርት....
.............Neo-orthodoxy............ 17
ኢቦናይታውያን .......Ebionites......... 26
ኢኮኖላትሪያ ........Iconoclastic ........ 47
የኢዘዶር ድንጋጌዎች ...........................
.........Decretals of Isidore ......... 58
ኤልቄሳውያን .......Elkesaites ........... 26
ኤየንስ ................Aeons ................ 27
ዐቃቤ እምነታውያን .....Apologists ......
.......................................... 12፥ 22
እውነትነታዊነት ......Realism............ 50
'ኡሲያስ' ..............'ousias' .......... 33
ካርዲናል.............Cardinal .............. 11
ኪዳናዊ ሥነ-መለኮት ...........................
.........Covenant Theology......... 80
ኬልቄዶን ..........Chalcedon............ 13
ክርስቲያን ሳይንስ ................................
.........Christian Science ............ 27

የክርስትና ሃይማኖት ድንጋጌዎች............
..Institutes of Christian Religion..
................................ 15፥ 62፥ 82
ዘመነ-ሊቃዊነት ...Scholasticism...... 11
ዘመነ ሬነዛንስ .........Renaissance...... 59
ዘመነ-ተሐድሶ ........Reformation..........
........................................ 11፥ 15
ዘመነ-አብርሆት .....Enlightenment... 11
የዌስትሚኒስተር የእምነት መግለጫ......
Westminster Confession of Faith
.................................................. 83
'ዲዳኬ' ......Didache...... 18፥ 21፥ 42
ዴሚኧርጅ ..........Demiurge........... 27
ድርብ ወይም ጥንድ ውፅአት ................
.....double procession................ 48
ዶሴቲሲያውያን .........Docetists ..... 31
የዶርት ሲኖደስ ቀኖናዎች ....................
.........Synod of Dort.................. 83
ገንዘብ ከፍሎ የኃጢአት ይቅርታ ማግኘት
..............Indulgence........... 60፥ 64
በጌታ እራት ሥርዓት ጊዜ በሚወሰደው ኅብስትና ወይን ዙሪያ የጌታ ሕልውና ይኖራል የሚል አመለካከት.............
.....Consubstantiation /
ካንሰብስታንሺዬሽን .............. 16፥ 76
ኖስቲክ .............Gnostic................. 26
ግጻዌ መለኮት .....Godhead ............. 32
የጣጣ ሥነ-መለኮት ..............................
.........Crisis Theology................ 86
ጥልቅ የትንተና ጥናት .........................
............Higher Criticism ........... 84
'ጰራቅሊጦስ' ........Paraclete .......... 38
'ፊሎክዌ' ............'filioque'............ 48
ፐርጋቶሪ .............Purgatory .... 14፥ 46
ፓንቲይዝም ..........Pantheism.......... 84
ፐሪስት.....................Priest ............ 11
ፐሬስቢቴሪያኖች....Presbyterians..... 82
ፖፕ.......................Pope................ 11